# ሞጁል አራት የተጨማሪ

# ዕሴት ታክስ የሥልጠና

# ማኑዋል







**የታክስ ጉዳዮች ትምህርት ዳይሬክቶሬት**

ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

**ሰኔ 2018 ዓ.ም**

**ማውጫ** ........ **ገጽ**


**ሞጁል አራት** ........ **I**

**የተጨማሪ ዕሴት ታክስ** ........ **I**

**የሥልጠና ማኑዋል** ........ **I**

**መግቢያ** ........ **V**

**ክፍል አንድ** ........ **1**

**አጠቃላይ ሁኔታ** ........ **1**

1.1. ዓላማ ........ 1
1.2. ውጤት ........ 1
1.3. ወሰን ........ 2
1.4. ትርጓሜ ........ 2
1.5. የግብይት ዋጋ ........ 6
1.6. በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ........ 7

**ክፍል ሁለት** ........ **8**

**የተጨማሪ እሴት ታክስ አከፋፈል ስርዓት እና መጣኔ** ........ **8**

2.1. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ትርጉም ........ 8
2.2. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ታሪካዊ ዳራ ........ 8
2.3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቀሜታዎች ........ 9
2.4. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ........ 10
2.5. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ስለመጣል ........ 10
2.6. ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን ........ 11
2.7. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ........ 12
*2.7.1.* የግዴታ ምዝገባ ........ *12*
*2.7.2.* በፈቃደኝነት ስለመመዝገብ ........ *13*
*2.7.3.* የምዝገባ አፈጻጸም ........ *13*
***2.7.4.*** **የቅርንጫፍ ምዝገባ** ........ *15*
*2.7.5.* የውጭ አቅራቢን ስለመመዝገብ ........ *18*
*2.7.6.* የተመዘገበ ሰው ግዴታዎች ........ *19*
2.8. የተጨ ማሪ ዕሴት ታክስ መጣኔዎች ........ 20
*2.8.1.* ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚሆንበት አቅርቦት ........ *20*
*2.8.2.* ከታክስ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶች ........ *30*

**ክፍል ሦስት** ........ **46**

**የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አቅርቦቶች** ........ **46**

3.1. ቅይጥ አቅርቦቶች ........ 46
3.2. የአደራ ሽያጭ እና በውክልና ስልጣን ደረጃ ስለማስተላለፍ ........ 47
3.3. በወኪሎች ወይም ለወኪሎች የተፈጸመ አቅርቦት ........ 47
3.4. ከቦንድድ የማምረቻ ፋብሪካ መጋዘን እቃ ወጪ ስለማድረግ ........ 47
3.5. የሰራተኞች አገልግሎት ........ 48
3.6. ያገለገሉ እቃዎች ........ 48
3.7. የዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ........ 50
3.8. ውርስ የተደረገ ተቀማጭ ገንዘብ ........ 52
3.9. የሙብት፣ የምርጫ እና የቫውቸር አቅርቦት ........ 52

3.10. ላልተገለጹ አቅርቦቶች የሚውል ቫውቸር ... 53
3.11. በቅድመ - ክፍያ የሚቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ... 54
3.12. የባለዕዳ ዕቃ አቅርቦት ... 55
3.13. የመድን አገልግሎት ... 57
3.14. ለራስ የሚደረግ አቅርቦት ... 60
3.15. የውጭ አቅራቢዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ አከፋፈል ... 61
*3.15.1.* በኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ አማካኝነት ከሩቅ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት ... *62*
*3.15.2.* በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚቀርብ የትራንስፖርት አገልግሎት ... *63*

**ክፍል አራት ... 67**

**አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ እና የአቅርቦት ዕሴት ... 67**

4.1. አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ ... 67
4.2. የአቅርቦት እሴት ... 68
*4.2.1.* ወደ ሀገር የገባ ዕቃ እሴት ... *69*
*4.2.2.* ዕቃ ወደ ሀገር ገባ የሚባልበት ጊዜ ... *70*
*4.2.3.* ወደ ሀገር በሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ላይ የሚከፈላውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማዘግየት ... *71*
4.3. በአቅርቦት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ መለወጥ ... 72
*4.3.1.* በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በሚከናወን አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም ላይ የሚደረግ ለውጥ ... *73*
*4.3.2.* በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የሚደረግ ለውጥ በሌሎች ሁኔታዎች የሚኖረው ተፈጻሚነት ... *73*

**ክፍል አምስት ... 76**

**የግብዓት ታክስ ተቀናሽ እና ማስተካከያ ስለማድረግ ... 76**

5.1 ... የግብዓት ታክስ ተቀናሽ 76
5.2. ማስተካከያ ስለማድረግ ... 84

**ክፍል ስድስት ... 87**

**የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመላሽ ... 87**

6.1. በብልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ ወደፊት ስለማሸጋገር ... 88
*6.1.1.* ወደፊት ሳይሸጋገር ተመላሽ የሚደረግ በብልጫ የተከፈለ የግብዓት ታክስ ... *88*
6.2. ዘግይቶ በተከፈለ የተመላሽ ሒሣብ ላይ ስለሚከፈል ወለድ ... 90
6.3. ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፣ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ለኢንቨስተሮች የሚከፈል ተመላሽ ሒሣብ ... 90

**ክፍል ሰባት ... 92**

**የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች ... 92**

7.1. የታክስ ደረሰኞች ... 92
*7.1.1.* የታክስ ደረሰኝ ይዘት ... *93*

7.2. የክሬዲት እና የዴቢት ሰነዶች ... 94
*7.2.1.* የክሬዲት ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፦ ... *94*
*7.2.2.* የደቢት ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፦ ... *95*
7.3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነድ እንዲሰጥ ስለመጠየቅ ... 95
7.4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች አያያዝ ... 96
7.5. በወኪሎች አማካኝነት የተከናወኑ አቅርቦቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች ... 97
7.6. የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶችን ... 98

**ክፍል ስምንት ... 98**

**በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ስለመጠቀም ... 98**

8.1. የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ... 98
8.2. የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ ተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር ... 99
8.3. የተመዘገበ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ተጠቃሚ ግዴታ ... 100
8.4. በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ መገልገል አለመቻል ... 100
8.5. የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ ዝግጁነት ... 101
8.6. በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ መጠቀምን ስለማቋረጥ ... 102
8.7. በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ የሚዘጋጅ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነድ ... 102
8.8. የመረጃ ደህንነት እና መረጃን ስለማስተላለፍ ... 103

**ክፍል ዘጠኝ ... 104**

**የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ስረዛ ... 104**

9.1. የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ ሲያቆም ስለሚሰጥ ማስታወቂያ ... 104
9.1. ምዝገባን ስለማገድ ... 105
9.2. የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን በታች በመሆን ምክንያት ስለሚቀርብ የምዝገባ ሥረዛ ማመልከቻ106
9.3. ምዝገባው የተሰረዘበት ሰው ግዴታዎች ... 107
9.4. ምዝገባ በሚሠረዝበት ጊዜ እንደተከናወኑ ስለሚቆጠሩ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች ... 108

**ክፍል አስር ... 109**

**የአስተዳደር እና የሥነ - ሥርዓት ደንቦች ... 109**

10.1. የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ... 109
10.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈያ ጊዜ ... 110
10.3. ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ታክስን ስለመሰብሰብ ... 111
10.4. ከአቅርቦቱ ተጠቃሚ ላይ ስለሚጠየቅ ታክስ ... 112
10.5. ከተከፋይ ሒሣብ ላይ የሚቀነስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ... 113
10.6. ዕቃዎችን በመመዝገብ ረገድ ስለተጣለ ገደብ ... 113
10.7. በገዢው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ... 115
10.8. የተጨማሪ እሴት ታክስ ቅጣት ... 116
10.9. የተጨማሪ እሴት ታክስ የታከለበት ዋጋ ... 117
10.10. የተመዘገበ ሰው መሞት፣ ክፍያ መፈጸም ያለመቻል ወይም መክሰር እና ንብረት በመያዣነት የተቀበለ ሰው ... 118
10.11. የተጨማሪ እሴት ታክስ ያለመክፈል ዕቅድ ... 119
10.12. የገንዘብ ምንዛሪ ... 120

## መግቢያ

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን የማበረታት ሚና ያለው፤ የካፒታል ዕቃዎችን ሳይጨምር በእቃ እና አገልግሎት ፍጆታ ላይ የሚጣል ቀጥተኛ ያልሆነ የታክስ ዓይነት ሲሆን በሃገራችን ኢትዮጵያ ከ 1994 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ተደርጎ ታክሱ ሲሰበሰብ ቆይቷል። በ 1994 ዓ.ም የወጣው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ በትንሹ 20 አመት አካባቢ ያስቆጠረ ሲሆን በአገራችን እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ረገድ የተደረጉ ለውጦችን እና ተቀባይነት ያገኙ እሳቤዎችን አጣጥሞ ለማስኬድ የማያስችል ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም አዳዲስ የኢኮኖሚ ለውጦችን እና እሳቤዎችን በአገራችን የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ በማካተት ታክሱ ለኢኮኖሚው ዕድገት የሚፈለገውን እገዛ እንዲያደርግ ማስቻል ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ በ1994 ዓ.ም የወጣው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አሁን ካለው የሀገራችን የኢኮኖሚ ለውጥ እና ነባራዊ ሁኔታ ጋር አብሮ በሚሄድ መልኩ አዲስ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም አዲስ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደንብ ተግባራዊ ተደርጓል።

ይህም የተጨማ ዕሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 ተብሎ የተሰየመ ሲሆን ለዚሁ አዋጅ ማስፈጸሚያ ደግሞ ደንብ ቁጥር 570/2017 ወጥቶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። በተለይ አሁን ላይ ተግባራዊ እየተደረጉ የሚገኙት የተጨማሬ እሴት ታክስ ህጎች ቀደም ባሉት ጊዚያት ከነበሩት የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህጎች በተለየ ሁኔታ አዳድስ እሳቤዎችን ጭምር በውስጣቸው አካተው ይዘዋል። ከነዚህም አዳድስ እሳቤዎች መካከል በአገራችን ተግባራዊ እየሆነ በሚገኘው በኢሌክትሮኒክ የግብይት ሥርዓት ከሚከናወኑ ግብይቶች ታክሱን በሚገባ መሰብሰብ የሚያስችል አሠራር፣ ከታክሱ ነፃ የመሆን መብት አተገባበር የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የታሰበውን የህብረተሰብ ክፍል ማዕከል ያደረገ እና በግብአት ታክስና በውጤት ታክስ መካከል ያለውን ሰንሰለት የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ ፍትሐዊነትንና የዜጎችንም ሆነ የንግድ ማኅበረሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሆነው ተዘጋጅተዋል።

ስለሆነም ይህ ሰነድ በዋናነት የአዋጁን እና የደንቡን ክፍል አጠቃሎ በመያዝ ለማስተማሪያነት በሚመች መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን ለማንኛውም የህግ ክርክር እንደ ማጣቀሻነት እንደማያገለግል ማሳሰብ እንወዳለን። የታክስ ህጎችን መማር፣ መሰልጠን፣ ማንበብ እና ማወቅ የታክስን እሳቤ በሚገባ በመረዳት ከታክስ ጋር ተያይዞ መብት እና ግዴታችንን ጠንቅቀን እንድናውቅ እና መብታችንን እንዲናስከብር እና ግዴታችንን እንዲንወጣ ይረዳናል።

# ክፍል አንድ አጠቃላይ ሁኔታ

## 1.1. ዓላማ

### ❖ ዋና ዓላማ

ከሥልጠናው በኋላ ሠልጣኞች መሰረታዊ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህጎች ላይ ግንዛቤው ይኖራቸዋል።

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሠረት የሥልጠና ሞጁሉን በመገንዘብ እና ውይይት በማድረግ ስለተጨማሪ እሴት ታክስ ይረዳሉ።

### ❖ ዝርዝር ዓላማ

- የተጨማሪ እሴትታክስ ምንነት እና ከታክሱ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶችን ይለያሉ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔዎችን ያብራራሉ፤
- በዜሮ መጣኔ እና ከታሱ ነጻ በሆኑ አቀርርቦቶች መካከል ያለውን ልዩነት ያብራራሉ፤
- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የምዝገባ ስርዓት ይገልጻሉ፤
- ታክሱ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች፣ ስለሚከናወኑበት ቦታ፣ ጊዜና ዋጋ ያብራራሉ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ በምሳሌ ያስረዳሉ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚደረግበትን የሕግ አግባብ ያብራራሉ፤
- ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ለመሰረዝ የሚያበቁ መስፈርቶችን ይዘረዝራሉ፤
- ከውጭ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ስለኤልክትሮኒክ ግብይትን ይገልጻሉ፤

## 1.2. ውጤት

- ታክስ ከፋዮች ስለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ፣ ስረዛ፣ ማቀናነስ፣ ስለተመላሽ፣ በገ fh ው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ያገኛሉ።
- ሕግ እና ሥርዓቱን መሠረት በማድረግ ወቅቱን ጠብቀው የተጨማሪ እሴት ታክስን አሳውቀው ይከፍላሉ።

## 1.3. ወሰን

- **የሰነዱ ሽፋን**

የሰነዱ ሽፋን የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 570/2017፣ ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ነጻ የሚሆነውን የኤሌክትሪክ እና የውሃ ፍጆታ መጠን ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 1021/2016 እና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶችን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1006/2016 አካቶ የያዘ ነው።

- **የሥልጠና ተሳታፊዎች**

ሥልጠናው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች የሚሰጥ ሲሆን የድርጅቱ (ህጋዊ ሰውነት ሙብት ያላው ድርጅት) ሥራ አስኪያጅ፣ ምክትል ሥራ አስኪያጅ እና የፋይናንስ ክፍል ሠራተኞች፤ የአሽሙር ማህበር፤ ወይም ሌላ የሚመለከተው ባለሙያ (ማርኬቲግ ማናጀሩ ወይም የሽያጭ ሠራተኛው) እንዲሁም የታክስ እንደራሴዎች ናቸው።

- **ጊዜ፡-**ሥልጠናው የሚሰጠው ለ16 ሰዓታት ነው።

## 1.4. ትርጓሜ

**"ማስተካከያ የሚደረግበት ሁኔታ"** ማለት አንድን አቅርቦት በሚመለከት፡-

- ➢ አቅርቦቱ ሲሰረዝ፤
- ➢ የአቅርቦቱ ሁኔታ መሠረታዊ ነው ሊባል በሚችል ደረጃ ሲቀየር ወይም ሲለወጥ፤
- ➢ ለአቅርቦቱ የሚፈፀመው ክፍያ የዋጋ ቅናሽ በመደረጉ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ሲለወጥ፣ የዕቃ አቅርቦትን በሚመለከት የተሸጠው ዕቃ ወይም የዕቃው ከፊል ለአቅራቢው ሲመለስ ነው።

**"ወኪል"** ማለት፡- አንድን ሰው በሚመለከት በዚህ ሰው ስም እና ትዕዛዝ የሚሠራ ማናቸውም ሰው ነው። **"የካፒታል ዕቃ"** ማለት፡- ማናቸውም ሰው ለሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የሚውል፣ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው እና ዕቃዎችን ለማምረት እና አገልግሎቶችን ለመስጠት የዋለ ንብረት ሲሆን፤ ህንፃዎችን፣ ተሽከርካሪዎችን፣ ማሽነሪዎችን፣ መሣሪያዎችን

እና ሌሎች ተመሳሳይ ግዙፋዊ ህልዎት ያላቸውን ሀብቶች ይጨምራል፤ ሆኖም የንግድ ዕቃዎችን አይጨምርም፡፡

**"ተቀናሽ የሚሆን ግዢ"** ማለት፡- የተመዘገበን ሰው በሚመለከት፣

- ➢ በሌላ የተመዘገበ ሰው ለዚህ ሰው የተፈፀመ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፤
- ➢ በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፤ ወይም
- ➢ ይህ ሰው ወደ አገር ያስገባው ዕቃ ነው፡፡

**"የኤሌክትሮኒክስ የማከፋፈያ ገበያ"** ማለት፡- አቅራቢው በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ከሩቅ የሚሰጥ

አገልግሎትን ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚታዘዝን እቃ አቅርቦት በሌላ ሰው (የማከፋፈያ መንገዱ አንቀሳቃሽ) አማካኝነት የሚያከናውንበት ድረ ገጽ፤ የኢንተርኔት ፖርታል፣ ጌትዌይ፣ መደብር፣ የገበያ ቦታ፣ የማከፋፈያ መድረክ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መንገድ ነው፡፡

**"በኢሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚታዘዝ እቃ"** ማለት፡- በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ የግዢ ትእዛዝ የተሰጠበት እቃ ነው፡፡

**"ዕቃ"** ማለት፡- ግዙፋዊ ህልዎት ያለው ማናቸውም የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ሲሆን የሚከተሉትን አይጨምርም

- ➢ ገንዘብን፣ ወይም
- ➢ በገመድ፣ በኬብል፣ በሬዲዮ፣ በብርሃን ወይም በሌላ ማናቸውም የኤሌክትሮ-ማግኔቲክ ዘዴ ወይም በተመሳሳይ ሌላ የቴክኒክ ዘዴ የሚተላለፍን ምርት፤

**"በአገር ውስጥ በጥቅል የሚሰጥ የቱሪዝም አገልግሎት"** ማለት፡- መኝታን፣ ምግብን፤ ትራንስፖርትን፣ ጉብኝትን ወይም ሌሎች የቱሪስት አገልግሎቶችን የሚጨምር አገልግሎት ነው፡፡

**"የግብአት ታክስ"** ማለት፡- የተመዘገበን ሰው በሚመለከት፡-

- ➢ ተቀናሽ የሚሆን ግዢ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ማንኛውንም አስተዳደራዊ ቅጣት ሳይጨምር ይህ ሰው ተቀናሽ የሚሆን ግዢ በሚፈጽምበት ጊዜ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ እና
- ➢ የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክስ ሆኖ እንዲቆጠር የተወሰነ የገንዘብ መጠን ነው፡፡

**"የግብአት ታክስ ተቀናሽ"** ማለት፡- በግብአት ላይ የተከፈለና ተቀናሽ እንዲሆን የተፈቀደ ታክስ ነው፡፡ **"ኢንቮይስ"** ማለት፡- ክፍያ የመፈፀም ግዴታ መኖሩን የሚገልጽ ማናቸውም ሰነድ ሲሆን የታክስ ደረሰኝን ይጨምራል፡፡

**"ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው"** ማለት፡

- ጠቅላላ አመታዊ የአቅርቦት መጠኑ ከ,2000,000 በላይ የሆነ እና ለታክሱ ያልተመዘገበ ሰው ወይም የመንግስት ተቋም ነው፡፡

**"ገንዘብ"** ማለት፡-

- በገንዘብ ቅርስ ሰብሳቢነት የተሰማሩ ከሚይዙት፣ በኢንቬስትመንት መልክ ከሚያዝ ወይም ሌሎች ስለገንዘብ የመመራመር ፍላጐት ባላቸው ከሚያዘው ውጪ ያለ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በሌላ አገር ሕጋዊ መገበያያ የሆነ ሣንቲም ወይም ወረቀት፣
- የሀዋላ ወረቀት፣ የባንክ ድራፍት፣ የቃል ኪዳን ሰነድ፣ የፖስታ ቤት ሀዋላ ወይም የገንዘብ ክፍያ ማዘዣ፣
- የገንዘብ ዋጋ ያለው እና በሕግ መሠረት መንግሥት ለሚሰበስባቸው ክፍያዎች የሚያገለግል ለሽያጭ የሚውል ቴምብር፣ ቅጽ ወይም ካርድ፣
- ክፍያን ለመፈፀም እንዲያገለግል የተሰጠ ማናቸውም ክሬዲት ካርድ ወይም ዴቢት ካርድ፤ ማናቸውም ሰው በሚያንቀሳቅሰው የባንክ ሒሣብ ገቢ ወይም ወጪ ማድረግ፤

**"የውጤት ታክስ"** ማለት፡- የተመዘገበን ሰው በሚመለከት፣

- ይህ ሰው ከሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ሊሰበስብ የሚችለው የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
- ይህ ሰው ከውጭ አገር ለተሰጠው ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ላገኘው አቅርቦት ሊከፍል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ወይም
- ለተመዘገበው ሰው የውጤት ታክስ ሆኖ እንዲቆጠር የተወሰነ የገንዘብ መጠን ነው፡፡ **"የቴሌኮሙኒኬሽን**

**አገልግሎት"** ማለት፡- መልዕክት፣ ስዕል፣ ድምጽ ወይም ማናቸውንም ሌላ መረጃ በገመድ፣ በሬዲዮ፣ በብርሃን፣ በኬብል ወይም በሌላ የኤሌክትሮ-ማግኔቲክ ዘዴ ወይም በተመሳሳይ የቴክኒክ ዘዴ ማስተላለፍ፣ ማሠራጪት ወይም መቀበል ሲሆን፣

- የማስተላለፍ፣ የማሠራጪት ወይም የመቀበል አቅምን የመጠቀም መብትን የማዘዋወር ወይም የማስተላለፍ ወይም
- ከዓለም ዐቀፍ ወይም ከአገር አቀፍ የመረጃ መረብ ጋር የማገናኘት አገልግሎትን ይጨምራል፡፡ ሆኖም የጽሑፍ፣ የስዕል፣ የድምፅ ወይም የመረጃ አቅርቦትን አይጨምርም፡፡

**"አስቀድሞ ክፍያ የተፈፀመበት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት"** ማለት፡- የስልክ ካርድ፣ የቅድሚያ ክፍያ ካርድ፣ ሒሣብ የመሙያ ካርድ ወይም ማናቸውም ሌላ አስቀድሞ ክፍያ የተፈፀመበት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሲሆን፣ በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚፈፀመውንም ይጨምራል።

**"ተቀባይ"** ማለት፡- አቅርቦትን በሚመለከት አቅርቦቱ የተፈፀመለት ሰው ነው።

**"ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት"** ማለት፡- ከኢትዮጵያ ውጪ በሚገኝ የንግድ ስራ ቦታ ባለ አቅራቢ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኝ ተቀባይ የተሰጠ አገልግሎት ነው።

- **"አገልግሎት"** ማለት፡- ከዕቃ ወይም ከገንዘብ ውጪ የሆነ ማናቸውም ነገር ነው።
- **"አቅራቢ"** ማለት፡- አቅርቦትን በሚመለከት አቅርቦቱን የሚያከናውነው ሰው ነው።
- **"አቅርቦት"** ማለት፡- የዕቃ አቅርቦት፣ የአገልግሎት አቅርቦት ወይም በቀጥታ በገfhው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ነው።

**"የዕቃ አቅርቦት"** ማለት፡-

- የዕቃ ሽያጭ፣ ልውውጥ ወይም የዕቃ ባለቤት የሆነ ሰው ዕቃውን በማስተላለፍ ረገድ ያለውን መብት በመጠቀም የሚያከናውነው ሌላ የማስተላለፍ ተግባር፣ ወይም
- በዱቤ ግfh ስምምነት ወይም በፋይናንስ ኪራይ ስምምነት አማካኝነት ዕቃዎችን በዱቤ የመግዛት ወይም የመከራየት ተግባር።

**"የአገልግሎት አቅርቦት"** ማለት፡- ከዕቃ ወይም ከገንዘብ አቅርቦት ውጪ ያለ ሌላ ማናቸውም ተግባር ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል።

- ማናቸውንም መብት መስጠት፣ ማስተላለፍ፣ ማቋረጥ ወይም መብት መጠየቅን መተው፣
- የመገልገያ ቦታን ወይም ጥቅምን ለሌላ ማመቻቸት፣
- ማናቸውንም ሁኔታ መፍቀድ ወይም አንድን ድርጊት ከመፈፀም መታቀብ፣
- ከሙቀት ወይም ከኤሌክትሪክ የሚመነጭን ኃይል፣ ጋዝ ወይም ውሃ ማስተላለፍ ወይም ማቅረብ፤ ወይም
- አንድን ምርት በገመድ፣ በኬብል፣ በሬዲዮ፣ በብርሃን ወይም በሌላ የኤሌክትሮ-ማግኔቲክ ዘዴ ወይም በተመሳሳይ የቴክኒክ ዘዴ ማስተላለፍ።

**"የታክስ ክፍልፋይ"** ማለት፡- ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር የሚከናወን የክፍልፋይ ስሌት ነው።

- ሀ/(100 + ሀ) ለዚህ ስሌት አፈፃፀም “ሀ” ማለት 15 በመቶ ተፈጻሚ የሚሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔ ነው፡፡

**“የንግድ ዕቃ”** ማለት፡-

- ማንኛውም የተመረተ፣ የተፈበረከ፣ የተገዛ ወይም ለማምረት፣ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ በማናቸውም ሁኔታ የተገኘ ዕቃ፤
- በማምረት ወይም በመፈብረክ ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ እቃ ወይም
- ለጭነት ወይም ለሥራ የሚያገለግሉ እንሰሳትን ሳይጨምር ማንኛውም እንስሳ ነው።

**“ቫውቸር”** ማለት፡- በአምጪው ለእቃ ወይም ለአገልግሎት ክፍያ ብቻ ሊውል የሚችል ቫውቸር፣ ቴምብር፣ ምትክ ሰነድ፣ ኩፖን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገር ሲሆን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚሰጡትን እና የቴሌኮሚኒኬሽን የቅድሚያ ክፍያ ካርድን ይጨምራል። ሆኖም የፖስታ ቴምብርን አይጨምርም።

## 1.5. የግብይት ዋጋ

I. የአንድ አቅርቦት የግብይት ዋጋ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጠቅላላ ድምር ይሆናል፡-

ሀ) ማናቸውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለአቅርቦቱ የከፈለው ወይም የሚከፍለው የገንዘብ መጠን፤

ለ) ማናቸውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለአቅርቦቱ በዓይነት የከፈለው ወይም የሚከፍለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፤

ሐ) የዕቃ አቅርቦትን በሚመለከት የዕቃው አቅርቦት ለተፈጸመበት የእቃ መያዣ የተከፈለውን ወይም የሚከፈለውን እና የዕቃው መያዣ ሲመለስ ተመላሽ የሚደረገውን ተቀማጭ ገንዘብ፤

መ) ለአቅርቦቱ የተከፈለው ወይም የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ እና

ሠ) በአቅርቦቱ ምክንያት የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ማናቸውም ቀረጥ፣ የኤክሳይዝ ታክስ፣ ሱር ታክስ፣ የአገልግሎት ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎች።

II. ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ የተመለከተው የአቅርቦቱ የግብይት ዋጋ በአቅርቦቱ ላይ የተከፈለውን ወይም ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አይጨምርም።

ከላይ በሮማን ቁጥር ሁለት ከተመለከተው የአቅርቦቱ የግብይት ዋጋ ላይ አቅርቦቱ በተከናወነ ጊዜ የተፈቀደው የዋጋ ቅናሽ ወይም ተመላሽ ተቀናሽ መደረግ አለበት። አቅርቦቱ ከተከናወነ በኋላ ከአቅርቦቱ ዋጋ ላይ

የተፈቀደው ተቀናሽ፣ ተመላሽ ወይም ሌላ ማስተካከያ የከፈለው ታክስ በመብዛቱ ወይም በማነሱ ምክንያት የሚደረገው ማስተካከያ መሠረት ሊሰላ ይገባል፡፡

አቅራቢው የተቀማጩን ገንዘብ ለአቅርቦቱ ክፍያ እንዲውል ካላደረገ በስተቀር ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ (ሐ) የተመለከተውን የተቀማጭ ገንዘብ ሳይጨምር የአቅርቦት የግብይት ዋጋ በተቀማጭ ገንዘብነት የተከፈለውን ወይም የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን አይጨምርም፡፡ ከአቅርቦት ጋር በተያያዘ የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባ መያዣ ለአቅራቢው ቀሪ እንዲሆን ከተደረገ የአዋጁ አንቀጽ 35 ውርስ የተደረገ ተቀማጭ ገንዘብ የሚለው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ የዱቤ ግዢ ስምምነት ወይም የፋይናንስ ሊዝ በሚመለከት የዕቃው አቅርቦት ዋጋ በስምምነቱ ወይም በኪራዩ ውል መሠረት የሚከፈለውን የፋይናንስ አገልግሎት ክፍያ አይጨምርም፡፡

## 1.6. በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት

በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የሚባለው የሚከተለው የአገልግሎት አቅርቦት ነው፡-

- የተመዘገበ ሰው ቢሆንም ባይሆንም አቅርቦቱ የተከናወነው ከኢትዮጵያ ውጪ ባለ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማያከናውን ሰው አማካኝነት ከሆነ፣
- አቅርቦቱ የተሰጠው ለተመዘገበ ሰው፣ ለመንግስት ተቋም ወይም ከፍተኛ ግብይት ላለው ያልተመዘገበ ሰው ከሆነ እና
- አቅርቦቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የንግድ ሥራ ቦታ ቢሰጥ ኖሮ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

የተመዘገበ ወይም ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ እና ከኢትዮጵያ ውጪ ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ሆኖ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያከናውነው የስራ እንቅስቃሴ (ከዚህ በኋላ <<የውጭ ሀገር የስራ ክፍል>> ተብሎ የሚጠራው) ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው የሥራ እንቅስቃሴ (ከዚህ በኋላ
<<ኢትዮጵያ የሚገኝ የስራ ክፍል>> ተብሎ ለሚጠራው) የውስጥ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ፤ የተሰጠው የውስጥ አገልግሎት ከታክሱ ነጻ የተደረገ ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ይሆናል፡፡ ይህ ተግባራዊ በሚሆንበት በውጭ ሀገር የሥራ ክፍል እና በኢትዮጵያ የስራ ክፍል መካከል የተደረገው አቅርቦት በሁለት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተከናወነ ግብይት ሆኖ ይቆጠራል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የተጨማሪ እሴት ታክስ አከፋፈል ስርዓት እና መጣኔ

### 2.1. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ትርጉም

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ በዕቃ እና አገልግሎት ላይ የሚጣል ቀጥተኛ ያልሆነ የታክስ አይነት ሲሆን ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ የተባለውም ታክሱን የሚከፍለው በንግድ ስራ ላይ የተሰማራው ሰው ካገኘው ገቢ ላይ ሳይሆን በውክልና ከተጠቃሚው ላይ ሰብስቦ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ የሚያደርገው ስለሆነ ነው፡፡ ታክሱ ከመጨረሻ ተጠቃሚው ወይም ሸማች የሚሰበሰብ በመሆኑ የፍጆታ ታክስ በመባል ይታወቃል።

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ በአቅርቦት ሰንሰለት ደረጃዎች (Supply chain) ላይ በሚፈጠር ዕሴት ወይም ከጥሬ አቅራቢው እስከ ቸርቻሪው ድረስ በሚኖረው የግብይት ሰንሰለት ወቅት በሚፈጠር እሴት ላይ የሚሰበሰብ እና የተንከባላይነት ባህሪ ያለው የታክስ አይነት ነው፡፡

### 2.2. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ታሪካዊ ዳራ

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከሌለሎች የታክስ አይነቶች አንጻር ሲታይ የቅርብ ጊዜ ታክስ ሲሆን እንደ ጎርጎሮሲያን አቆጣጠር በ20ኛው ክፍለዘመን የመጀመሪያዎቹ አካባቢ (ከ1960 -1970ዎቹ) ባሉት ጊዚያት ውስጥ እንደተጀመረ ይነገራል።

VATCalc-global (VAT calculations and reporting) የሚባለው ድርጅት በ2025 ባወጣው መረጃ በአለም ላይ ከ175 በላይ ሀገራት የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ አመላክቷል። የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የራሱ የሆነ መጣኔ ያለው ሲሆን እንደየሀገሮቹ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና የዕድገት ደረጃ መጣኔያቸውም የተለያየ ነው፡፡

በአለም ላይ ሞያዊ አገልግሎትን በስፋት በመስጠት በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው Price water house Coopers(PwC) የሚባለው የብሪትሽ ካምፓኒ በሂሳብ አያያዝ፣ በታክስ፣ በአመራር ሰጭነት እና በሌሎችም ሞያዎች የማማከር ስራ የሚሰራ ትልቅ ድርጅት ነው፡፡ ይህ ድርጅት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ2025 ባወጣው መረጃ በዓለም ላይ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መጣኔ ያላቸውን አገራት ከታች ባለው ሰንጠረfh መሰረት አስቀምጧል።

| የሀገሬት ስም | ከፍተኛ የታክስ መጣኔ | የአገሬት ስም | ዝቅተኛ የታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| ሀንጋሪ | 27% | ኦማን | 5% |
| ፊንላድ | 25.5% | ዩናይትድ አረብ ኤምሬት | 5% |
| ክሮሺያ | 25% | ታይላንድ | 7% |
| ኖርዌ | 25% | ናይጀሪያ | 7.5% |
| አይስ ላንድ | 24% | ኮሪያ ሪፐብሊክ | 10% |
| ግሪክ | 24% | ሞንጎሊያ | 10% |
| ፖላንድ | 23% | ቬትናም | 10% |
| ጣሊያን | 22% | ካምቦዲያ | 10% |

የተጨማሪ እሴት ታክስ በእኛም ሀገር በሚመረቱና ከውጭ አገር በሚገቡ ዕቃዎችና ሌሎችም አገልግሎቶች ላይ የሚሰበሰበውን የሽያጭ ታክስ ተክቶ ከታህሳስ 23 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ ነው፡፡ አሁን ላይ ቀድሞ የነበረው አዋጅ በአዋጅ ቁ.1341/2016 የተተካ ሲሆን ይህ አዋጅ አሁን ካለው የኢኮኖሚ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ተግባራዊ እንዲደረት በአዋጁ የተቀመጡት የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔዎች ሁለት ሲሆኑ እነሱም ዜሮ በመቶ (0%) እና አስራ አምስት በመቶ (15%) ናቸው፡፡

## 2.3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቀሜታዎች

- ➢ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ከውጭ ከሚገቡ ምርቶች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይረዳል፡፡
- ➢ ለካፒታል ዕቃዎች የሚደረገው የታክስ ተመላሽ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል፡፡
- ➢ ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች ላይ ለግብዓቶች የተከፈለው ታክስም ተመላሽ ይደረጋል፡፡
- ➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም በደረሰኝ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን በመሆኑ፤
  - ✓ በቀላሉ ሳይከፈል ሊታለፍ ወይም
  - ✓ ሊጭበረበር የሚችል ታክስ ባለመሆኑ
  - ✓ የታክስ ስወራንና ማጭበርበርን በመቀነስ
  - ✓ በታክስ ሕግ አፈፃፀም ሊኖር የሚገባን ትክክለኛነትና ፍትሐዊነት በተሻለ አኳኋን ያስጠብቃል፡፡

- ➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት አነስተኛ ገቢ ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሚዛናዊ ያልሆነ ጫና እንዳይፈጠር ለኑሮ መሠረታዊ የሆኑ የፍጆታ እቃዎችና አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## 2.4. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ

ማናቸውም በተከታታይነት ወይም በመደበኛነት እና በሙሉ ወይም በከፊል የግብይት ዋጋን በማስከፈል አንድ ሰው ለሌላ ሰው የሚያቀርበው ወይም ለማቅረብ የሚፈልገው ዕቃ ወይም አገልግሎት ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ይሆናል፡፡

ማናቸውም ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በማስጀመር፣ በማቋረጥ ወይም መልሶ በማደራጀት ረገድ የሚያከናውነው ማናቸውም ሥራ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የተከናወነ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

- የሚከተሉት ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ ሆነው አይቆጠሩም፡-
  - ➢ ተቀጣሪ የሚያከናውነው ሥራ፣
  - ➢ ማናቸውም ግለሰብ ለትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ወይም ለመዝናናት የሚያከናውነው እንቅስቃሴ ወይም
  - ➢ ከግለሰብ ውጪ ማናቸውም ሌላ ሰው ለማህበርተኞቹ ወይም ለባለቤቶቹ ወይም ግንኙነት ላላቸው ሰዎች ጥቅም የሚያከናውነው የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ወይም የመዝናኛ እንቅስቃሴ፡፡

## 2.5. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ስለመጣል

- ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አቅርቦቶች ላይ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡
  - ➢ በተመዘገበ ሰው የሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፤
  - ➢ ማናቸውም ሰው ወደ ሀገር በሚያስገባው ዕቃ፤
  - ➢ ለተመዘገበ ሰው፣ ለመንግሥት ተቋም ወይም ከፍተኛ ግብይት ላለው ያልተመዘገበ ሰው የሚቀርብ በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፡፡

ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ወደ ሀገር በሚገባ ዕቃ ወይም በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰላው በዕቃው ወይም ወደ ሀገር በሚገባው አቅርቦት ዋጋ ላይ እንደየ አቅርቦቱ ባህሪያት ዜሮ በመቶ የሚመለከተው ከሆነ ዜሮ በመቶ፤ አስራ አምስት በመቶ የሚመለከተው ከሆነ አስራ አምስት በመቶ ተፈጻሚ በማድረግ ይሆናል፡፡

ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋመው አቅርቦቱ በተከናወነ ጊዜ ሲሆን፤ ታክሱ አቅርቦቱን ባከናወነው የተመዘገበ ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የሚኖረውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተከፋይ የተጣራ ሂሳብ ታክሱን ሊያስታውቅ በሚገባው ጊዜ ውስጥ መክፈል አለበት።

በማናቸውም ሕግ የተመለከተው ቢኖርም የተመዘገበው ሰው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የአቅርቦቱ ተጠቃሚ ከሆነው ሰው መልሶ የመጠየቅ መብት **አለው።** ነገርግን ግብር ከፋዩ በራሱ ለመመዝገብ ማመልከቻ ካላቀረበና በታክሱ ባለስልጣን ውሳኔ የተመዘገበ ሰው ከመመዝገቡ በፊት ያከናወነውን ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም።

ወደ ሀገር በሚገባ አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋመው የካፒታል ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲዘገይ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ አቅርቦቱ ወደ ሀገር በገባበት ጊዜ አስመጪው ታክሱን መክፈል አለበት።

በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋመው አቅርቦቱ በተከናወነ ጊዜ ሲሆን፣ አገልግሎቱን ያገኘው የተመዘገበ ሰው፤ የመንግሥት ተቋም ወይም ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው ታክሱን መክፈል አለበት።

## 2.6. ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን

የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚወሰነው እና የሚሰበሰበው እንደአግባብነቱ በገቢዎች ሚኒስቴር ወይም በጉምሩክ ኮሚሽን ይሆናል። ሆኖም የገቢዎች ሚኒስቴር ስለእርሱ ሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስን እንዲወስኑ እና እንዲሰበስቡ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮዎች ውክልና ሊሰጥ ይችላል። ነገርግን ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ ውክልና ሊሰጥ የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል።

- የገቢዎች ሚኒስቴር በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር ውስጥ ቢሮ የሌለው ከሆነ፤
- በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር የኢንተርኔት ግንኙነት ውስን በመሆኑ ወይም ጭራሹንም የሌለ በመሆኑ ምክንያት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ታክስ ለማስታወቅ እና ለመክፈል የማይችሉ ሆኖ ከተገኘ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር የሚሰጠው ውክልና የሚያገለግለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመሰብሰብ ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስን መወሰን፣ የግብአት ታክስን ክሬዲት ማድረግ፣ ተመላሽ መስጠት፣ የታክስ ሕጉን መሠረት

በማድረግ አቅርቦቶች ከታክሱ ነጻ እንዲሆኑ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆን መወሰንን ጨምሮ ሌሎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተያያዘ የተሰጡ ሃላፊነቶች በሙሉ የገቢዎች ሚኒስቴር ይሆናሉ።

ታክሱን ለመሰብሰብ ውክልና የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ በውክልናው መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሰበሰበውን ታክስ ወሩ በተጠናቀቀ በአምስት ቀን ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለገቢዎች ሚኒስቴር ገቢ ማድረግ አለበት።

የገቢዎች ሚኒስቴር ከግለሰብ ግብር ከፋዮች ከተሰበሰበው ገቢ ውስጥ የየክልሉ ድርሻ የሆነውን ወሩ በተጠናቀቀ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ የገቢው ባለቤት ለሆነው ክልል ማስተላለፍ አለበት። የክልል ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች በተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደር ረገድ ሊያከናውኑት የሚገባ ተግባር በፌዴራል እና በክልል የገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች በሚፈረም የጋራ መግባቢያ ስምምነት ይወሰናል።

## 2.7. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ

### 2.7.1. የግዴታ ምዝገባ

ማናቸውም ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘረውን የሚያሟላ ከሆነ የመመዝገብ ግዴታ አለበት።

- ➢ በማናቸውም የ 12 ወራት ጊዜ መጀመሪያ በዚህ ሰው የሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ጠቅላላ ድምር 2,000,000 ብር ሊበልጥ እንደሚችል የሚያሳምን ምክንያት ሲኖር፣ ወይም
- ➢ በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ መጨረሻ ወይም ከዚህ ባነሰ ጊዜ ውስጥ በዚህ ሰው የተከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) ብር የጠቅላላ አቅርቦት ድምር ሲኖር፤
- ➢ የታክሱ ባለስልጣን አንድ ሰው የመመዝገብ ግዴታ ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን መድረሱን በሚያሰላበት ጊዜ ከዚህ ሰው ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ያከናወነውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ጨምሮ መደመር አለበት።
- ➢ አንድ ሰው የመመዝገብ ግዴታ የሚያስከትለው የገንዘብ መጠን ላይ መድረሱ በሚሰላበት ጊዜ የሚከተሉት ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም።
    - ✓ ይህ ሰው ለሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የዋለን የካፒታል ዕቃ ሽያጭ የሚመለከት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፣
    - ✓ አንድ ሰው የሚያከናውነውን ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመሸጡ ምክንያት ወይም ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በዘላቂነት በማቆሙ ምክንያት የሚኖረውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፤ ነገርግን የአንድ ሰው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ

ወይም የዚህ ሰው ከፊል ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል ገዝቶ መሸጥ በሚሆንበት ጊዜ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል ገዝቶ በመሸጥ ተግባር ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

- ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚያከናውን የመንግስት ተቋም የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት ሲሆን ነገርግን በፍቃደኝነት ለመመዝገብ ሊያመለክት ይችላል። ይሁን እንጂ ከንግድ ስራ ወይም በተመሳሳይ አቅርቦት ስራ ላይ ከተሰማራ የንግድ ስራ ጋር ተወዳዳሪ በሆነ አኳኋን በመደበኛነት ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ስራ ላይ የተሰማራን የመንግስት ተቋም አይጨምርም።

## 2.7.2. በፈቃደኝነት ስለመመዝገብ

የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት ሰው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የሚያከናውን ከሆነ ወይም ለማከናወን ያቀደ ከሆነ በፈቃደኝነት ለመመዝገብ ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል። ይህ ሰው የፍቃደኝነት የምዝገባ ማመልከቻ ሊያቀርብ የሚችለው በዓመቱ ያከናወነው ወይም ሊያከናውን የሚችለው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦቱ ዋጋ ከ 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) ብር የሚበልጥ ሲሆን ነው።

## 2.7.3. የምዝገባ አፈጻጸም

- የግዴታ የምዝገባ ማመልከቻ የቀረበለት የታክስ ባለስልጣን አመልካቹ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት መሆኑን ሲያምንበት ይመዘግበዋል።
- የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ግዴታ ከሚኖርበት ቀን አንስቶ በ 7 ቀናት ውስጥ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለታክሱ ባለስልጣን የምዝገባ ማመልከቻ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ይህን ማድረግ ካልቻለ የታክስ ባለስልጣኑ በራሱ ውሳኔ እንዲመዘገብ ያደርጋል።
- የታክሱ ባልስልጣን የፍቃደኝነት የምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበ ሰው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላቱን ሲያረጋግጥ መመዝገብ አለበት።

  - ✓ በዓመቱ ያከናወነው ወይም ሊያከናውን የሚችለው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦቱ ዋጋ 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) ብር የሚበልጥ ሲሆን፣
  - ✓ አመልካቹ የኢንተርኔት አድራሻን ወይም የማህበራዊ ሚዲያ አድራሻን ጨምሮ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ የሚያከናውንበት ቋሚ አድራሻ ያለው ከሆነ፣
  - ✓ አመልካቹ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ ማከናወን የጀመረ ከሆነ፡-

- የሥራ እንቅስቃሴውን የሚያሳዩ ተገቢ ሰነዶችን የያዘ ከሆነ፣
- በታክስ ሕጐች የተጣሉበትን ግዴታዎች የተወጣ ከሆነ፣

✓ ተገቢ የሆነ ሰነዶችን መያዝ እና በቋሚነት እና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢን ማሳወቅን ጨምሮ አመልካቹ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግን መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች የሚወጣ መሆኑን የሚያሳምኑ መረጃዎች ያሉ ከሆነ ነው።

➢ የታክሱ ባለስልጣን የግዴታም ሆነ የፍቃደኝነት የምዝገባ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን አንስቶ በ21 ቀናት ውስጥ በቀረበው ማመልከቻ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የሚገልጽ ምላሽ ለአመልካቹ መስጠት አለበት።

➢ የታክሱ ባለስልጣን ለተመዘገበው ሰው ከታች የተዘረዘሩትን መረጃዎችን የያዘ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት።

✓ የተመዘገበውን ሰው ስም፣ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤

✓ የተመዘገበውን ሰው ልዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር፤

✓ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበትን ቀን እና

✓ ምዝገባው የጸና የሚሆንበትን ቀን።

➢ ከአንድ የንግድ ሥራ ቦታ በላይ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም ለእያንዳንዱ የንግድ ሥራ ቦታ የሚያገለግል የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጂ እንዲሰጠው ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ማቅረብ የሚችል ሲሆን የታክሱ ባልስልጣንም ቅጂ ወይም ቅጂዎችን መስጠት አለበት። አንድ ሰው "የተመዘገበ ሰው" ነው ሊባል የሚችለው፡-

✓ በተመዘገበው ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ወይም

✓ ለመመዝገብ ግዴታ እያለበት በ7 ቀናት ውስጥ ማመልከቻ ያላቀረበ ከሆነና ይህንንም ባለስልጣኑ ሲያረጋግጥ በራሱ ውሳኔ እንዲመዘገብ የሚያደርገው ከሆነ የመመዝገብ ግዴታ ከተጣለበት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ይህ ሰው የተመዘገበ ሰው ነው ሊባል ይችላል።

### 2.7.4. የቅርንጫፍ ምዝገባ

- የቅርንጫፍ፤ የስራ ክፍል ወይም የአንድ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የተለየ ምዝገባ "የቅርንጫፍ ምዝገባ" ይባላል።
- የተመዘገበው ሰው የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም የተለየ የቅርንጫፍ ምዝገባ ለሚያስፈልገው ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ፤ የስራ ክፍል ወይም ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የቅርንጫፍ ምዝገባ እንዲፈቀድለት ማመልከት አለበት። አዲስ የሚመዘገብ ሰው የምዝገባ ማመልከቻ እና የቅርንጫፍ ምዝገባ ማመልከቻ በአንድ ጊዜ ሊያቀርብ ይችላል።

- የተመዘገበ ሰው አንድ ምዝገባ ብቻ ያለው መሆኑ ግዴታውን በመወጣት ረገድ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድርበት ከሆነ የቅርንጫፍ ምዝገባ እንዲፈቀድለት ሊያመለክት ይችላል። የታክሱ ባለስልጣን ታክስ ከፋዩ አንድ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ በትክክል ችግር የሚያስከትልበት መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ ይወስናል።

- የቅርንጫፍ ምዝገባ ሊፈጸም የሚችለው የታክሱ ባለስልጣን ሲፈቅድ ብቻ ሲሆን አመልካቹ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት።

    ✓ አመልካቹ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ መሆን አለበት። ነገርግን በፈቃደኝነት የተመዘገበ መሆን የለበትም።

    ✓ ማመልከቻው የአመልካቹን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ቁጥር የያዘ እና በአመልካቹ የተፈረመ መሆን አለበት።

    ✓ አመልካቹ የንግድ ስራውን በኩባንያ አማካኝነት የሚያከናውን መሆን አለበት።

- አመልካቹ ለንግድ ስራው ሁሉ አንድ የታክስ ማስታወቂያ እንዲያቀርብ ቢደረግ ይህንን ግዴታውን መወጣት ሊያደርስበት የሚችለውን ጫና ማስረዳት ያለበት ሲሆን በተለይም በማመልከቻው መሰረት ባይፈቀድለት ሊያጋጥመው የሚችለውን ችግር እና በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ለሁሉም የንግድ ስራው የተጠቃለለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ሊያቀርብ የማይችልበትን ምክንያት ማብራራት አለበት። የቅርንጫፍ ምዝገባ የተጠየቀለት ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ገንዘብ መቀበል፤ መክፈል እና የሂሳብ መግለጫ ማቅረብን ጨምሮ ከተመዘገበው ሰው ዋና

መስሪያ ቤት እና ከሌሎች የስራ ክፍሎች የተለየ ራሱን የቻለ የሂሳብ ስርአት ሊኖረው ይገባል፡፡

- አመልካቹ ሂሳቡን ከማጠቃለሉ በፊት የተለየ ሂሳብ ሲያዘጋጅ የነበረ መሆን አለበት፡፡ እያንዳንዱ የቅርንጫፍ ምዝገባ የተጠየቀለት ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በሚያከናውነው የስራ እንቅስቃሴ ወይም በሚገኝበት አድራሻ ተለይቶ የሚታወቅ መሆን አለበት፡፡ እያንዳንዱ የቅርንጫፍ ምዝገባ የተጠየቀለት ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ከዋናው መስሪያ ቤት ጋር አንድ አይነት የሂሳብ ጊዜ እና የሂሳብ ጊዜ መጨረሻ የሚከተል መሆን አለበት፡፡ አዲስ የሚመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ሊያሟሉ የሚገባውን ቅደመ ሁኔታ ጨምሮ የታክሱ ባለስልጣን የሚወስናቸው ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡፡
- የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበ ሰው በጽሁፍ የሚያቀርበውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ የተመዘገበው ሰው ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ወይም የስራ ክፍል ወይም በተናጠል ለሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ራሱን የቻለ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ያለው መሆኑን እና በሚያከናውነው የስራ እንቅስቃሴ የተለየ ባህሪ ወይም ባለበት አድራሻ ተለይቶ የሚታወቅ መሆኑን ሲያምንበት የተመዘገበው ሰው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በግለሰብ ደረጃ የሚያከናውነውን አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቅርንጫፍ ወይም የስራ ክፍል ወይም በተናጠል የሚያከናውነውን ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ራሱን የቻለ የተመዘገበ ሰው አድርጎ እንዲያስመዘግብ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ቅርንጫፉ፣ የስራ ክፍሉ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ራሱን ችሎ እንዲመዘገብ የሚፈቀደው የታክሱ ባለስልጣን ለተመዘገበው ሰው በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ የተመለከቱ ሁኔታዎች እና ገደቦች እንደተጠበቁ ይሆናል፡፡
- የተመዘገበው ሰው ያሉት ቅርንጨፎች፣ የስራ ክፍሎች ወይም የተለዩ ታክስ የሚከፈልባቸው የስራ እንቅስቃሴዎች ራሳቸውን ችለው እንዲመዘገቡ ከተደረገ፡-
  - ✓ የተመዘገበው ሰው እና የዚህ ሰው ቅርንጫፎች፣ የስራ ክፍሎች እና የተለየው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች እንደሆኑ ይቆጠራል፡፡
  - ✓ ቅርንጫፉ፣ የስራ ክፍሉ ወይም የተለየው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ እራሱን እንደቻለ ሰው ይቆጠራል፡፡
  - ✓ በቅርንጫፎች እና በስራ ክፍሎች ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ሰው መመዝገብ ያለበት በራሱ ስም እንጂ በቅርንጫፍ እና በስራ ክፍሎች ስም ሊሆን አይችልም፡፡
  - ✓ እያንዳንዱ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ተለይቶ

የሚታወቅበት የቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የኩባንያው የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ንኡስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር ሊኖረው ይገባል።

- ✓ ለተመዘገበው ቅርንጫፍ የሚሰጠው "ንኡስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር" የተመዘገበው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሲሆን በቅርንጫፍ፣ በስራ ክፍል ወይም በተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ጥቅም ላይ የሚውል ንኡስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መሆኑን ለማሳየት ተጨማሪ መለያ ሊኖረው ይገባል።
- ✓ በታክስ ባለስልጣኑ ተለይቶ የተመዘገበ እያንዳንዱ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ራሱን የቻለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት። እያንዳንዱ ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የአመልካቹ አካል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ እሴት ታክስ ህግ የተጣሉ ግዴታዎች ሁሉ በተመዘገበ ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆኑበታል።
- ✓ የታክሱ ባለስልስጣን ለቅርንጫፍ፣ ለስራ ክፍል ወይም ለተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ሊከፈል የሚገባውን ተመላሽ በተመዘገበው ሰው ወይም በተመዘገበው ሰው ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ወለድ እና መቀጫ ለማሟላት ሊጠቀምበት ይችላል። ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ለዋናው መስሪያ ቤት ወይም ለሌላ ተለይቶ ለተመዘገበ ቅርንጫፍ የሚያቀርበው አቅርቦት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተፈጸመ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። አቅራቢው ለአቅርቦቱ የታክስ ደረሰኝ መስጠት ያለበት ሲሆን ተቀባዩ በአቅርቦቱ ላይ ለከፈለው ታክስ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊጠይቅ ይችላል። የተመዘገበው ሰው ዋና መስሪያ ቤት ተለይቶ ለተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የደለደለው የጠቅላላ አገልግሎት ወጪ ዋናው መስሪያ ቤት በክፍያ ለቅርንጫፍ፣ ለስራ ክፍል ወይም ለተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የፈጸመው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል።

- በተመዘገበው ዋና መስሪያ ቤት እና ተለይቶ በተመዘገበ ቅርንጫፍ ወይም ተለይተው በተመዘገቡ የተመዘገበው ሰው ቅርንጫፎች መካከል የሚደረግ ግብይት ተለየተው በመመዝገባቸው ምክንያት የተለየ

የታክስ ጥቅም የሚገኝበት (የታክስ ዕቅድ) እንዳይሆን በታክሱ ባለስልጣን ጥብቅ ክትትል ሊደረግበት ይገባል።

- እያንዳንዱ ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል፣ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ለሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ተለይቶ የተሰጠውን ንኡስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ቁጥር በመጠቀም ደረሰኝ መስጠት አለበት።
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታን ለሚያስከትለው የግብይት መጠን አፈጻጸም እያንዳንዱ ተለይቶ የተመዘገበ የአንድ ኩባንያ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል፣ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ግብይት የኩባንያው አቅርቦት ውስጥ ይደመራል።
- የታክሱ ባለስልጣን የሚደረገውን የግብአት ተቀናሽ በቅርንጫፍ ደረጃ ሳይሆን በተመዘገበው ሰው ዋና መስሪያቤት ደረጃ እንዲፈጸም ሊያዝ ይችላል።

### 2.7.5. የውጭ አቅራቢን ስለመመዝገብ

- የውጭ አቅራቢዎች በታክሱ ባለስልጣን የጸደቀውን የምዝገባ ቅጽ በመጠቀም በኦንላይን የምዝገባ ዘዴ ለመመዝገብ ማመልከት አለባቸው። የምዝገባው ማመልከቻ ቅጽ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል።
- የንግድ ሰሙን ጨምሮ የውጭ አቅራቢውን ስም፤ የውጭ አቅራቢውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ፋክስ እና የሚገኝበትን የኤሌክትሮኒክ ዝርዝር፤ የውጭ አቅራቢው በኢትዮጵያ የሚኖርበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ግዴታ የሚወጣለትን ሰው ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ ፋክስ እና የሚገኝበትን የኤሌክትሮኒክ ዝርዝር፤ የውጭ አቅራቢው ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውንበት ዌብሳይት ወይም ዩኒፎርም ሪሶርስ ሎኬተር (U.R.L.)፤ የውጭ አቅራቢው ነዋሪ በሆነበት አገር የተሰጠው ብሄራዊ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፤ የውጭ አቅራቢው የንግድ ስራ በተመዘገበበት ወይም በተቋቋመበት አገር የተሰጠው የምስክር ወረቀት እና የታክሱ ባለስልጣን የሚጠይቀው ሌላ መረጃ፤ የታክሱ ባለስልጣን የውጭ አቅራቢው በምዝገባ ማመልከቻው የሰጣቸውን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።
- በዚህ ሁኔታ የታክሱ ባለስልጣን የውጭ አቅራቢውን ከመዘገበ በኋላ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል የሚያስችለውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር መስጠት ያለበት ሲሆን ታክስ የሚከፈልባቸውን አቅርቦቶች ማቅረብ ያቋረጠ የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።

## 2.7.6. የተመዘገበ ሰው ግዴታዎች

- ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቅሴ በማይንቀሳቀስ የስራ ቦታ የሚያከናውን ማናቸውም የተመዘገበ ሰው፡-
  - ✓ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በሚያካሂድበት ዋንኛ የስራ ቦታ በግልጽ በሚታይ ስፍራ ዋናውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት የመለጠፍ፤
  - ✓ የተሠጠውን የተጨማ ዕሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጂ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በሚያካሂድባቸው ሌሎች የስራ ቦታዎች ሁሉ በግልጽ በሚታይ ሥፍራ የመለጠፍ ግዴታ አለበት።
- የተመዘገበ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበበትን ዝርዝር መረጃ ታክስ የሚከልበትን ስራ በሚያከናውንበት ዌብሳይት እና የማህበራዊ ሚዲያ አድራሻ ላይ ማስፈር አለበት።

- የተመዘገበው ሰው ከታች በተዘረዘሩት መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲያጋጥም ይህንኑ ለውጥ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።
  - ✓ የተመዘገበው ሰው የስልክ ቁጥር፣ የፋክስ ቁጥር፣ የኤሌክትሮኒክ እና ሌሎች የግንኙት አድራሻዎች፤
  - ✓ አዳዲስ ቅርንጫፎችን ወይም የሥራ ክፍሎችን መክፈትና መዝጋትን እንዲሁም የኢንተርኔት ወይም የማህበራዊ ሚዲያ አድራሻ መለወጥን ጨምሮ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በሚያከናውንበት ቦታ ወይም በሚያከናውንባቸው ቦታዎች፤
  - ✓ የተመዘገበው ሰው የንግድ ሥራ ባህሪ፣ እና ስሙ፣ ቋሚ አድራሻው ወይም የፓስፖርት አድራሻ፣ የተቋቋመበት መተዳደሪያ ደንብ ወይም ዋንኛ የስራ እንቅስቃሴው፤
  - ✓ ከባለስልጣኑ ጋር ግንኙነት የሚያርግበት የባንክ አድራሻ፤
  - ✓ ከባለስልጣኑ ጋር ግንኙነት የሚደርግበት የኤልክትሮኒክ አድራሻ እና በመመሪያ የሚደነገጉ ሌሎች ለውጦችን ማሳወቅ አለበት።

<u>የሙከራ ጥያቄ</u>

- ➢ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ አፈጻጸም የቅርንጫፍ ምዝገባ ማለት ምን ማለት ነው?
- ➢ የግዴታ ምዝገባ እና የፍቃደኝነት ምዝገባ ልዩነታቸውን አብራራ?

## 2.8. የተጨ ማሪ ዕሴት ታክስ መጣኔዎች

በኢትዮጵያ ሁለት አይነት የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መጣኔዎች ያሉ ሲሆን ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩ ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች እና ሌሎችም የተመረጡ ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርቡ አቅርቦቶች በዜሮ መጣኔ የሚስተናገዱ ይሆናል። ሌሎች እቃዎች እና አገልግሎቶች ግን ከታክሱ ነጻ ካልተደረጉ በስተቀር ወደ ሃገር ውስጥም ሲገቡ ሆነ ለሀገር ውስጥ ገበያ ሲቀርቡ 15 በመቶ ታክስ የሚከፈልባቸው ይሆናል።

### 2.8.1. ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚሆንበት አቅርቦት

- ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎች

➢ ከኢትዮጵያ ውጪ በሚገዝ አውሮፕላን፣ ተሽከርካሪ ወይም ባቡር ላይ የተጫኑ ከኢትዮጵያ ውጪ ለጥቅም ወይም ለፍጆታ የሚውሉ የጉዞ ዕቃዎች፤

➢ ለጥገና፣ ለዕድሳት፣ ለማሻሻያ ወይም ለማስተካከያ ተግባር በጉምሩክ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች፣

እነዚህ ዕቃዎች፡-

✓ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር በገቡ ዕቃዎች ላይ ሊገጠሙ፣ ከእነዚህ ዕቃዎች ጋር ሊያያዙ ወይም በማናቸውም መልክ የእነዚህ ዕቃዎች አንድ ክፍል የሚሆኑ እስከሆነ ድረስ ወይም

✓ ለጥገና፣ ለዕድሳት፣ ለማሻሻያ ወይም ለማስተካከያ ተግባር የዋሉ በመሆኑ ምክንያት ለሌላ አገልግሎት የማይውሉ ወይም ዋጋ የማይኖራቸው ከሆነ፤

➢ ዕቃዎች ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ወይም የሚገቡ ከሆነ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ሊደረግበት አይችልም።

➢ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች ወደ ሀገር የገቡት ከ 12 ወራት በላይ ለሆነ የቆይታ ጊዜ ከሆነ የዕቃው አቅርቦት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ሊደረግለት አይችልም።

➢ በአቅርቦቱ ላይ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደረገ የተመዘገበ ሰው በታክሱ ባለስልጣን ተቀባይነት ያላቸውን አቅርቦቱ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆንለት ለማድረግ ያስቻሉትን የሰነድ ማስረጃዎች መቀበል እና መያዝ አለበት።

- የተመዘገበ ሰው ለውጭ ገበያ ለሚያቀርብ ለሌላ የተመዘገበ ሰው (ላኪ) የሚያቀርባቸው እቃዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ለውጭ ገበያ የተላኩ እንደሆነ ይቆጠራል፦
  - ➢ የእቃውን አይነት እና አግባብነት እስካለው ድረስ የላኪውን መደበኛ አሰራር እንዲሁም ምክንያታዊ የሆነውን የጉዳዩን አፈጻጸም ከግምት ውስጥ በማስገባት ላኪው እነዚህን እቃዎች እንደተረከበ ወዲያውኑ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ከሆነ፤
  - ➢ ላኪው እነዚህን እቃዎች የተረከበው ለፍጆታ፣ ለመጠቀሚያ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ለገበያ ለማቅረብ ካልሆነ፤
  - ➢ የእቃዎቹ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ እቃዎቹን ለማጓጓዝ አስፈላጊ ካልሆነ ወይም የማጓጓዙ አካል ካልሆነ በስተቀር እቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደገና ለመሰራት፣ ለመለወጥ ወይም ተሻሽለው ለመሰራት የማይውሉ ከሆነ እና
  - ➢ ላኪው እቃዎቹ ለውጭ ገበያ የተላኩ መሆኑን የሚያስረዱ የታክስ ባለስልጣኑን የሚያሳምኑ ማስረጃዎችን መያዝ አለበት። ለነዚህ ከላይ ለተዘረዘሩት አፈጻጸም፡-
    - ✓ ላኪው እቃዎችን ለመላክ ያቀደ እና እቃዎቹን የሚልክ መሆን አለበት።
    - ✓ እቃዎችን ወደውጭ ለመላክ ላቀደ ላኪ እቃዎችን ለሚያቀርብ ሰው የሚፈጸም አቅርቦት ለውጭ ገበያ የተላከ እንደሆነ አይቆጠርም።
    - ✓ እንደገና መስራት፣ መለወጥ ወይም አሻሽሎ መስራት ከተፈጥሮዊ እድገት ውጪ ዝግጅትን፣እያያዝን ወይም ሌላ በእቃው ላይ አካላዊ ወይም ኬሚካላዊ ለውጥ ማስከተልን ይጨምራል። ሆኖም ቆጠራን፣ ማቀዝቀዝን፣ በመጋዘን ማከማቸትን፣ ለውጭ ገበያ በሚላክበት አኳኋን ማሸግን፣ መልሶ ማሸግን፣ የኤክስፖርት ምልክት ማድረግን፣ ለውጭ ገበያ በሚቀርብ አይነት በሳጥን ማሸግን፣መጫኑን ወይም ከአንዱ ወደ ሌላ ማስተላለፍን እና
    - ✓ የታክሱን ባለስልጣን በሚያሳምን አኳኋን እቃው ለውጭ ገበያ ለመቅረቡ በቂ ማስረጃ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በታክሱ ባለልጣን ተቀባይነት ባለው ቅርጽ ከእቃው ተቀባይ እንደ የኤክስፖርት ሰርተፊኬት ያለ ማስረጃ ሲቀርብ ነው።

ለዚህ አፈጻጸም “እቃ” የተፈጥሮ ሃብትን የሚጨምር ሲሆን፤ የአልኮል እና የትምባሆ ውጤቶችን አይጨምርም።

- ለውጭ ሀገር የሚቀርቡ አገልግሎቶች፡- ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሲሟሉ ለውጭ ሀገር የሚቀርቡ አገልግሎቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ይደረግባቸዋል።

- አገልግሎቱ የተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ ከሆነ፤
- ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ የተሰጠን የአገልግሎት አቅርቦት ሳይጨምር አገልግሎቱ የተሰጠው አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ ነዋሪ ለሆነ ሰው ከሆነ፦
    - ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ከሆነ፤
    - ✓ አገልግሎቱ ከተሰጠ በኋላ የሚንቀሳቀሰው ንብረት ከኢትዮጵያ ውጪ የተላከ ካልሆነ በስተቀር አገልግሎቱ የተሰጠው አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተገናኘ ከሆነ፤
    - ✓ አገልግሎቱ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ውስጥ ከማካሄድ መቀጠብን የሚመለከት ከሆነ፤
    - ✓ ሌላ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ማናቸውንም ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ማካሄዱን መቀበልን የሚመለከት ከሆነ፤
- የሚሰጡት አገልግሎቶች፦
    - ✓ የፈጠራ መብትን ከኢትዮጵያ ውጪ ለመጠቀም ማስመዝገብ፣ መከታተል፣ መስጠት፣ ማደስ፣ ማዘዋወር፣ መብት ማስተለለፍ፣ ፈቃድ ማውጣት ወይም ማስፈጸም እና እነዚህን አገልግሎቶች ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ተዛማጅ አገልግሎቶች፤ ወይም
    - ✓ ከኢትዮጵያ ውጪ የፈጠራ መብቶችን በሙሉ ወይም በከፊል ለመጠቀም ማናቸውም ሰው አንድን ነገር ከመከታተል ወይም ከማድረግ ለመቆጠብ የሚገባው ግዴታ፤
- አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ በቀጥታ የሚገናኘው ኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ ዕቃ ጋር ሲሆን፤
- በጊዜያዊነት ወደ ሀገር የገቡት ዕቃዎች ከ 6 (ከስድስት) ወራት በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የማይቆዩ እስከሆነ ድረስ አገልግሎቱ የተሰጠው በቀጥታ ከእነዚህ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ከሆነ፤
- አገልግሎቱ የተሰጠው በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው ከሆነ እና አገልግሎቱ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ አቅርቦቶች እና ከኢትዮጵያ ውጪ በሚጓዝ አውሮፕላን፣ ተሽከርካሪ ወይም ባቡር ላይ የተጫኑ ከኢትዮጵያ ውጪ ለጥቅም ወይም ለፍጆታ የሚውሉ የጉዞ ዕቃዎች ማመቻቸትን የሚመለከት ከሆነ፤
- አገልግሎቱ በአካል የተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጪ ከሆነ፤
- የትራንስፖርት ደጋፊ አገልግሎቶችን ሳይጨምር አገልግሎቱ የዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት ከሆነ፤ አገልግሎቱ ሰዎችን በኢትዮጵያ ውስጥ ካለ ቦታ ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ ወዳለ ሌላ

ቦታ በአውሮፕላኖች ማጓጓዝ ሲሆን እና ይህም ትራንስፖርት በአለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽን <<ዓለም አቀፍ ጉዞ>> በሚለው የተሸፈነ ከሆነ፤

- ➢ አገልግሎቱ የትራንስፖርት ደጋፊ አገልግሎቶችን ሳይጨምር የዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት ተፈጻሚነት ባለው የአገልግሎት አቅርቦት አካል ሆኖ የሚቀርበው በአንድ አቅራቢ እስከሆነ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ዕቃዎችን ማጓጓዝ ነው፡፡
- ➢ አገልግሎቱ ከኢትዮጵያ ውጭ ጥቅምላይ የሚውሉ አገልግሎቶች ተፈጻሚ ለሚደረግባቸው አገልግሎቶች የሚውል የመድን አገልግሎት፣ የመድን አገልግሎትን ማመቻቸት ወይም መንገደኞችን እና ዕቃዎችን የማጓጓዝ አገልግሎት ከሆነ፤
- ➢ አገልግሎቱ ረዳት የትራንስፖርት አገልግሎት ሆኖ ከኢትዮጵያ ውጭ ላሉ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የንግድ አድራሻ ለሌላቸው ሰዎች የሚቀርብ ከሆነ።
- ➢ ለሚከተሉት አገልግሎቶች አቅርቦት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ አይደረግም፡-
  - ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወን የቱሪዝም አገልግሎት ሲሆን፤
  - ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወን የቱሪዝም አገልግሎት እንቅስቃሴን ማመቻቸትን የሚመለከቱ ሲሆን እና
  - ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝን የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚመለከቱ ሲሆን፤

<<በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወን የቱሪዝም አገልግሎት እንቅስቃሴን ማመቻቸት>> የሚባለው በኢትዮጵያ ውስጥ በጥቅል የሚሰጡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የቱሪዝም ውጤቶች ወይም አገልግሎቶችን እና ከኢትዮጵያ ውጪ ላለ ላልተመዘገበ ሰው መሸጥ ማለት ነው፡፡

- አለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት

ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ አፈጻጸም የሚከተሉት የአለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ተደርገው ይቆጠራሉ፦

- ➢ አውሮፕላኑ በኪራይ ወይም በቻርተር ውሉ ዘመን በተላከበት የውጭ አገር ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ በኪራይ ወይም በቻርተር ውል መሰረት የቀረበ አውሮፕላን፤
- ➢ ለውጭ አገር አውሮፕላን የተሰጠ የጥገና፣ የእድሳት፣ የጽዳት ወይም የጠቅላላ እድሳት አገልግሎት እና እነዚህን ድርጊቶች በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው በማመቻቸት ረገድ አገልግትን ማቅረብ፤

- ➢ በወኪል ወይም በሌላ ሰው አማካኝነት በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው በቀጥታ የሚሰጥ የሚከተሉትን የሚጨምር አገልግሎት፤
  - ✓ ወደውጭ አገር ለሚሄድ አውሮፕላን ኢትዮጵያ ውስጥ ባለበት ጊዜ የሚሰጥ የማስተናገድ፤ ወደመቆሚያ ወይም ከመቆሚያ በመውጣት ሂደት ማገዝ፤ የሳልቬጅ ወይም የመጎተት አገልግሎት ወይም
  - ✓ ለውጭ አገር አውሮፕላን ከስራ እንቅስቃሴ ወይም አስተዳደር ጋር በታያያዘ የሚሰጥ አገልግሎት፤ እና እነዚህን ድርቶች በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው በማመቻቸት ረገድ አገልግትን ማቅረብ፤
- ➢ በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ ያልተመዘገበ ሰው የሚከተሉትን በማመቻቸት ረገድ የሚሰጥ አገልግሎት፦
  - ✓ ተጓዳኝ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠትን ጨምሮ እቃዎችን ማጓጓዝ፤
  - ✓ ነዋሪ ያልሆነ ያልተመዘገበ ሰው ለሚሰጠው የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት የጥገና፣ የእድሳት፣ የጽዳት ወይም የጠቅላላ እድሳት አገልግሎት አቅርቦት እና
  - ✓ በጉዞ ወኪል አማካኝነት የአለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን ማመቻቸት፣

- የጉዞ ወኪል ጥቅል የቱሪዝም አገልግሎትን የሚያካትት የጉዞ ጥቅል እና አለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት ለደንበኞቹ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉት ሲሟሉ ተፈጻሚ ይሆናሉ፦
  - ➢ የአለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት እና የጉዞ ወኪሉ አለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎትን በማመቻቸት ረገድ የሚሰጠው አገልግሎት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግባቸው ከሆነ እና
  - ➢ ጥቅል የቱሪዝም አቅርቦቱ እና የጉዞ ወኪሉ ጥቅል የቱሪዝም አገልግሎት በማመቻቸት ረገድ የሚሰጠው አገልግሎት 15 በመቶ የማስከፈያ መጣኔ መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልባቸው ከሆነ፤

  "ወደውጭ አገር የሚጓዝ አውሮፕላን" ማለት መንገደኞችን ወይም እቃ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በኢትዮጵያ ከሚገኝ የአውሮፕላን ማረፊያ በውጭ አገር ወደሚገኝ አውሮፕላን ማረፊያ ወይም በውጭ አገር በሚገኙ አውሮፕላን ማረፊያ ከአንዱ ወደሌላው የሚያጓጉዝ አውሮፕላን ነው።

- የፋይናንስ አገልግሎትን ወደውጭ ስለመላክ የሚከተሉት ለወጭ የሚቀርቡ የፋይናንስ አገልግሎቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ይደረግላቸዋል፦
  - ➢ ወደውጭ ከሚላኩ እቃዎች ጋር በተያያዘ የሚሰጡ የፋይናንስ አገልግሎቶች፤

- ➢ ለውጭ ገበያ የሚላኩ እቃዎችን ወጪ ለመሸፈን ነዋሪ ላልሆነ እና ላልተመዘገበ ሰው ከሚሰጥ ብድር ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ተጓዳኝ የፋይናንስ አገልግሎቶች እና
- ➢ በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ የዚህ አይነቱ አቅርቦት ኤክስፖርት የማይባል ካልሆነ በስተቀር አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጪ ለነበረ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ባንክ የተሰጠ የባንክ አገልግሎት፤ ወደውጭ የሚላኩ እቃዎች እና ተዛማጅ አገለግሎቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆንላቸው ማድረግ የሚቻለው የታክሱ ባለስልጣን በሚያዘው መሰረት ላኪው በወጪ እቃዎች ወደብ እቃዎቹን እና የጽሁፍ ማስረጃዎችን ለይቶ ሲያቀርብ ይሆናል።

- ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ በስራ ላይ እንዳለ ድርጅት ሰለማስተላለፍ
  - ➢ በስራ ላይ ያለ ድርጅት ወይም የዚሁ ድርጅት ከፊል ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በማስተላለፍ ሂደት የእቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦት ተፈጽሟል የሚባለው የማስተላለፉ ተግባር በተከናወነብት ጊዜ ነው።
  - ➢ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ወይም የዚሁ እንቅስቃሴ ከፊል በስራ ላይ ያለ ነው የሚባለው የማስተላለፉ ተግባር ከተፈጸመ በኋላ የስራ እንቅስቃሴው ያለማቋረጥ የሚከናወን ወይም ሊከናወን የሚችል ሲሆን ነው። ስራውን ያቋረጠ ወይም ወደፊት ሊሰራ ይችላል የሚባል ድርጅት በስራ ላይ ያለ ነው ሊባል አይችልም።
  - ➢ የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ወይም የዚሁ የስራ እንቅስቃሴ ከፊል ትርፋማ ባይሆንም ወይም የተላለፈው ለኪሳራ አጣሪ፣ ለተቀባይ፣ በኪሳራ ሂደት ለተሰየመ ባለአደራ ወይም የተመዘገበው ሰው ኪሳራ በመጣራት ላይ ባለበት ሂደት ለተሰየመ ሌላ ሰው ቢሆንም በስራ ላይ እንዳለ ይቆጠራል።
  - ➢ በተመዘገበ ሰው በስራ ላይ እንዳለ ድርጅት የተላለፈ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ወይም የዚሁ የስራ እንቅስቃሴ ከፊል ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግለት ነባር ታክስ የሚከፈልበት የስራ ዕንቅስቃሴን በማስተላለፍ ተግባር እንደገና በማደራጀት ሂደትን የመሳሰለ ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ የህግ ሰውነት ወይም ቅርጽ የመለወጥ ሲሆን ነው።
  - ➢ የተላለፈለት ሰው እና አስተላላፊው ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ከሆኑ ወይም የተላለፈለት ሰው ታክስ በሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ላይ አስቀድሞ ጥቅም የነበረው ከሆነ የታሱ ባለስልጣን ግብይቱ በትክክለኛ የገበያ ዋጋ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል። የተላለፈው

ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ራሱን ችሎ የሚሰራ እስከሆነ ድረስ የተላለፈለት ሰው ይህንን ገቢ የሚያመነጭ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ራሱ ማካሄዱ አስፈላጊ አይሆንም።

- ➢ የንግድ የግብርና ስራ አቅርቦት በመካሄድ ላይ ያለ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠረው የቁም እንስሳት፣ የግብርና መሳሪያዎች፣ መገልገያዎች እና ሌሎች የግብርና ንግድ ስራውን ለመስራት የሚያስፈልጉ ሃብቶች የአቅርቦቱ አካል ከሆኑ ነው። የንግድ የግብርና ስራ ብቻውን መተላለፍ በመካሄድ ላይ ያለ የንግድ ስራ እንቅስቃሴ እንደተላለፈ አይቆጠርም።
- ➢ አስተላላፊው የማስተላለፉ ተግባር በተከናወነ በ45 (በአርባ አምስት) ቀን ጊዜ ውስጥ ወይም የታክሱ ባለስልጣን በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ማስታወቂያ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ይህም ጊዜ አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ ይሆናል። አስተላላፊው ማስታወቂያ ካቀረበ በኋላ የማስተላለፉ ተግባር በመካሄ ላይ ላለ ድርጅት የተፈቀደው ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የማይደረግለት ሆኖ ቢገኝ የሚከተሉት ተፈጻሚ ይሆናሉ፦
  - ✓ የማስተለለፉ ተግባር የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈልበታል።
  - ✓ የተላለፈበት ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስን የማይጨምር ሆኖ ይወሰዳል።
  - ✓ የተላለፈለት ሰው ለአቅርቦቱ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊጠይቅ ይችላል።

- ለታክሱ ባለስልጣን የሚቀርበው ማስታወቂያ የሚከተሉትን ጭምር የሚይዝ መሆን አለበት፦
  - ➢ የተለለፉትን ንብረቶች የተሟላ ዝርዝር፤
  - ➢ የማስተላለፉ ተግባር በተፈጸመበት ጊዜ እያንዳንዱ የተላለፈው ንብረት የነበረው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፤
  - ➢ አስተላላፊው ሲያካሂድ የነበረው የንግድ ስራ ባህሪ እና የተላለፈለት ሰው በተላለፈበት ንብረት የሚያካሂደው የንግድ ስራ፤
  - ➢ አስተላላፊው በተላለፉት ንብረቶች የንግድ ስራውን ሲያካሂድ የቆየበትን ጊዜ እና
  - ➢ የታክሱ ባለስልጣን ከአስተላላፊው ወይም ከተላለፈለት ሰው ወይም ከሁለቱም የሚፈልጋቸው ሌሎች መረጃዎች።
- የተላለፈለት ሰው የማስተላለፉ ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ያልተመዘገበ ከሆነ የማስተላለፉ ተግባር ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግለት የተላለፈለት ሰው የማስተላለፉ ተግባር በተፈጸመበት ጊዜ በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ አቅርቦት ተከናውኗል የሚባልበትን ጊዜ መሰረት አድርጎ ሲመዘገብ ነው።

- አስተላላፊው በመካሄድ ላይ የሚገኘውን የንግድ ስራ እንቅስቃሴ በማስተላለፉ ምክንያት ምዝገባውን የሰረዘ እንደሆነ፤ አስተላላፊው ለተላለፈለት ሰው ያላስተላለፈውን ንብረት በሚመለከት ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች ተደርገው ይወሰዳሉ። በዚህም መሰረት የሚቀርበው ማመልከቻ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ፦
  - ➢ አስተላላፊው በእጁ የሚገኙትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች ለተላለፈለት ሰው ያስረክባል። የተላለፈለት ሰው እነዚህን ሰነዶች ለታክስ ህጉ 5 (አምስት) አመት እንዲሁም ለንግድ ህጉ ለ 10 (አስር) አመት ያህል ጊዜ ይዞ ያቆያል።
  - ➢ አስተላላፊው የንግድ ስራው ባለቤት ሆኖ በቆየበት ጊዜ ለነበረ የተጨማሪ እሴት ታክስ እዳ ሁለቱም ወገኖች ኃላፊ ይሆናሉ።
  - ➢ አስተላላፊው እና የተላለፈለት ሰው የተመዘገቡ ካልሆነ ሁለቱም ጊዜውን ጠብቀው በማመልከቻው ላይ በመፈረም ካላቀረቡ በስተቀር የተላለፈው በመካሄድ ላይ ያለ ድርጅት ቢሆንም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ አይደረግም።
- ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግባቸው የሀገር ውስጥ አቅርቦቶች የሚከተሉት የሀገር ውስጥ አቅርቦቶች ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ይደረግላቸዋል፡-

(I) ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተሟልተው ሲገኙ አንድ የተመዘገበ ሰው በመንቀሳቀስ ላይ ያለውን ድርጅቱን ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል በማስተላለፍ ሂደት የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦት ሲያከናውን፡-

- ➢ የንግድ ሥራው የተላለፈለት ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በቀጣይነት ማከናወን እንዲችል የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የተላለፈው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም የተላለፈው ከፊል የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አካል ሆነው የተላለፉ ከሆነ፤
- ➢ አስተላላፊው የማስተላለፉ ተግባር እስከተከናወነበት ቀን ድረስ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ ሲያከናውን የነበረ ከሆነ፤
- ➢ የተላለፈለት ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ ከታክስ ነጻ የሆነ አቅርቦቶችን ለማከናወን የሚጠቀምበት ካልሆነ ወይም ዕቃዎቹ እና አገልግሎቶቹ ለግል ጥቅም የማይውሉ ከሆነ፤
- ➢ የተላለፈለት ሰው እና አስተላላፊው የማስተላለፉ ተግባር በተከናወነበት ዕለት ወይም ከዚህ ጊዜ በፊት የማስተላለፉ ተግባር፤ በመንቀሳቀስ ላይ ያለን ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴን በሙሉ ወይም በከፊል የማስተላለፍ ተግባር ሆኖ እንደሚቆጠር በጽሑፍ የተስማሙ ከሆነ እና

➢ አስተላላፊው የማስተላለፉ ተግባር በተከናወነ በ45 (በአርባ አምስት) ቀን ጊዜ ውስጥ ወይም የታክሱ ባለስልጣን በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ድርጅት የማስተላለፉ ተግባር ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል ማስተላለፍ ተደርጐ ሊወሰድ እንደሚገባ ከገለጸ፣

➢ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ፤

➢ ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ እንቅስቃሴ በከፊል በማስተላለፍ ሂደት የተከናወነ የእቃ ወይም አገልግሎት አቅርቦት ላይ ከላይ የሮማን ቁጥር (I) ተፈጻሚ የሚሆነው የተላለፈው የንግድ እንቅስቃሴ ራሱን ችሎ ሊሰራ የሚችል ከሆነ ነው፡፡

➢ በዕቃ ወይም አገልግሎት አቅርቦት ከላይ የሮማን ቁጥር (I) ተፈጻሚ ከሆነ እና አቅርቦቱ ከተከናወነ በኋላ ተቀባዩ የተላለፈለትን ዕቃ እና አገልግሎት ከታክስ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶችን ለማቅረብ ያዋለ ወይም የተላለፉለትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለግል ጥቅም ያዋለ እንደሆነ፣ ከላይ የሮማን ቁጥር

(I) ተፈጻሚ የሆነባቸውን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በተመለከተ ተቀባዩ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንዳከናወነ በመቁጠር፡-

✓ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት በተከናወነበት ጊዜ ከታክሱ ነጻ ለሆነ አቅርቦት ወይም የተላለፈው ዕቃ ወይም አገልግሎት ለግል ጥቅም እንደዋለ ይቆጠራል፡፡

✓ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ዋጋ የሚባለው ግብይት በተከናወነበት ጊዜ የዕቃዎቹ ወይም የአገልግሎቶቹ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው፡፡

- አቅርቦትን ወደውጭ ከመላክ ጋር የተያያዙ ትርጓሚዎች

➢ <<የትራንስፖርት ደጋፊ አገልግሎት>> ማለት ጭነት መጫንና ማውረድ፣ ጭነትን የመመርመር አገልግሎት፣ የጉምሩክ ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ ኮንቴይነሮችን የማስተናገድ አገልግሎት እና ለተጓጓዙ ዕቃዎች ወይም ለሚጓጓዙ ዕቃዎች የመጋዘን መስጠት ነው፡፡

➢ <<መላኪያ ሀገር>> ማለት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የመላኪያ ሀገር ተብሎ እንዳይቆጠር ከሚወሰነው ሀገር ወይም ግዛት በስተቀር ከኢትዮጵያ ውጪ ያለ ማናቸውም ሀገር ወይም ግዛት ነው።

➢ <<ዕቃዎችን ወደውጭ መላክ>> ማለት ዕቃዎችን፡-

✓ የሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች በተሟሉበት ሁኔታ ማቅረብ ነው፡-

✓ በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አቅራቢው ዕቃዎችን ወደውጭ ሀገር ለመላክ ሲያቀርብ፤ እና

- ✓ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው የሰነድ ማስረጃ ዕቃዎቹ መላኪያ ሀገር የደረሱ መሆኑ ሲረጋገጥ።
- ➢ ዕቃዎቹ አስቀድሞ ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ያልቀረቡ ቢሆንም የታክሱ ባለስልጣን እቃዎቹ ከኢትዮጵያ ውጪ የተላኩ መሆኑን ሲያምንበት፤
- ➢ ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያከናውን እና በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የስራ ቦታ የሌለው ሰው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የታዘዘን ዕቃ በኢትዮጵያ ውስጥ ማቅረብ ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን ዕቃዎች ሳይጨምር በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሰረት አቅርቦቱ በተከናወነበት ጊዜ እቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ የሌሉ ወይም አቅራቢው ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እቃዎቹን ወደ ኢትዮጵያ የማያስገባ ከሆነ።

- <<ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት>> ማለት በአየር፣ በየብስ ወይም በባቡር ዕቃዎችን ወይም መንገደኞችን፡-
  - ➢ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ክፊል የጉዞው መስመር የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ማቋረጥን የሚጨምር ሆኖ ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ አንድ ቦታ ከኢትዮጵያ ውጪ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ፤
  - ➢ ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚገኝ አንድ ቦታ የመጨረሻ መዳረሻው ወደሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደሚገኝ ቦታ ወይም
  - ➢ የጉዞው መነሻ ከሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ አንድ ቦታ ከኢትዮጵያ ውጪ ወደሆነ ቦታ ማጓጓዝ ነው።
    - ✓ <<የጉዞ ዕቃዎች>> ማለት፡- በጉምሩክ አዋጅ ምዕራፍ ስድስት የተመለከቱት ዕቃዎች ናቸው።
    - ✓ <<በጊዜያዊነት ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች>> ማለት፡- በጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 71 መሠረት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች ናቸው።
    - ✓ <<የቱሪዝም ውጤቶች ወይም አገልግሎቶች>>፡- የሚለው ሐረግ መኝታን፣ የትራንስፖርትን፣ ጉዞን ወይም ሌሎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎችን ይጨምራል።

## 2.8.2. ከታክስ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶች

- የሚከተሉት አቅርቦቶች ከታክሱ ነጻ ተደርገዋል።
  - የመኖሪያቤት
    - ➢ በመኖሪያ ቤትነት ለሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ፤

➢ ከሁለት ወራት በታች ለሆነ ጊዜ የተከራየን ሳይጨምር የመኖሪያ ቤት ኪራይ፤

➢ በመኖሪያ ቤቱ ለመገልገል አስፈላጊ የሆኑትን የመኖሪያ ቤቱን ቅጥር ግቢ እና እንደ መኪና ማቆሚያ፣ መኪና ማሽከርከሪያ፣ የአትክልት ቦታ፣ የተስተካከለ መሬት እና መተላለፊያ ያሉትን መገልገያዎች የሚጨምር ሲሆን ከመኖሪያ ቤቱ ጋር የተያያዘ የእርሻ ቦታን አይጨምርም።

➢ ከታክሱ ነጻ የሆኑት የመኖሪያ ቤቶች አካል የሆኑትን የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች መሸጥ፤

➢ ከታክሱ ነጻ የሆኑት የመኖሪያ ቤቶች አካል የሆኑትን የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ማከራየት።

<<የመኖሪያ ቤት>> ማለት ሆቴልን ወይም የእረፍት ጊዜ መኖሪያን ሳይጨምር ለግል መኖሪያነት በማገልገል ላይ የሚገኝ ወይም የሚያገለግል የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው።

<<ሽያጭ>> ማለት ከመኖሪያ ሕንጻዎች ጋር በተያያዘ የረጅም ጊዜ የሊዝ ውል መስጠትን ወይም ማስተላለፍን ያጠቃልላል።

- የፋይናንስ ተቋም፡-

ፈቃድ በተሰጠው ባንክ ወይም የፋይንናስ ተቋም ወይም በሌላ ማናቸውም ሰው የሚሰጥ የፋይናንስ አገልግሎት አቅርቦት፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ግልጽ ወይም በግልጽ ያልተመለከተ ቢሆንም አቅርቦቱ ከታክስ ነጻ ነው። “ለፋይናንስ አገልግሎት” ለተሰጠው ትርጉም አፈጻጸም “ቼክ” የሚለው ቃል የፖስታ ቤት ትእዛዝን፣ የገንዘብ ክፍያ ትእዛዝን፣ የመንገደኞች ቼክ ወይም ማናቸውንም ገንዘብ ገቢ ወይም ወጪ የማድረግ ትእዛዝ ወይም ፈቃድ (በጽሁፍ፣ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወይም በሌላ ዘዴ) ለፋይናንስ ተቋም መስጠትን ይጨምራል።

ሚኒስቴሩ ነጻ የተደረጉ ተጨማሪ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ዝርዝር የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል። ሚኒስቴሩ አዳዲስ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በማከል ወይም በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱትን የፋይናንስ አገልግሎቶች ባህሪ በመቀየር ዝርዝሩን ሊያሻሽል ይችላል። ማናቸውም በዝርዝሩ ላይ የሚደረግ ለውጥ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከወጣበት ቀን በኋላ በሚኖሩ ግብይቶች ላይ ነው።

➢ <<የፋይናንስ አገልግሎት>> ማለት፡-

✓ በአበዳሪው የሚከናወንን ብድር፣ ክሬዲት ወይም የክሬዲት ዋስትናን ማስተዳደርን ጨምሮ ብድር መስጠት፣ መደራደር፣ ወይም በብድር፣ በክሬዲት፣ በክሬዲት ዋስትና ወይም ለገንዘብ በሚሰጥ ዋስትና መነገድ፤

✓ ዕዳ መሰብሰብን እና ተሰብሳቢ ሒሣብን መሸጥን ሳይጨምር ገንዘብ፣ ተቀማጭ ሒሣብን፣ ቁጠባን እና ሌሎች ተመሳሳይ ሂሳቦችን፣ ክፍያዎችን፣ የገንዘብ ማስተላለፍ ተግባራትን (የፋይናንስ

ቴክኖሎጂ አገልግሎትን ሳይጨምር) ዕዳን፣ ቼክን ወይም የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችን የሚመለከቱ ተግባራት፤

- ✓ የፋይናንስ ዴሪቬቲቭ ሀብትን የመግዛትና የመሸጥ ውሎች፤ የፋይናንስ ሀብትን ወደፊት በሚውል ቀን ለመግዛት ወይም ለመሸጥ የሚደረግ ስምምነት፤ የፋይናንስ ሰነዶችን ለመግዛት የሚኖር ምርጫን የመግዛትና የመሸጥ ውሎች እና ተመሳሳይ ተግባራትን፤
- ✓ የአደራ አገልግሎት ሳይጨምር በአክሲዩን፣ ድርሻ፣ ቦንድ እና ሌሎች የግዴታ ምስክር ወረቀቶች መገበያየት እና ከእነዚህ ጋር የተያያዘ ማናቸውም ምርጫ ወይም ዋስትና፤
- ✓ የኢንቨስትመንት ፈንድን ማስተዳደር፤
- ✓ የረfhም ጊዜ የመድን ውል መስጠት ወይም የባለቤትነት መብት ማስተላለፍ ወይም ለዚህ ዓይነቱ ውል የጠለፋ መድን መስጠት ወይም አነስተኛ የመድህን ውል መስጠት፤
- ✓ የጡረታ ፈንድ፣ የፕሮቪደንት ፈንድን ወይም ሌላ ተመሳሳይ የጥቅም ፈንድ፤ የመድን ጡረታ ፈንድ፤ የጡረታ ሂሳብን ለማስጠበቅ የሚቋቋም ፈንድ ማቋቋም ወይም የባለቤትነት መብትን ማስተላለፍ፤
- ✓ ለዕቃው በሚሰጠው ብድር ላይ የተለየ ክፍያ የሚጠየቅ እና ክፍያው ለዕቃው ተጠቃሚ የተገለጸ እስከሆነ ድረስ በኪራይ ግfh ስምምነት ወይም በፋይናንስ ሊዝ መሠረት የሚከናወን አቅርቦት፤
- ✓ ብር ወይም የውጭ ምንዛሪ የመግዛት ወይም የመሸጥ ውል፤
- ✓ ከላይ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ማመቻቸት፤ ወይም
- ✓ በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ መሠረት የእስልምና ባንክ አገልግሎት መስጠት።

I. ከፋይናንስ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የተሰጡ ቢሆንም ባይሆንም የሚከተሉት የፋይናንስ አገልግሎት አይባሉም፦

- ➢ በፋይናንስ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ለተሰማራ ሰው ወይም በፋይናንስ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ለተሰማራ ሰው ደንበኛ የተሰጡ የህግ፣ሂሳብ እና የሂሳብ መረጃን የማጠቃለል ወይም የሰነድ አያያዝ፣ የፋይናንስ ስጋትን የመገምገም፣ የሰነድ ማረጋገጫ ወይም የታክስ ወኪል (የታክስ አማካሪነትን ጨምሮ) አገልግሎቶች፤
- ➢ ጥሬ ገንዘብ፣ ሰንድ ወይም ሌላ ነገር በአደራ ማስቀመጥ፤
- ➢ መረጃን የማቀነባበር እና የደመወዝ ክፍያ አገልግሎት፤
- ➢ እዳ የመሰብሰብ ወይም ተሰብሳቢ ሂሳብን መሸጥ፤

➢ የጡረታ መዋጮ ፈንድን ማስተዳደርን የመሳሰሉ የአስተዳደር ስራዎች፤

➢ የባለአደራ፣ የፋይናንስ ምክር እና የሃብት አስተዳደር እቅድ የማውጣት አገልግሎቶች፤

➢ ከፋይናንስ ሰነዶች ውጪ ያሉ ንብረቶችን የማከራየት፣ ፈቃድ የመስጠት እና ተመሳሳይ የማመቻቸት ስራዎች፤

- “ሂሳብ እና የሂሳብ መረጃን የማጠቃለል ስራ” የሚለው ሀረግ ሂሳብ በማወራረድ ሂደት በፋይናንስ ተቋማት የተከናወኑ የገንዘብ እንቅስቃሴዎችን የማስታረቅ ስርአትን፤ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን በደንበኞች ሂሳብ ላይ መመዝገብን፤ የደንበኞችን ሂሳብ ማስተዳደርን እና በሮማን ቁጥር አንድ ስር የተዘረዘሩት አገልግሎቶች ጋር ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶችን መስጠትን ይጨምራል።
- ተሰብሳቢ ሂሳብን በመግዛት ብድር መስጠትን ጨምሮ እዳን መግዛት ብቻውን የፋይናንስ አገልግሎት እንደሆነ ይቆጠራል። ይሁን እንጂ ተሰብሳቢ ሂሳብን ከመግዛት ጋር የተያያዘውን የሽያጭ ሂሳብ አያያዝ አገልግሎት እና ተሰብሳቢ ሂሳብን ከመግዛት ጋር የተያያዙ ሌሎች አገልግሎቶችን ጨምሮ እዳውን ከማስመለስ፤ ከክስ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች እና ከባለእዳዎች ላይ የሚፈለገውን ገንዘብ ለማስመለስ የሚከናወኑ የአስተዳደር ተግባራት የፋይናንስ አገልግሎት አይባሉም።
- የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እና ከታክሱ ነጻ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ከሆነ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የተመለከተውን የማከፋፈያ ዘዴ መሰረት በማድረግ የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክሶችን እንዲያከፋፍል የታክሱ ባለስልጣን ሊፈቅድ ይችላል። የግብአት ታክስን ለማከፋፈል የትኛውም ዘዴ በጥቅም ላይ የዋለ ቢሆንም፤የፋይናንስ አገልግሎትን የሚያቀርብ የተመዘገበ ሰው የተከተለው ተገቢውን ዘዴ መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን መያዝ አለበት። የታክሱ ባለስልጣን የፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢዎች የያንዳንዱን የአቅርቦት ዘርፍ ስታትስቲካዊ መረጃ እንዲያቀርቡ ሊያዝ ይችላል። ከታክሱ ነጻ በሆነው የኢንሹራንስ ዋስትና ፖሊሲ ሽፋን የሚካተቱ ከታክሱ ነጻ ከሆነው የኢንሹራንስ ፖሊሲ ጋር ያልተያያዙ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች እነዚህ አገልግሎቶች ለብቻቸው ቢሰጡ ሊከፈል በሚገባው ታክስ ልክ ታክሱን እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። የታክሱ ባለስልጣን የኢንሹራንሱ ፖሊሲ አካል ያልሆነው አገልግሎት ከዋናው የኢንሹራንስ ፖሊሲ ጋር የተያያዘ ተጨማሪ አገልግሎት መሆን ያለመሆኑን የመወሰን ሙሉ ስልጣን አለው።
- “ለፋይናንስ አገልግሎት” በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈን የኢንሹራንስ ፖሊሲ አቅርቦት ከታክሱ ነጻ የሆነ አቅርቦት ሊሆን የሚችለው ፖሊሲው የተሰጠው በኢንሹራንስ ስራ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 746/2004 (እንደተሻሻለ) ፈቃድ በተሰጠው ሰው ሲሆን ነው።

- ለደንበኞቻቸው የኢንሹራንስ ሽፋን ለማስገኘት የሚሰሩ የኢንሹራንስ ደላሎች ወይም ወኪሎች የሚያገኙት ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ እንደ ፋይናንስ አገልግሎት የማይቆጠር በመሆኑ ለኢንሹራንስ በተሰጠው የታክስ ነጻ መብት አይሸፈንም። የኢንሹራንስ ፖሊሲ ለንብረት ጥራት ወይም አፈጻጸም ዋስትና የሚገባ የኢንሹራንስ ሽፋንን አይጨምርም።
- ለፋይናንስ አገልግሎት የተሰጠው ከታክሱ ነጻ የመሆን መብት የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ድርጅቶች እና የክፍያ ስርዓት ኦፕሬተሮች የሚያከናውኑትን አቅርቦት አይጨምርም።

- የዋስትና ሰነዶች እና የፋይናንስ አገልግሎቶች
  - ➢ “ለፋይናንስ አገልግሎት” በተሰጠው ትርጉም የተመለከተው የዋስትና ሰነዶችን የመገበያየት ተግባር ከታክሱ ነጻ የሆነ ግብይት ነው። ይህም ማለት የአደራ አገልግሎት ሳይጨምር በአክሲዮን፣ ድርሻ፣ ቦንድ እና ሌሎች የግዴታ ምስክር ወረቀቶች መገበያየት እና ከእነዚህ ጋር የተያያዘ ማናቸውም ምርጫ ወይም ዋስትና ሲሆን የዋስትና ሰነዶችን የመገበያየት ተግባር ከአቅርቦቱ ተግባር ጋር የተያያዘ የማስታወቂያ፤ የህትመት ወጪዎችን፣ የሂሳብ አያያዝ፣ የህግ እና የምክር አገልግሎቶችን አይጨምርም።
  - ➢ “የፋይናንስ አገልግሎት” ዋንኛ ስራቸው የአክሲዮን ባለቤቶችን፣ የአባላትን ወይም የሌሎች ሰዎችን ገንዘብ ኢንቬስት የማድረግ ተግባር ለሆነ የንግድ ስራዎች የሚሰጥ የስራ አመራር ወይም የአስተዳደር ተግባርን አይጨምርም።
- የእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት፡- የታክሱ ባለስልጣን ለለእስልምና የፋይናንስ ስርአት የተደነገጉትን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ ለማስፈጸም የሚከተሉትን ተግባራዊ ያደርጋል።
  - ➢ የፋይናንሱ ስራ የሚያካትታቸውን የተለያዩ አቅርቦቶች ለይቶ ማወቅ፤
  - ➢ በእስልምና የፋይናንስ ስራ ውስጥ የማይካተቱ አቅርቦቶችን የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም መወሰን እና
  - ➢ በእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት የሚቀርቡ አገልግሎቶች አንድ አይነት የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም እንዲኖራቸው ማድረግ።
  - ➢ ለእስልምና የባንክ አገልግሎት አቅርቦቶች የሚኖረው የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻደም እስልምና ነክ ካልሆኑ የባንክ አገልግሎት አቅርቦቶች ጋር እኩል ካልሆነ፤ የተጨማሪ እሴት ታክሱ አፈጻጸም

የአቅርቦቱን አላማ፣ ባህሪያት እና ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ይወሰናል። ሚኒስቴሩ የአንድን የእስልምና የባንክ አገልግሎት አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

  - ➢ "የእስልምና የፋይናንስ አገልግሎት" ማለት የሸሪአ ህግ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ የፋይናንስ አቅርቦት አገልግሎት ውል ነው።

- የሐይማኖት ነክ አገልግሎት
  - ➢ በሃይማኖት ተቋም የሚሰጡ የሃይማኖቱ ስርአት አንድ ክፍል የሆኑ አቅርቦቶች የሃይማኖት ነክ አገልግሎት ይባላሉ። የሃይማኖት ተቋም የሚያቀርባቸው እና ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር ተወዳዳሪ የሆኑ አቅርቦቶች ወይም የሃይማኖቱ ስርአት አካል ያልሆኑ አቅርቦቶች የሃይማኖት ነክ አገልግሎት አይባሉም።
  - ➢ የሃይማኖቱ ተቋም የሚያቀርባቸው የዚህ አይነት አቅርቦቶች ዋጋ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ከተቀመጠው ገንዘብ በላይ ከሆነ የሃይማኖት ተቋሙ ለምዝገባ ማመልከቻ የማቅረብ ግዴታ አለበት።
  - ➢ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት የሚሰጥ እርዳታ (እንደ ሙዳየ ምጽዋት ያለ) ወይም አገልግሎት፤ በእርዳታው እና የእርዳታ ሰጪው በሚያገኘው ጥቅም መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ከሌለ በስተቀር የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አይሆንም።
  - ➢ ከዚህም በተጨማሪ ቅዱሳን መጻህፍትን ማቅረብን ጨምሮ በእምነት ተቋማት የሚሰጡ ከእምነቱ ወይም ከኃይማኖቱ ሥርዓት ጋር በቀጥታ የተያያዙ አገልግሎቶች ነጻ ተደርገዋል።
  - ➢ የሃይማኖት ተቋም ከንግድ ድርጅት የሚቀበለው ገንዘብ የሰጪው ስም በመጽሄት ወይም በፕሮግራም እንዲጠቀስ የሚያስችል ቢሆንም ለአቅርቦት የተከፈለ ዋጋ እንደሆነ አይቆጠርም። ሆኖም የሃይማኖት ተቋሙ በመጽሄት ወይም በፕሮግራም ውስጥ ቦታ ለመሸጥ ክፍያ የተቀበለ ከሆነ ክፍያው ለአቅርቦት የተፈጸመ ክፍያ እንደሆነ ስለሚቆጠር ለሃይማኖት ነክ አገልግሎት በተሰጠው ከታክስ ነጻ የመሆን መብት አይሸፈንም።
  - ➢ በልማት ኮሚሽን ወይም ተመሳሳይ ተቋም ወይም በቅርንጫፍ ወይም የስራ ክፍል አማካኝነት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የሚያከናውን የሃይማኖት ተቋም፤ አንድ ወይ ከአንድ በላይ ያለው ኮሚሽን፤ ቅርንጫፍ ወይም የስራ ክፍል የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተናጠል ምዝገባ እንዲያደርግ እንዲፈቀድለት ሊያመለክት ይችላል።

- የህክምና ተቋም

➢ “የታወቀ የህክምና ተቋም፡- ፈቃድ የተሰጠውን የህክምና ባለሙያ፣ ሆስፒታልን፣ የማዋለጃ ክሊኒክን፣ የአረጋውያን እንክብካቤ መስጫን ወይም የህክምና ክሊኒክን ይጨምራል።

✓ የሕክምና መገልገያ፣ የሕክምና መሣሪያ እና የወባ አጎበር አቅርቦት፤

✓ የሕክምና አገልግሎት አቅርቦት፤

✓ በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች አቅርቦት፤

➢ “የታወቀ የህክምና አገልግሎት” ማለት በሽታን ወይም ሌላ ህመም የመመርመር፣ የማከም፣ የመከላከል፣ ወይም የማገገም እና የአእምሮ ደህንነትን የመንከባከብ አገልግሎት ነው። የህክምና አገልግሎት በክፍያ የተሰጠ ከሆነ ክፋዩ ተመላላሽ ታካሚው ተኝቶ የሚታከመው ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን ቢሆንም ባይሆንም የታወቀ የህክምና አገልግሎት ይሆናል። ምግብ እና መኝታ ማቅረብ፤ የአረጋውያን እንክብካቤ እና የግል የህክምና እንክብካቤ እና በእለት ተእለት እንቅስቃሴ የሚደረግ ድጋፍን ጨምሮ የታወቀ የህክምና ባለሙያ ለተመላላሽ ወይም ተኝቶ ለሚታከም ታካሚ በታወቀ የህክምና ተቋም ውስጥ የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት የታወቀ የህክምና አገልግሎት ይባላል።

➢ “የታወቀ የህክምና ባለሙያ” የሚባው አግባብ ባለው የፌዴራል ወይም የክልል መንግስት ተቋም በጤና ባለሙያነት ወይም በህክምና ባለሙያነት እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው። ይህም የጤና ዶክተሮችን፣ አካሚዎችን፣ የጤና ኦፊሰሮችን፣ ፊዝዮቴራፒስቶችን እና ሌሎች የጤና አገልግሎት ሰጪዎችን ይጨምራል።

➢ የሚከተሉት የታወቀ የህክምና አገልግሎት የሚሰጣቸው አገልግሎት እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ፡-

✓ የተለየ ክፍያ የማይጠየቅባቸው በታወቀ የህክምና አገልግሎት የሚቀርቡ መድሃኒቶች፤

✓ የላቦራቶሪ፣ የኤክስሬይ ወይም ሌላ የምርመራ አገልግሎት፤

✓ ከላይ በርዕሱ የተዘረዘሩትን የህክምና አገልግሎቶች በመስጠት ሂደት የሚቀርቡ የህክምና መገልገያዎች፤

✓ የህክምና መሳሪያዎች ወይም አቅርቦቶችን ጨምሮ በኦፕራሲዮን ክፍል፣ በምርመራ ክፍሎች እና በማደንዘዣ ክፍሎች የሚሰጡ አገልግሎቶች፤

✓ የታወቀ የህክምና አገልግሎት በመስጠት ሂደት የሚከናወኑ የራዲዮ ቴራፒ፣ የፊዚዮቴራፒ እና የአእምሮ እድገት ህክምና አገልግሎቶች፤

✓ ታካሚ ላልሆኑ ሰዎች የሚሰጠውን የሬስቶራንት ወይም የካፊቴሪያ አገልግሎት ሳይጨምር ለተመላላሽ እና ተኝተው ለሚታከሙ ታካሚዎች የሚሰጥ የመኝታ እና የምግብ አገልግሎት፤

- ✓ ከታወቀ የህክምና ተቋም ጋር በተያያዘ አገልግሎት የሚሰጡ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እና ቴክኒሽያኖችን ጨምሮ በታወቀ የህክምና ተቋም ሰራተኞች የሚሰጡ አገልግሎቶች፤
- ✓ አጠቃላይ የጥርስ ሕክምናን ወይም ጥርስ ማስጌጥን ሳይጨምር ከበሽታ፣ ከጭንቀት ተሞክሮ ወይም ከተፈጥሮ መዛባት ጋር በተያያዘ የሚሰጥ የጥርስ ህክምና፣ የጥርስ ደጋፊ አካላት እና የጥርስ የውስጥ ክፍል ህክምና፤
- ✓ ስነ-አእምሮአዊ ትንተና።

➢ “የህክምና መገልገያ” ማለት የታወቀ የህክምና አገልግሎት በመስጠት ሂደት በታወቀ የህክምና ተቋም ውስጥ ለተመላላሽ ወይም ተኝቶ ታካሚው አገልግሎት የሚሰጥበት ወይም በሃኪም ትእዛዝ ለታካሚው የሚሰጥ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፦

- ✓ የአተነፋፈስ ወይም የልብ ምት መከታተያ፣ የኩላሊት ማጠቢያ መስሪያ ወይም የአካል ጉዳተኞች መመገቢያ ቁሳቁስ፤
- ✓ የታወቀ የህክምና አገልግሎት አካል ሆኖ በህክምና ወም በኦፕራሲዮን ሂደት የሚሰጥ ሰው ሰራሽ የሰውነት አካል ወይም የአካል ድጋፍ መሳሪያ እና
- ✓ ለታወቀ የህክምና ተቋም የሚቀርብ የህክምና ወይም የኦፕራሲዮን መሳሪያ ወይም ለተመላላሽ ወይም ተኝቶ ለሚታከም ሰው የሚሸጥ ወይም በኪራይ የሚቀርብ ተመሳሳይ መሳሪያ፤

- <<የትምህርት ፕሮግራም>>፡- በሚከተሉት የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም ነው፡-

➢ አግባብ ባለው ክልል የትምህርት ቢሮ ፈቃድ የተሰጠው ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤

➢ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 152/2011 መሠረት በትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና የተሰጠው ዩኒቨርሲቲ፣ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣ ኮሌጅ ወይም ኢንስቲትዩት፣ ሆኖም የትምህርት ፕሮግራሙ ዲግሪ ወይም ተመሳሳይ የብቃት ማስረጃ የሚያስገኝ ከሆነ፤

➢ በቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ሥልጠና አዋጅ ቁጥር 954/2010 መሠረት ዕውቅና የተሰጠው የሥልጠና ተቋም፣ ሆኖም የትምህርት ፕሮግራሙ በአዋጁ መሠረት ዕውቅና የተሰጠው የቴክኒክ ወይም የሙያ ሥልጠና ፕሮግራም ከሆነ፤

➢ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተቋም።

➢ ከታች የተዘረዘሩር የትምህርት ፕሮግራም አካል ሆነው ይቆጠራሉ

- ✓ በታወቀ የትምህርት ተቋም ለተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርት፤

- ✓ በታወቀ የትምህርት ተቋም የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም አካል ሆነው በአይነት የሚቀርቡ የምግብ እና ሌሎች ተዛማጅ እቃና አገልግሎቶች፤
- ✓ በታወቀ የትምህርት ተቋም የተሰጥ እስከሆነ ድረስ ስለፈተና የሚደረግ ገለጻ ወይም የፈተና አስተዳደር፤
- ✓ ከታወቀ የትምህርት ኮርስ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ትምህርት ወይም ማስጠናት እና
- ✓ ከትምህርት ቤቱ ጋር በተደረገ ውል በሚሰራ የግል ድርጅት ሳይሆን በትምህርት ቤቱ በራሱ የሚሰጥ ተማሪዎችን ከቅደመ- አንደኛ ደረጃ፣ ከአንደኛ ደረጃ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ ቤታቸው እንዲሁም ከቤታቸው ወደ ትምህርት ቤቱ በማመላለስ የሚሰጥ የትምህርት ቤት የትራንስፖርት አገልግሎት፤

➢ የሚከተሉት ክፍያዎች ለትምህርት ፕሮግራም አቅርቦት የተፈጸሙ ክፍያዎች ሆነው ይቆጠራሉ፦

- ✓ ከትምህርቱ፣ ከአገልግሎት መስጫዎች እና ከካሪኩለም ጋር ለተያያዙ ተግባራት የሚፈጸም ክፍያ፤
- ✓ የታወቀው የትምህርት ተቋም ከትምህርቱ ጋር በተያያዘ ለሚያቀርባቸው መገልገያዎች የሚያስከፍላቸው አስገዳጅ የሆኑ ክፍያዎች፤
- ✓ የተማሪዎች ምክር ቤት ክፍያ፤ የሥፖርት ቡድን ክፍያ እና ሌሎች ከትምህርት ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ አስገዳጅ ክፍያዎች፤
- ✓ ከትምህርት ፕሮግራም ጋር በቀጥታ በተያያዘ ሁኔታ የታወቀው የትምህርት ተቋም ለሚሰጣቸው የተማሪ ሪፖርት፣ የመጽሃፍት ቤት አገልግሎት፣ የመታወቂያ ካርድ፣ የመረጃ አያያዝ እና ሌሎች የአስተዳደር አገልግሎቶች የሚፈጸም ክፍያ፤
- ✓ ለትምህርት አገልግሎት መሣሪያዎች የሚከፈል ክፍያ ከስርዓተ ትምህርቱ ጋር የተያያዙ ዕቃዎችን ለምሳሌ (የሙዚቃ መሳሪያዎችን መከራየት) በትምህርቱ አቅራቢ ማከራየት እና በቀጥታ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር የተያያዙ እና በዋናነት መዝናኛ ያልሆኑ የመስክ ጉዞዎች
- ✓ በታወቀ የትምህርት ተቋም የሚቀርቡ የተማሪ ማረፊያዎች (ሆስቴሎችን ጨምሮ) እና
- ✓ ለህንጻዎች፣ የግቢዎች፣ የቤተ-መጻሕፍት እና የኮምፒውተር ሳይንስ እና ሌሎች የላቦራቶሪዎችን የመገልገያ ክፍያዎችን ያካትታል።

➢ ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚከተሉት ከቅደመ አንደኛ ደረጃ፤ የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ ክፍያዎች የትምህርት ፕሮግራም ክፍያዎች ሆነው ይወሰዳሉ፦

✓ የልዩ ትምህርትን ጨምሮ ለመሰረታዊ ትምህርቶች የሚፈጸም ክፍያ፤

✓ ትምህርት ቤት ከሚያካሂደው የትምህርት ፕሮግራም በተያያዘ ለቅድመ አንደኛ ወይም ለድህረ ትምህርት ፕሮግራሞች የሚፈጸም ክፍያ

✓ በትምህርት ቤቱ የሙዚቃ ወይም የስፖርት መሳሪያዎች ለመጠቀም የሚፈጸም ክፍያ

✓ የትምህርቱ ፕሮግራም አካል ለሆነ በተማሪዎች ወይም በመምህራን ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚፈጸም ክፍያ እና

✓ የትምህርት ቤት ቲያትር፣ ዳንስ፣ ጉዞ ወይም ሌላ በዋንኛነት ለተማሪዎች ለተዘጋጀ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ የሚፈጸም ክፍያ፤

➢ በዩኒቨርሲቲ ወይም በቴክኒክ ኮሌጅ የሚሰጥ ከታክሱ ነጻ የሆነ የትምህርት አገልግሎት ተማሪው ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ ለማግኘት የሚማር ባይሆንም በርቀት ወይም በርቀት ግንኙነት የሚሰጡ ለዲግሪ ወይም ለዲፕሎማ የሚያበቁ ኮርሶችም ከታክሱ ነጻ ናቸው።

➢ የሚከተሉት ለአዋቂ ትምህርት፣ ለሙያ ትምህርት እና ለቴክኒክ ትምህርት ኮርሶች እና ለአካል ጉዳተኞች እና ለአእምሮ ጉዳተኞች ስልጠና የሚከፈሉ ክፍያዎች ሆነው ይወሰዳሉ፦

✓ ለዲግሪ ወይም ለዲፕሎማ የሚያበቁ የአዋቂ የትምህርት ኮርሶች ወይም የኮርሱ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎችን ከቅጥር ጋር የተያያዙ ክህሎቶች ለማዳበር ለሚያስፈልጉ ኮርሶች የሚከፈል ክፍያ፤

✓ የተማሪዎችን የሙያ ክህሎት ለማዳበር ለሚያግዙ በሙያ ትምህርት ቤቶች ለሚሰጡ የሙያ ኮርሶች የሚከፈል ክፍያ፤

✓ አግባብ ባለው የመንግስት እውቅና ሰጪ ተቋም የሙያ ወይም የንግድ ስራ እውቅና ወይም ስያሜ ለማግኘት ወይም ይህ ማረጋገጫ እንዲቀጥል ለማድረግ ወይም የሙያ ማሻሻያ ለማድረግ ለሚሰጡ ኮርሶች የሚፈጸም ክፍያ፤ እና

✓ የእውቅና ወይም የስያሜ ኮርስ ወይም ፕሮግራም የምስክር ወረቀት ለማግኘት ወይም ፈተና ለመውሰድ የሚፈጸም ክፍያ።

➢ አንድ ኮርስ ከቅጥር ጋር የተያያዘን ክህሎት ለማሳደግ የሚያስችል ነው የሚባለው የኮርሱ አላማ ተማሪዎች የሚያገኙትን ክህሎት ለይቶ የሚይሳይ እና ተማሪዎች ያገኙትን ክህሎት ለመዝናኛ፣ ለግል

ፍላጎት ማርኪያ፣ ለኪነጥበብ ወይም ባህላዊ አላማዎች ሳይሆን ለቅጥር፣ ለንግድ ስራ ወይም ለሙያ ስራ የሚጠቀሙበት ከሆነ ነው፡፡

➢ የሚከተሉት ኮርሶች አቅርቦት የትምህርት ኮርስ አቅርቦት ነው አይባልም፦

✓ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ የሚያስገኝ ካልሆነ በስተቀር የስፖርት፣ የጨዋታ፣ የቪዲዮ ቀረጻ ወይም የፎቶግራፍ ወይም ሌላ የግል ፍላጎትን የሚመለከቱ ወይም የመዝናኛ ኮርሶች፤

✓ ለግል መገልገያ ወይም መጠቀሚያ የሚውል የሰእል፣ የምግብ ዝግጅት፣ የመኪና መንዳት፣ የጸጉር ስራ እና ሌሎች የውበት መጠበቂያ ኮርሶች እና

✓ የትምህርት ካሪኩለም አካል ያልሆነ የሙዚቃ ትምህርት፡፡

➢ የሚከተሉት የትምህርት ፕሮግራም አቅርቦት አካል ሆነው አይወሰዱም፦

✓ የትምህርት ተቋም ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውጪ ላለ ቡድን የሚሰጠው የኪራይ አገልግሎት፡

✓ የትምህርት ቤቱን የስፖርት ውድድር ለሚከታተል አጠቃላይ ማህበረሰብ የመግቢያ ቲኬት መሸጥ፤

✓ በትምህርት ቤቱ ይዞታ ውስጥ በሳንቲም የሚሰሩ መሳሪያዎችን ከሚያስቀምጡ የሚገኝ ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ እና

✓ የትምህርት ቤቱን አርማ የያዙ እቃዎችን እና የመሳስሉትን ከትምህርት ጋር ግንኙነት የሌላቸውን እቃዎች በመሸጥ የሚገኝ ገቢ፤ ከዚሁ ጋር ተያዞ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙ የእምነት ተቋማት ሰራተኞች ተማሪ ሆነው ይወሰዳሉ፡፡

➢ አቅራቢው የትምህርት ፕሮግራም ለሚከታተሉ ተማሪዎች የሚያቀርባቸውን ዋጋቸው ለፕሮግራሙ የሚከፈለው ዋጋ ውስጥ የተካተተ የመማሪያ መጻህፍት፣ ቁሳቁሶች ወይም መሣሪያዎችን ጨምሮ የትምህርት ፕሮግራሞች አቅርቦት ከታክሱ ነጻ ናቸው፡፡

➢ ፈቃድ በተሰጠው አገልግሎት ሰጪ የሚከናወን የህጻናት ማቆያ አገልግሎት፤

• የብዙሐን ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት፤

➢ <<የብዙሐን ትራንስፖርት አገልግሎት>> ማለት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር ለመንገደኞች እና ለግል መገልገያ ዕቃዎቻቸው እንዲሁም ለጭነት ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በመንገድ፣ በባቡር ወይም በጀልባ በክፍያ የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፦

✓ ባለሦስት እግር ተሽከርካሪን ሳይጨምር አሽከርካሪውን ጨምሮ ከስምንት ሰው በታች የመጫን አቅም ያለው ተሽከርካሪን በመጠቀም የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት፤

- ✓ ከነሹፌሩ ቢሆንም ባይሆንም የሚሰጥ የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት፤ እና
- ✓ ቱሪስቶችን ማጓጓዝ።

➢ ለትርፍ ባልተቋቋሙ ድርጅቶች የሚቀርቡ በእርዳታ የሚሰጡ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፤

<<በእርዳታ የሚሰጡ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች>> ማለት ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችን በሚመለከት ለእነዚህ ድርጅቶች በስጦታ የሚቀርቡ ወይም በስጦታ በተገኘ የሚገዙ እና ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም የሚውሉ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች።

➢ ሰብአዊ እርዳታ፡- የአደጋ መካከል የብሄራዊ የስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የተፈጥሮ አደጋ፣ የኢንዱስትሪ አደጋ ወይም ሌላ የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ በማጋጠሙ ምክንያት ባደረገው ጥሪ መስረት ወደ አገር ለሚገቡ እና አገር ውስጥ ለሚቀርቡ እቃዎች ተፈጻሚ ይሆናል።

➢ ለግብርና አገልግሎት ብቻ የሚውል የምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የጸረ - ተባይ፣ የጸረ - አረም፣ የአፈርን አሲዳማነት ለመከላከል የሚውል ካልሲየም ሃይድሮክሳይድ (ውህድ ኖራ) ወይም የፈንገስ መከላከያ ኬሚካሎች፤

➢ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ በተደነገገው መሠረት ኢንቨስተሮች ወደ ሀገር የሚያስገቡት ወይም ከሀገር ውስጥ የሚገዙት ዕቃ፤

➢ የ 200 ኪሎ ዋት ሰዓት ወረሃዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታ መጠን እና የታሸገ ወሃን ሳይጨምር የ 15 ሜትር ኩብ ውሃ ወርሃዊ ፍጆታ መጠን

➢ የአካል ጉዳተኞችን ወይም የዐዕምሮ ጉዳታኞችን ቀጥረው በሚሰሩበት ድርጅት የዕቃ እና የአገልግሎት አቅርቦት ለሚገኙ ሰዎች 60 በመቶና ከዚያ በላይ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው የሚያቀርባቸው ማናቸውም አቅርቦቶች፤ የ60% ተፈላጊ መስፈርት ከአጠቃላይ የድርጅቱ ሰራተኞች መካከል የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኞችን ብዛት በመቶኛ በመውሰድ የሚሰላ ሲሆን፤ ይህ ቁጥር ሁልጊዜም የተሟላ መሆን አለበት። ለዚህ አላማ “ሰራተኛ” ቋሚ፤ የከፊል ጊዜ እና ጊዜያዊ ሰራተኛን ይጨምራል።

➢ ሚኒስቴሩ በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከታክስ ነጻ እንዲሆኑ የሚፈቅዳቸው እቃዎች፤

➢ አምቡላንስ እና የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች እና መሣሪያዎች አቅርቦት።

- <<የእረፍት ጊዜ ወይም የሆቴል መስተንግዶ>> ማለት፡-

➢ በሆቴል፣ በሞቴል፣ በኢን፣ በመኝታ ቤቶች፣ በእንግዳ ማረፊያ፣ በሆስቴል ወይም በተመሳሳይ ሌላ ተቋም በተለምዶ በሚሰጥ መስተንግዶ ለበርካታ ሰዎች በቀን፣ በሣምንት፣ በወር ወይም በሌላ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት በሚፈጸም ክፍያ አገልግሎት መስጠት፤ ወይም ከዚህ ከተመለከተው የመስተንግዶ አቅርቦት ውጪ በግለሰቦች ለአጭር ጊዜ ለሚደረግ ቆይታ የሚሰጥ መስተንግዶ ነው፡፡

- <<የረ fh ም ጊዜ የመድን ስራ>> የሚለው ሐረግ በመድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 746/2004 (እንደተሻሻለ) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡
- <<የሕክምና አገልግሎት>> ማለት በምግብ፣ መድኃኒትና የጤና እንክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1112/2011መሠረት ፈቃድ በተሰጠው የጤና ባለሙያ ወይም የሕክምና ባለሙያ በታወቀ የህክምና ተቋም ውስጥ የሚሰጥ የህክምና ሙያ አገልግሎት ነው፡፡
- <<አነስተኛ መድህን ውል>> የሚለው ሐረግ በመድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 746/2004 (እንደተሻሻለ) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡
- <<ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት>> ማለት ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር የማይገናኝ የንግድ ስራ ገቢን ሳይጨምር ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የሚያገኘው ገቢ ከታክሱ ነጻ ነው፡፡
- <<በሐኪም የሚታዘዝ **መድኃኒት>>** ማለት በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011መሠረት በሐኪም ትዕዛዝ ብቻ የሚወሰድ መድኃኒት ነው፡፡
- ከታክስ ነጻ የሆኑ ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች

➢ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች ከታክሱ ነጻ ተደርገዋል፡-

✓ በቪዬና የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ኮንቬንሽን ሚሲዮኖች፣ ዲፕሎማቶች ወይም የኩንሱላር ጽ/ቤቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ እስከሆኑ ድረስ እነዚህ ሚሲዮኖች፣ ዲፕሎማቶች ወይም የኩንሱላር ጽ/ቤቶች ወደ ሀገር የሚያስገቡዋቸው ዕቃዎች፤

✓ በዓለም አቀፍ ስምምነት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የተደረጉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወደ ሀገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፤

✓ በፋይናንስ፣ በቴክኒክ፣ በሰብዓዊ ዕርዳታ ወይም በአስተዳደር ድጋፍ የዓለም አቀፍ ስምምነት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ እስከተደረገ ድረስ የውጭ ሀገር መንግሥት ወደ ሀገር የሚያስገባቸው ዕቃዎች፤

✓ በጉምሩክ ደንብ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ እስከተደረገ ድረስ መንገደኛው ይዞት የሚመጣ የግል መገልገያ ዕቃ፤

- ✓ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ከሚወስነው እስካልበለጠ ድረስ ተመላሾች ወደ ሀገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፤
- ✓ ወደ ሀገር የሚገባ ለግብርና ሥራ ብቻ የሚውል ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የተባይ ማጥፊያ፣ የአረም ማጥፊያ ወይም የፈንገስ ማጥፊያ፤
- ✓ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወደ ሀገር የሚገባ ወርቅ፡-ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እንዲውል ወደአገር የሚገባ ወርቅ የወርቁ የጥራት ደረጃ ወይም የሚቀርበበት ቅርጽ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ወደአገር ገብቶ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ መሰረት ከታክሱ ነጻ ይሆናል።
- ✓ የውሃ ማከሚያ፤ አጐበር፣ የሕክምና መገልገያ፣ እና የሕክምና መሣሪያ፤
- ✓ ወደ ሀገር የሚገባ በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት፤
- ✓ ኢንቨስተሮች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር የሚያስገቡት ዕቃ፤
- ✓ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር እንዲገቡ የተፈቀዱ የካፒታል ዕቃዎች፤
- ✓ በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ከጉምሩክ ቀረጥና ከማናቸውም ታክስ ነጻ የሆኑ ያልተመደቡ ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች፤ እና
- ✓ አምቡላንስ እና የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ወደ ሀገር ማስገባት።

➢ አንድ አቅርቦት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግለት እንዲሁም ከታክሱ ነጻ የተደረገ ከሆነ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ አፈጻጸም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ብቻ ተፈጻሚ እንዲሆንለት ይደረጋል።

- ከውጭ ወደአገር ውስጥ ሲገቡ እና አገር ውስጥ ግብይት ሲፈጸምባቸው ከታክሱ ነጻ የተደረጉ ተጨማሪ አቅርቦቶች፡-

➢ የዕንስሳት መድሃት

➢ የመድሃኒት መርጫ

➢ ለህክምና መገልገያ መሳሪያዎች እና በሐኪም ለሚታዘዙ መድሃቶች ማምረቻ የሚውሉ ግብዓቶች

➢ የጸረ-ወባ ክትባት፣ኮንዶም እና ለህክምና ተቋማት የሚቀርብ ኦክሲጅን

➢ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖ፣የኮንስላር ጽ/ቤቶች፣የዲፕሎማቲክ አቋም ያላቸው ዓለምአቀፍ ድርጅቶች እና ዲፕሎማቶች በአገር ውስጥ የሚፈጽሟቸው ግዢዎች

- የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ተቋሞች፣የህዝብ ደህንነት ተቋሞች፣የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ወደ አገር የሚያስገቧቸው እና በአገር ውስጥ የሚገዟቸው ለመከላከያ እና ለህዝብ ደህንነት የሚያገለግሉ ዕቃዎች እና መሣሪያዎች፣ለእነዚሁ አገልግሎት የሚውሉ ክፍሎች እና አክሰሰሪዎች
- እህል እና ጥራጥሬ
  - ✓ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ ዳጉሳ ፣ አጃ፣
  - ✓ አተር፤ ባቄላ፤ ምስር፤ አኩሪ አተር፤ ሽምብራ፤ ግብጦ፤ ጓያ እና የመሳሰሉት ጥራጥሬዎች፤ እና የእነዚህ ዱቄት፡፡
- የበሰሉ ወይም የተዘጋጁ ምግች/መጠጦች
  - ✓ እንጀራ
  - ✓ ዳቦ እና ወተት
- ማናቸውም የስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን በመንግስት ተቋማት ለሚሰጡ ፈቃዶች እና አገልግሎቶች የሚፈጸም ክፍያ
- ለግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት የሚውሉ እና በጉምሩክ ታሪፍ መጽሐፍ ከማናቸውምቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ ከተፈቀዱ ዕቃዎች ውስጥ “የተመደቡ” ትብለው የተዘረዘሩት የግብርና ዕቃዎች
- ያልተዘጋጁ ሸንኩርት፣ድንች እና አትክልቶች
- ምግብ ለማበልጸግ የሚውሉ ቫይታሚኖች (ቫይታሚን ኤ፣ ቢ 1፣ ቢ 2፣ በ 3፣ በ 6፣ በ 9፣ በ 12፣ ዲ፣ ፖታሽየም፣ አዮዴት እና ዚንክ ኦክሳይድ)።
- የገንዘብ ሚኒስቴር ነጻ የተደረጉ ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን ዝርዝር ሊያሻሽል ይችላል። <u>የሙከራ ጥያቄ</u>
- ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ የሚያቀርባቸው አቅርቦቶች በዜሮ መጣኔ የሚስተናገዱበትን መንገድ አብራራ?

# ክፍል ሦስት

## የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አቅርቦቶች

ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ነጻ የተደረጉ እና ታክሱ እንዳይመለከታቸው በታክስ ህጉ ከተገለጹት በስተቀር ከውጭ የሚገቡ እና ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርቡ ማናቸውም ዕቃዎች እና አገልግሎቶች የተጨማ ዕሴት ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች ይሆናሉ ከታች እያንዳንዳቸውን አቅርቦቶች እና የታክስ አከፋፈል ሂደታቸውን በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን።

## 3.1. ቀይጥ አቅርቦቶች

- አገልግሎትን ከማቅረብ ጋር በተያያዘ የሚከናወን የዕቃ አቅርቦት የአገልግሎት አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል።
- **ለምሳሌ፡-** የጋራ fh ስራ የሚሰራ ሰው ዋና ተግባሩ እቃ መሸጥ ሳይሆን አገልግሎት መስጠት ነው፤ ነገር ግን በዚሁ አጋጣሚ ለተበላሸው መኪና ተለዋጭ ዕቃ ሊቀይር ይችላል፡፡ ይህንን የዕቃ አቅርቦት ልንል አንችልም። ለተበላሸው ዕቃ የቀየረው መለዋወጫ የአገልግሎት አቅርቦት ተደርጎ ነው መወሰድ ያለበት።
- ከዕቃ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት የዕቃ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል።
- **ለምሳሌ፡-** አንድ ድርጅት ዋና ስራው ሊፍት ማቅረብ ቢሆን እና ሊፍቱን በመግጠም ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆን የሚያደርገውን ስራ ቢሰራ ሁለቱንም አንድ አቅራቢ እስካከናወናቸው ድረስ አቅርቦቱ የዕቃ አቅርቦት ተደርጎ ይወሰዳል። ምክንያቱም ዋና ስራው ሊፍት ማቅረብ እስከሆነ ድረስ።
- ከውጭ የሚገቡ የዕቃ አቅርቦቶች ዋጋ ውስጥ የአገልግሎት ዋጋ አብረው የተካተቱ ከሆነ የአገልግሎቱ አቅርቦት የዕቃው አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል።

➢ አንድ አቅርቦት የዕቃ አቅርቦት እና የአገልግሎት አቅርቦት ከሆነ፣ የታክሱ ባለስልጣን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ አቅርቦቱ የዕቃ አቅርቦት ወይም የአገልግሎት አቅርቦት ተደርጐ የሚወሰድበትን ሁኔታ **በመመሪያ** ይወስናል፡፡

➢ አቅርቦቱ፡-

✓ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማስከፈያ መጣኔ ተፈጻሚ የሚደረግበት ከሆነ፣

✓ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግለት ከሆነ እና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ በሚሆንበት ጊዜ አንድ ግብይት የማይቀር የሌላ ግብይት አካል ሆኖ፤ የማይቀረው ግብይት የሌላኛው ግብይት አካል ካልሆነ በስተቀር እያንዳንዱ የአቅርቦቱ ክፍል ራሱን የቻለ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል፡፡

➢ በዱቤ ግ fh ወይም በፋይናንስ ሊዝ ውል ለሚቀርብ ዕቃ ራሱን የቻለ ክፍያ ሆኖ የተካተተ እና ለአቅርቦቱ ተጠቃሚ የተገለጸ የወለድ ክፍያን የሚጨምር ሲሆን፣ የዚህ ዓይነቱ አቅርቦት የዕቃ አቅርቦት እና የፋይናንስ አገልግሎትን የያዘ ሁለት አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል፡፡

## 3.2. የአደራ ሽያጭ እና በውክልና ስልጣን ደረጃ ስለማስተላለፍ

- የእቃው ባለቤት (ሻጭ) እቃውን በአቅርቦት ወይም በተመላሽ (የአደራ ሽያጭ) ለሌላ ሰው መስጠቱ ግብይት እንደተፈጸመ አያስቆጥርም፡፡
- ከዚህ ጋር ተያይዞ የእቃ አቅርቦት ግብይት ተፈጽሟል የሚባለው ባለቤቱ የእቃውን ባለቤትነት ወደ ገዢው ሲያስተላልፍ ይሆናል፡፡
- በውክልና ስልጣን ደረጃ እቃ ለአንድ ሰው ሲተላለፍ ግብይት እንደተፈጸመ አይቆጠርም፡፡ ሚኒስቴሩ ለዚህ አፈፃፀም የሚያግዝ **መመሪያ** ያወጣል፡፡

## 3.3. በወኪሎች ወይም ለወኪሎች የተፈጸመ አቅርቦት

- ማናቸውም ወኪል ወካዩን በመወከል የሚያከናውነው የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦት በወካዩ የተከናወነ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይቆጠራል፡፡
- ወኪሉም የታክስ እንደራሴ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ወኪል ለሆነ ሰው የሚቀርብ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለወካዩ የተደረገ አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
- ነገር ግን ወኪሉ ለወካዩ የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 3.4. ከቦንድድ የማምረቻ ፋብሪካ መጋዘን እቃ ወጪ ስለማድረግ

- በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት መሰረት ዕቃ ከቦንድድ የማምረቻ ፋብሪካ መጋዘን ወጪ ሲደረግ ወይም የእቃ አቅርቦት ሲፈጸም በኢትዮጵያ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የእነዚህ እቃዎች አቅርቦት እንደተፈጸመ ይቆጠራል።
- እነዚህ እቃዎች ለአገር ውስጥ ገበያ የዋሉ ከሆነ አቅርቦቱ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ስለሆነ 15 በመቶ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ይከፈልበታል።
- አቅርቦቱ ተፈጽሟል የሚባለው እቃዎቹ ለአገር ውስጥ ገበያ ሲቀርቡ ሲሆን፤ የአቅርቦቱ ዋጋ ሽያጩ በተከናወነበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይሆናል።
- ነገር ግን ዕቃዎቹ ለውጭ ገበያ የተላኩ ከሆነ አቅርቦቱ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ይደረግለታል። ወደ ውጭ የተላኩት ዕቃች ጋር በተያያዘ አቅርቦቱ ተፈጽሟል የሚባለው እቃው ወደ ውጭ አገር ሲላክ ነው።

## 3.5. የሰራተኞች አገልግሎት

- ➢ የተመዘገበው ሰው ሠራተኞችን ቀጥሮ የሚያሰራ ከሆነ እና ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ለሠራተኞች የሚሰጥ ጥቅማ ጥቅም አንድ ክፍል በማድረግ የሚያቀርብ ከሆነ፣ አቅርቦቱ ክፍያን በመቀበል በትክክለኛ የገበያ ዋጋ እንደተፈጸመ ይቆጠራል። አሠሪው ለሠራተኞቹ ለሚያከናውነው አቅርቦት እንዲውል በፈጸመው ተቀናሽ የሚሆን ግዢ ላይ የታክስ ተቀናሽ ሊያገኝ የማይችል ከሆነ አቅርቦቱን ለሠራተኞቹ ያለክፍያ እንደፈጸመ ይቆጠራል።
- ➢ ሰራተኛ በቅጥር ውል መሰረት ለአሰሪው የሚሰጠው አገልግሎት አቅርቦት እንደሆነ አይቆጠርም።
- ➢ አሰሪው ለሰራተኛው።
  - ✓ በሰራተኛው ስም ለአቅራቢ ክፍያ የሚፈጽም ከሆነ፤ ወይም
  - ✓ ሰራተኛው ያወጣውን ወጪ የሚተካ ከሆነ፤ እነዚህም ክፍያዎች በጥቅማ ጥቅም መልክ ለሰራተኛ የሚሰጥ እቃ እና የአገልግሎትን ወጪ ለመሸፈን የሚውሉ ከሆነ፤ ለሰራተኛ የሚሰጥ እቃ እና አገልግሎት ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የተፈጸመ ባለመሆኑ አሰሪው በዚህ አይነቱ ወጪ ላይ የታክስ ተቀናሽ ሊያገኝ አይችልም።
- ➢ አሰሪው ለሰራተኛው በቅናሽ ወይም በነጻ የሚያቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ታክስ ይከፈልበታል።

## 3.6. ያገለገሉ እቃዎች

➢ <<ያገለገለ ዕቃ>> ማለት ከማይንቀሳቀስ ንብረት እና ከቁም እንስሳት በስተቀር ባልተመዘገበ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል ጥቅም ላይ ይውል የነበረ ዕቃ ነው፡፡

➢ <<ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ>> ማለት በሚገዛቸው ጊዜ በነበሩበት ሁኔታ ላይ ያሉ ያገለገሉ ዕቃዎችን ባሉበት ሁኔታ በመሸጥ እና ወይም በመለወጥ ሥራ ላይ የተሰማራ የተመዘገበ ሰው ነው።

- ካገለገሉ ዕቃዎች ጋር ተያይዞ ታክሱ ተፈጻሚ የሚሆነው ከታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡-

➢ ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ ያገለገሉ ዕቃዎችን ካልተመዘገበ ሰው በሚገዛበት ጊዜ፣

➢ ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ ያገለገሉትን ዕቃዎች ወደ ሀገር ያስገባ ካልሆነ፣

➢ ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ ያገለገሉ እቃዎችን የገዛው ከታክስ ነጻ በሆነ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ በሚደረግበት ግብይት ካልሆነ፣ እና

➢ ያገለገሉት ዕቃዎች አቅራቢ፡-

✓ ያገለገሉትን እቃዎች በሚከፈልበት አቅርቦት በሽያጭ ወይም በለውጥ ያቀረበ ከሆነ እና

✓ ያገለገሉትን ዕቃዎች በገዛበት ጊዜ በነበሩበት ሁኔታ መልሶ የሚሸጥ ከሆነ። እነዚህ

ሁኔታዎች በተሟሉ ጊዜ ያገለገሉ ዕቃዎች አቅራቢ፡-

➢ ያገለገሉትን ዕቃዎች የግብዓት ተቀናሽ በሚፈቀድለት ግfከ እንደገዛቸው፣

➢ ያገለገሉትን ዕቃዎች በገዛበት ጊዜ ላገለገሉት ዕቃዎች ከከፈለው ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ የታክስ ክፍልፋይ የግብዓት ታክስ እንደከፈለ ተቆጥሮ፤ ያገለገሉ ዕቃዎችን አቅርቦት ባከናወነበት የሒሣብ ጊዜ በግብዓት ላይ ለከፈለው ታክስ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ይፈቀድለታል።

➢ ማናቸውም አቅራቢ ላልተመዘገበ ሰው ላከናወነው አቅርቦት በከፊል ክፍያ መልክ የተቀበለው ያገለገሉ ዕቃዎችን "ዕቃን በዕቃ መገበያየት" በሚሆንበት ጊዜ ዕቃን በዕቃ በመገበያየት በተከናወነው አቅርቦት የተሸጡ ያገለገሉ ዕቃዎችን ዋጋ ለመወሰን ጥቅም ላይ የዋለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ አቅራቢው እነዚህን ዕቃዎች ለመግዛት ያወጣውን ወጪ ለመወሰን ጥቅም ላይ ከዋለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ጋር እኩል እንደሆነ ይቆጠራል።

➢ ካልተመዘገበ ሰው ያገለገሉ እቃዎችን የሚገዛ ያገለገሉ እቃዎች አቅራቢ የሚከተሉትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ በቂ መረጃዎችን መያዝ አለበት፦

✓ ላገለገሉ እቃዎች አቅራቢ እቃዎቹን ያቀረበውን ሰው ስም እና አድራሻ፤

- ✓ ያገለገሉት እቃዎች ላገለገሉ እቃዎች አቅራቢ የቀረቡበትን ቀን፤
- ✓ የቀረቡትን እቃዎች አይነት የሚገልጽ መግለጫ፤
- ✓ የቀረቡትን እቃዎች ብዛት ወይም መጠን፤ እና
- ✓ ለአቅርቦቱ የተፈጸመውን ክፍያ፤

➢ ያገለገሉ ዕቃዎችን የሚገዛ ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ በሚዘጋጅ የክፍያ ደረሰኝ ላይ ያገለገሉ ዕቃዎችን አቅራቢ ማስፈረም አለበት።

## 3.7. የዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት

➢ የዕድል ሙከራ ጨዋታን በሚመለከት የተመዘገበ ሰው በሚያከናውነው በእያንዳንዱ ታክስ የሚከፈልበት ጨዋታ ሳይሆን በእያንዳንዱ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ካከናወነው ጨዋታ በሚገኘው ትርፍ ላይ በመመስረት የሚሰላ ሲሆን በእድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ላይ የተሰማራ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ሊኖረው የሚገባው የውጤት ታክስ ስሌት በሚከተለው ቀመር መሰረት የሚገኘውን የገንዘብ መጠን የሚጨምር ይሆናል፦

**(ሀ-ለ) x ሐ**

በዚህ ቀመር ውስጥ፤

➢ **"ሀ"** ማለት፡- በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የእድል ሙከራ የተደረገበት ጠቅላላ የገንዘብ መጠን፤

➢ **"ለ"** ማለት፡- በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የተሰጠው ሽልማት የገንዘብ ዋጋ፤

➢ **"ሐ"** ማለት የታክስ ክፍልፋይ {15 / (100+15)} ወይም {15%/ (100%+15%)}

➢ በቀመሩ መሰረት ስሌቱ ሲከናወን የአንድ የሂሳብ ጊዜ የገንዘብ መጠን ከዜሮ በታች ከሆነ፤ በሂሳብ ጊዜው የተመዘገበው ሰው የውጤት ታክስ ሆኖ የሚያዝ የገንዘብ መጠን አይኖርም።

➢ የተመዘገበ ሰው ለዕድል ሙከራ ጨዋታው በአቅርቦትነት ባዋላቸው የዕድል ሙከራ ማጫወቻ አቅርቦቶች ላይ የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም እንዲሁም አቅርቦቱን ያከናወነው የተመዘገበ ሰው ለአቅርቦቱ የታክስ ደረሰኝ መስጠት የለበትም።

ምሳሌ፡- በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የዕድል ሙከራ የተደረገበት ጠቅላላ የገንዘብ መጠን 5,000,000 ቢሆን እና የተሰጠው የሽልማት መጠን ደግሞ 1,000,000 ቢሆን፣ ይህንን

(ሀ-ለ)*ሐ በሚለው ቀመር በመጠቀም

(ሀ)=5,000,000 (ለ)=1,000,000 (ሐ)=የታክስ ክፍልፋይ {15%/ (100%+15%)} ነው።

ይህም እንደሚከተለው ይሆናል።

5,000,000 - 1,000,000*(15/115) = 4000000*(15/115) = **521,739.1** የውጤት ታክስ ሆኖ ይወሰዳል።

- “የእድል ሙከራ” ማለት
  - ✓ ሎተሪ፤ ቶምቦላ ወይም ተመሳሳይ ውድድር ማከናወን፤ ወይም
  - ✓ አንድ ውጤት ያለው ወይም እንዲኖረው የተደረገ ውርርድ፤ ጨዋታ፤ የስፖርት ክንውን፤
- “የእድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት” ማለት
  - ✓ በማናቸውም መንገድ የተገለጸ ቢሆንም የሎተሪ፤ የቶምቦላ ወይም ተመሳሳይ የእድል ሙከራ ወይም የውርርድ ቲኬት አቅርቦት፤ ወይም
  - ✓ በማናቸውም መንገድ የተገለጸ ቢሆንም የእድል ሙከራ ወይም የውርርድ ጨዋታ ውጤትን መቀበል ነው።
- “ታክስ የሚከፈልበት የእድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት” ታክስ የሚከፈልበት የእድል ሙከራ ጨዋታ ነው”፤
- “የእድል ሙከራ የተደረገበት ጠቅላላ ገንዘብ” የተመዘገበን ሰው በሚመለከት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የተከናወነው የሚከተሉት ድምር ነው፦
  - ✓ የተመዘገበው ሰው ለሚያቀርባቸው የእድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦቶች በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የተከፈለ ገንዘብ፤እና
  - ✓ በገንዘብ ሽልማቶች ውስጥ ከተጠቃለለው ሂሳብ ውስጥ በተያዘው የሂሳብ ጊዜ ወይም ባለፈው የሂሳብ ጊዜ ከተሰረዘው የገንዘብ መጠን ውስጥ የተመዘገበው ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ መልሶ የሰበሰበው የገንዘብ መጠን
- “ጠቅላላ የገንዘብ ሽልማት” ማለት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የእድል ሙከራ ውርርድ፤ የእድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ወይም የእድል ሙከራ ጨዋታ ኪሳራ የነበረ ቢሆንም ባይሆንም የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ያገጠመው የሚከተለው ሁኔታ ነው:-
  - ✓ በእድል ሙከራ ጨዋታ ውጤት መሰረት የተመዘገበው ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ የከፈለው የጥሬ ገንዘብ ሽልማት፤

- ✓ የተመዘገበው ሰው የእድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ተሳታፊዎች ካጋጠማቸው ኪሳራ ውስጥ የተወሰነውን መልሶ እንዲከፍል በመካከላቸው የነበረው ውል የሚያስገድድ በመሆኑ ምክንያት የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ጊዜው ውስጥ ለእድል ሙከራ ጨዋታ ተሳታፊዎች የከፈለው ገንዘብ፤
- ✓ በዕድል ሙከራ የተገኘው የገንዘብ መጠን በቀዳሚው የሂሳብ ጊዜ አጋጥሞ ከሆነ (ካለ) እና
- ✓ የተመዘገበው ሰው ያልተሰበሰበው እዳ ከተገባበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር 12 ወር ጊዜ ውስጥ ያልሰበሰበው እና በተመዘገበው ሰው ለቀረበ ለሁሉም ወይም ለከፊል የእድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ሊከፈል ሲገባ ያልተከፈለ በመሆኑ ምክንያት ከሂሳብ መዝገብ የተሰረዘ ሊሰበብ የማይችል እዳ፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለጠቅላላ የገንዘብ ሽልማት በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የተካተተው ክፍያ ለአቅርቦት የተፈጸመ ክፍያ እንዳልሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። (የደንቡ አንቀጽ 12/ሠ ሮማን ቁጥር 4)

## 3.8. ውርስ የተደረገ ተቀማጭ ገንዘብ

ማናቸውም አቅራቢ ከዕቃ ወይም ከአገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ተቀማጭ ገንዘብ የተቀበለ እና ይህም ተቀማጭ ገንዘብ በአቅራቢው ውርስ የተደረገ እንደሆነ፣ ተቀማጩ ገንዘብ ውርስ በተደረገበት ጊዜ አቅራቢው የአገልግሎት አቅርቦት እንዳከናወነ ይቆጠራል። የአገልግሎት አቅርቦት እና ውርስ የተደረገው የተቀማጭ ገንዘብ አቅርቦት አንድ ዓይነት ባህሪ ያላቸው እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ። የአገልግሎት አቅርቦት እሴት የሚከተለው ይሆናል፡-

- ➢ ተቀማጩ ገንዘብ ውርስ በተደረገ ጊዜ የተመዘገበ ሰው የነበረን አቅራቢ በሚመለከት፣ በተወረሰው ተቀማጭ ገንዘብ መጠን ላይ ከተቀማጩ ገንዘብ ጋር እኩል የሆነ የገንዘብ መጠን ሲቀነስ እና በታክሱ ክፍልፋይ ሲበዛ፣ ወይም
- ➢ ሌላ ማናቸውንም አቅራቢ በሚመለከት ውርስ የተደረገው ተቀማጭ ገንዘብ መጠን። ይሁን እንጅ ለዕቃ ማሸጊያነት ለሚውሉ ዕቃዎች የሚሰጠውን ተቀማጭ ገንዘብ አይጨምርም።

## 3.9. የመብት፣ የምርጫ እና የቫውቸር አቅርቦት

- ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡-
  - ➢ የመብት፤ የምርጫ ወይም የቫውቸር አቅርቦት ሲኖር፣ እና
  - ➢ መብቱን ወይም ምርጫውን በመጠቀም ሂደት ወይም ለተከታታይ አቅርቦት ክፍያ ቫውቸሩን በሙሉ ወይም በከፊል በመመለስ ሂደት ሌላ አቅርቦት (‹‹ተከታይ አቅርቦት››) ተፈጽሞ ከሆነ።

- የመብት፤ የምርጫ ወይም የቫውቸር አቅርቦቱ ታክስ የማይከፈልበት አቅርቦት ከሆነ እና ተከታይ አቅርቦቱ ብቻ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከሆነ ለተከታዩ አቅርቦት የሚፈጸመው ክፍያ ለመብቱ፤ ለምርጫው ወይም ለቫውቸሩ አቅርቦት የተፈጸመን ክፍያ ይጨምራል፡፡
- የቫውቸር አቅርቦቱ የሚፈጸመው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከሆነ፣ ለተከታታይ ክፍያ ለተከታዩ አቅርቦት ወይም ከመብቱ ወይም ምርጫው አቅርቦት ጋር በተያያዘ በተጨማሪነት ከሚፈጸመው ክፍያ መጠን ሊበልጥ አይችልም፡፡
- ቫውቸርን ማዘጋጀት የአገልግሎት አቅርቦት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ይሁን እንጅ ከታች በ 3.10 በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም ፡፡

## 3.10. ላልተገለጹ አቅርቦቶች የሚውል ቫውቸር

- የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ ቫውቸር ማዘጋጀት ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ አፈጻጸም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደሆነ አይቆጠርም፦
  - ቫውቸሩ በእጁ የሚገኝ ሰው ቫውቸሩን በማስረከብ እስከተወሰነ የገንዘብ መጠን ድረስ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የሚያገኝበት ከሆነ፤
  - ቫውቸሩን መጠቀም የሚቻልባቸው እቃዎች እና አገልግሎቶች የተለየ የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸምን የሚከተሉ ከሆነ፤ እና
  - ቫውቸሩ የተወሰነ የገንዘብ መጠን ይዞ የሚታተም ከሆነ፡፡ ይህ ቫውቸር ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ከሚደረግበት በስተቀር የተመዘገበ ሰው ለሚያከናውነው አቅርቦት በክፍያ መልክ የሚሰጥ ከሆነ የተመለከተው የገንዘብ መጠን ሁለት መልኮች እንዳሉት ሆኖ ይቆጠራል፡-
    - ✓ ለአቅርቦቱ ሙሉ ዋጋ ወይም ከፊል ዋጋ ክፍያ የሚውለው የተወሰነ ገንዘብ ይዞ የታተመው ቫውቸር ተሰልቶ ሊከፈል የሚገባው የታክስ ክፍልፋይ መጠን ተቀናሽ ይደረጋል፣
    - ✓ በአቅርቦቱ ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ በሙሉ ወይም ከፊሉ የተወሰነ ገንዘብ ይዞ የታተመው ቫውቸር የገንዘብ መጠን ላይ በማስከፈያው ታክስ ክፍልፋይ መሠረት እንዲሰላ ይደረጋል፡፡
  - የተጠቀሰው ቫውቸር በሙሉ ወይም በከፊል ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ጊዜው ያለፈ እንደሆነ፡-በቫውቸሩ ጊዜ ማለፍ የቫውቸሩ አቅራቢ ቫውቸሩ ለተሰጠው ሰው የአገልግሎት አቅርቦት እንዳከናወነ ይቆጠራል ከዚሁ ጋር ተያይዞ አገልግሎት አቅርቦት ተፈጽሟል የሚባለው የቫውቸሩ መጠቀሚያ ጊዜ

ባለፈበት ቀን ነው፡፡ የአቅርቦት ዋጋ የሚባለው፡- የቫውቸሩ የመጠቀሚያ ጊዜ ባለፈበት ቀን የተመዘገበ ሰው የነበረን አቅራቢ በሚመለከት ጥቅም ላይ ካልዋለው የቫውቸሩ ዋጋ ላይ፤ ጥቅም ላይ ያልዋለው የቫውቸሩ ዋጋ ሲባዛ በታክስ ክፍልፋይ የሚገኘው ወጤት ተቀንሶ፤ ወይም ለሌላ ማናቸውም አቅራቢ ጥቅም ላይ ያልዋለው የቫውቸሩ ዋጋ፡፡

- ከታች የተዘረዘሩት የተሟሉ በሚሆንበት ጊዜ የአቅርቦቱ ዋጋ እንደሆነ የሚወሰደው የቫውቸሩን የገንዘብ ዋጋ በታክስ ማስከፈያው መጣኔ በማባዛት የሚገኘውን ውጤት ከቫውቸሩ ዋጋ ላይ በመቀነስ የሚገኘውን ሒሳብ ይጨምራል። ለዚህም መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች
  - ✓ የተመዘገበ ሰው ያለአንዳች ክፍያ ቫውቸር ሲሰጥ፣
  - ✓ ቫውቸሩ የተሰጠው ሰው ቫውቸሩን በመጠቀም ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በቅናሽ ዋጋ ከሌላ አቅራቢ መግዛት የሚችል ሲሆን፣እና ምሳሌ ቢካተት

ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ከሚሆንበት በስተቀር ቫውቸሩ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ለመግዛት የሚውል በሚሆንበት ጊዜ ሲሆን አቅራቢው ቫውቸሩን ለተመዘገበው ሰው በሚመልስበት ጊዜ የተመዘገበው ሰው ለአቅራቢው በከፈለው የገንዘብ መጠን ልክ የግብዓት ታክስ ተቀናሽ ያገኛል። ተቀናሽ የሚደረገው የግብአት ታክስ ለአቅራቢው የተከፈለው የገንዘብ መጠን በታክሱ ክፍልፋይ ሲባዛ የሚገኘው ውጤት ሲሆን፣ የግብዓት ታክሱ ተቀናሽ የሚደረገው ለአቅራቢው ክፍያ በተፈጸመበት የሒሣብ ጊዜ ይሆናል።

## 3.11. በቅድመ - ክፍያ የሚቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት

- ይህ በዋናነት ተፈጻሚ የሚሆነው፡-
  - የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ የቅድሚያ ክፍያ በማስከፈል የሚሰጠውን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ ወይም
  - በቅድመ-ክፍያ የሚቀርብን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በማቅረብ ረገድ አከፋፋይ፣ ወኪል ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኝ ሆኖ የሚሰራ ሰው የሚያቀርበውን አገልግሎት በሚመለከት ሲሆን አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ የሚሰጠውን እና በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ መሠረት ከሚከናወን መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተገናኘን አቅርቦት በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም።

➢ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ በቅድመ ክፍያ የሚቀርብን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ከችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በታች በሆነ የቅናሽ ዋጋ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኝ በሚያቀርብ ጊዜ የአቅርቦቱ ዋጋ የሚሰላው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኙ አቅርቦቱን በችርቻሮ መሸጫ ዋጋ እንደገዛ ተቆጥሮ ነው፡፡

➢ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኝ በቅድመ ክፍያ የሚቀርብን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚገዛ እና የሚሸጥ በሚሆንበት ጊዜ፡-

✓ የሚፈጽመው ግfh እንዳልተፈጸመ፣ እና

✓ የሚሸጠው አገልግሎት እንዳልቀረበ፣ ተደርጎ ይቆጠራል።

➢ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢ በቅድመ ክፍያ የሚቀርብን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ወኪል ሆኖ በሚሠራ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አገናኝ አማካኝነት የሚያቀርብ በሚሆንበት ጊዜ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቱ ከሚከፈለው ዋጋ ላይ ለአገናኙ የሚከፈለው ኮሚሽን ተቀናሽ አይደረግም።

## 3.12. የባለዕዳ ዕቃ አቅርቦት

- የተመዘገበ ቢሆንም ባይሆንም ባለዕዳ ለባለገንዘብ መከፈል የሚገባውን ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል ለማስከፈል ባለገንዘቡ የባለዕዳውን ዕቃ ለሦስተኛ ወገን የሸጠ እንደሆነ፡-

➢ ለሦስተኛ ወገን የተከናወነው ሽያጭ በባለዕዳው የተፈጸመ እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠር ሲሆን፣

➢ ባለዕዳው ለባለገንዘቡ አቅርቦቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ መሆኑን በጽሑፍ እስካላረጋገጠለት ድረስ ባለገንዘቡ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት። ባለዕዳው ለባለገንዘቡ የሚሰጠው ማረጋገጫ አቅርቦቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የተደረገበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን አለበት። ማረጋገጫ ያልተሰጠው ባለገንዘብ በእጁ ያለውን ማናቸውንም መረጃ መሠረት በማድረግ አቅርቦቱ በባለዕዳው ቢከናወን ኖሮ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ይሆን እንደነበር አድርጎ መውሰድ ይችላል። የባለዕዳውን ዕቃ የሚሸጥ ባለገንዘብ የከፈለው የግብአት ታክስ ከሚሰበሰበው የውጤት ታክስ ላይ እንዲቀነስለት ማድረግ አይችልም።

- የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ባለገንዘብ፦

➢ የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቅ እና ገቢ ማድረግ፤ እና ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ የታክስ ደረሰኝ የአገልግሎቱ ተቀባይ ለሆነው የተመዘገበ ሰው መስጠት አለበት።

➢ የተመዘገበ ሰው ቢሆንም ባይሆንም አበዳሪው ለሽያጭ የሚያቀርበውን የባለእዳውን እቃ በሚመለከት የሚቀርበው የታክስ ማስታወቂያ በጸደቀው ቅስ መቅረብ ያለበት ሲሆን፤ የሚከተለውን መረጃ ጭምር ሊይዝ ይገባል፦

✓ የአበዳሪውን ስም፤ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲሁም የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥሩን፤

✓ የባለዳውን ስም፤ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲሁም የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥሩን፤

✓ የእቃው አቅርቦት የተፈጸመበትን ቀን፤

✓ ስለቃው መግለጫ እና ብዛት፣

✓ ለአቅርቦቱ የተፈጸመውን ክፍያ የተሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ እና

✓ በጸደቀው ቅጽ የተመለከቱ ሌሎች መረጃዎች፤

➢ አበዳሪው እና ባለዳው አቅርቦቱን እና በአቅርቦቱ ላይ የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና በማናቸውም ታክስ በሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴያቸው ላይ ሊያቀርቡት በሚገባ የታክስ ማስታወቂያ ውስጥ ማካተት የለባቸውም።

➢ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ ያለበት አበዳሪ አቅርቦቱ ከተከናወነበት የሂሳብ ጊዜ መጨረሻ ባለው የመጨረሻ ቀን ወይም ከዚያ በፊት የታክስ ማስታወቂያውን ማቅረብ እና የሚፈለግበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል አለበት።

➢ አበዳሪው የተበዳሪውን እቃ ለሽያጭ በማቅረብ ለአቅርቦቱ ተቀባይ የሚሰጠው የታክስ ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች የሚይዝ መሆን አለበት፦

- ✓ ግልጽ በሆነ ቦታ “ የታክስ ደረሰኝ “ የሚል ጽሁፍ፤
- ✓ የአበዳሪው ስም፤አድራሻ ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤
- ✓ የተበዳሪው ስም፤ አድራሻ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤
- ✓ የአቅርቦቱ ተቀባይ ስም፤ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
- ✓ አቅርቦቱ የተከናወነበት እና የታክስ ደረሰኝ የተሰጠበት ቀን”
- ✓ ስለእቃው መግለጫ ( ብዛቱን እና መጠኑን ጨምሮ) ፤ እና
- ✓ ለአቅርቦቱ የተፈጸመውን ክፍያ እና የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

- ➢ ይሁን እንጅ ከላይ በ 3.12 የተዘረዘሩት ጉዳዮች ባለገንዘቡን ወክሎ የሚሠራን ንብረት ተረካቢን በሚመለከትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 3.13. የመድን አገልግሎት

- ➢ የመድን ሰጪ ድርጅት የሚያቀርበው የጠቅላላ መድን ውል አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡
- ➢ የውሉ አካል ቢሆንም ባይሆንም የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት በደረሰ ጉዳት ምክንያት የጠቅላላ መድን ካሣ የተቀበለ እንደሆነ የዚህ ዓይነቱ ክፍያ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ለአገልግሎቱ አቅርቦት እንደተከፈለው ዋጋ ይቆጠራል፡፡
- ➢ ይህ ተፈፃሚ የሚሆነው ለታክሱ ለተመዘገበ ሰው በሚከፈለው የመድን ካሳ ክፍያ ላይ ብቻ **ነው፡፡** ለታክሱ የተመዘገበ ሰው ከመድን ሰጪው የመድን ካሳ በሚከፈለው **ጊዜ፣** የካሳ ክፍያው መድን ሰጪው ለመድን ተቀባዩ ላቀረበው አገልግሎት የተከፈለ ዋጋ እንደሆነ **ይቆጠራል፡፡**
- ➢ ስለሆነም የካሳ ክፍያ የተከፈለው ለታክሱ የተመዘገበ ሰው በአቅርቦቱ ላይ የሚከፈለውን ታክስ የመሰብሰብ እና ለታክስ ባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ መድን ሰጪው ለተመዘገበው የመድን

አገልግሎት ተጠቃሚ የሚከፍለው የካሳ ክፍያ የተጨማሪ እሴት ታክሱን ያካተተ ተደርጎ ስለሚቆጠር መድን ገቢው የሚከፍለው የውጤት ታክስ መጠን ከታክስ ማስከፈያ መጣኔው ጋር እኩል ነው። የተከናወነው አቅርቦት የተመዘገበው ሰው ክፍያውን በተቀበለ ቀን እንደተፈጸመ የሚቆጠር ሲሆን፣ የአቅርቦቱ ዋጋ ነው የሚባለው የተመዘገበው ሰው ከተቀበለው ገንዘብ ላይ የታክሱ ክፍልፋይ የገንዘብ መጠን ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ሒሣብ ነው።

**ምሳሌ** ለካሳ የተከፈለው ጠቅላላ አቅርቦት 11,500 ብር ቢሆን ይህንን በታክሱ ክፍልፋ አባዝተን የተገኘውን ውጤት ከ11,500 ላይ በመቀነስ የአቅርቦቱን ዋጋ እናገኛለን በዚህም መሰረት

ሀ/(100+ሀ)= 15%/(100+15%) =15/115*115000*= 11,500-1500 =10,000

በዚህም መሰረት የአቅርቦቱ ዋጋ 10,000 ብር ሲሆን ታክሱ 1500 ይሆናል ማለት ነው። ይሁን

እንጅ፡-

- ክፍያ የተፈጸመበት የጠቅላላ የመድን ውል አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ወይም ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግበት ከሆነ፣ ወይም
- የካሣ ክፍያው የተፈጸመው በሰው አካል ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

I. የተመዘገበ የኢንሹራንስ ኩባንያ በአንድ ሌላ ሰው ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት በጠቅላላ መድን ውል መሠረት የካሣ ክፍያ የከፈለ እንደሆነ፣ ከዚህ በታች የተመለከቱት ተሟልተው ሲገኙ ከተከፈለው የካሣ ክፍያ ውስጥ የታክሱ ክፍልፋይ የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲሆን ይደረጋል፡-

- የጠቅላላ መድን አቅርቦት ዜሮ የማስከፈያ መጣኔ ተፈጻሚ ከሚደረግበት ውጪ ያለ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከሆነ፣
- ክፍያው የተፈጸመው በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ላልሆነ የተመዘገበ ሰው ከሆነ፣
- ክፍያው የተፈጸመው የኢንሹራንስ ኩባንያው ለሚያከናውነው አቅርቦት ወይም ወደ ሀገር የማስገባት ተግባር ካልሆነ። የግብአት ታክስ ተቀናሽ የሚደረገው የኢንሹራንስ ኩባንያው ክፍያውን በፈጸመበት የሒሣብ ጊዜ ሲሆን የተመዘገበው የኢንሹራንስ ኩባንያ ለሞራል ወይም በቀጣት መልክ ከሚከፈል

ካሣ በስተቀር በአጠቃላይ የመድን ውሉ መሠረት በተፈጸመ መዳረግ ምክንያት የከፈለውን ካሣ መልሶ የተቀበለ እና በዚህ መልክ መልሶ በተቀበለው ገንዘብ ላይ ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ ከሆነ መልሶ የተቀበለው ገንዘብ የተመዘገበው የኢንሹራንስ ኩባንያ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ካቀረበው አገልግሎት የተቀበለው ገንዘብ እንደሆነ ይቆጠራል። ይህ አቅርቦት የኢንሹራንሱ ኩባንያ የከፈለውን የካሣ ገንዘብ መልሶ በተቀበለበት ቀን እንደተከናወነ ይቆጠራል። ለዚህ አፈጻጸም፡-

- <<ጠቅላላ መድን ስራ>> የሚለው ሐረግ አነስተኛ የመድን ንግድ ስራ ማከናወንን አይጨምርም።
- << የጠቅላላ መድን ስራ ውል>> ማለት የጠቅላላ መድን የንግድ ሥራን በማከናወን ሂደት የተፈጸመ የመድን ውል ነው።

II. መድን ገቢው ለታክሱ የተመዘገበ ሰው ቢሆንም ባይሆንም፣ የመድን ሰጪው ላቀረበው የመድን አቅርቦት የሚከፈለው የአረቦን ክፍያ የአቅርቦቱ ዋጋ እንደሆነ ተቆጥሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ ይደረግበታል። የጠቅላላ መድን አገልግሎት አቅርቦቱ የተከናወነው ለተመዘገበ ሰው በሚሆንበት ጊዜ እና አገልግሎቱን ተጠቅሞ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ከሆነ፣ የተመዘገበው ሰው በአረቦኑ ላይ የከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በግብአት ታክስነት የማቀናነስ መብት ይኖረዋል።

III. በአገር ውስጥ የተመዘገበ የጠለፋ መድን ሰጪ ኩባንያ ለጠለፋ መድን አቅርቦት የሚያስከፍለው አረቦን እና በጠለፋ መድን ውሉ መሰረት የሚከፍለው የካሳ ክፍያ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ የጠቅላላ መድን አቅርቦት ድንጋጌዎችን የሚከተል ይሆናል፡

IV. የጠለፋ መድን ሰጪ ኩባንያው በአገር ውስጥ ያልተመዘገበ በሚሆንበት ጊዜ፣ የተጨማሪ እሴት ታክሱ በቀጥታ በገዢው ሚሰበሰብ ይሆናል። የተመዘገበው መድን ሰጪ በአጠቃላይ መድን ውል መሰረት የመዳረግ መብቱን ተጠቅሞ ለመድን ገቢው የከፈለውን ካሳ ከሌሎች አካላት መልሶ የተቀበለ እንደሆነ የተቀበለው ገንዘብ ታክስ ለሚጣልበት የመድን አገልግሎት እንደተከፈለ ክፍያ ተቆጥሮ በተከፈለው የካሳ ክፍያ ውስጥ የታክስ ክፍልፋይ መጠኑ እንደ ውጤት ታክስ ይቆጠራል።

V. የዕስልምና ኢንሹራንስ ለረጅም ጊዜ መድህን በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈን ከሆነ ከታክሱ ነጻ ይሆናል። የመድን ረዳቶች በአጠቃላይ ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች የሚከፈል የኮሚሽን ክፍያ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ ይደረጋል።

- “የመድን ረዳቶች” የሚባሉት፡- በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጣቸው የመድን ወኪሎች፣ የመድን ደላሎች፣ የጉዳት ገማቾች እና የመድን መርማሪዎች ናቸው።።

## 3.14. ለራስ የሚደረግ አቅርቦት

- የዕቃዎቹን ግ fh ሲፈጽም ወይም ወደ ሀገር ሲያስገባ የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ የተደረገለት የተመዘገበ ሰው ዕቃዎቹን የግብአት ታክስ ተቀናሽ ለማይፈቀድለት ተግባር ያዋለ እንደሆነ ይህ ተግባር ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል።
- በዚሁ መሠረት በተመዘገበ ሰው የተከናወነ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የግብአት ታክስ ተቀናሽ ለማይፈቀድለት ተግባር በዋለ ጊዜ እንደተከናወነ ይቆጠራል።
- በዚህ መሰረት በተከናወነ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የተመዘገበው ሰው የተቀበለው የውጤት ታክስ እንደሆነ የሚቆጠረው የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክስ ተቀናሽ ለማይደረግበት አቅርቦት ያዋለውን ዕቃ በገዛበት ወይም ወደ ሀገር ባስገባበት ጊዜ የከፈለው የግብአት ታክስ ነው።።
- <<የግብአት ተቀናሽ የማይፈቀድለት ተግባር>> ማለት ዕቃን በሚመለከት ዕቃውን ታክስ ከሚከፈልበት አቅርቦት ውጪ ለሆነ አላማ ማዋል ነው፡፥

## 3.15. የውጭ አቅራቢዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ አከፋፈል

ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከተለው የገንዘብ መጠን በላይ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ባላቸው የውጭ አገር አቅራቢዎች ላይ ነው።

- “የውጭ አቅራቢ” ማለት፦
    - በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚታዘዝ እቃ አቅራቢ፤
    - ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት አቅራቢ ወይም
    - የኤሌክትሮኒክ ማከፋፈያ መድረክ አንቀሳቃሽ ነው።
- በኤሌክትሮኒክ ዘዴ አቅርቦትን ስለማከናወን ለተጨማሪ እሴት ታክስ በተመዘገበ ወኪል በኩል ካልሆነ በስተቀር የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትን ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ዕቃዎችን እና አገልግሎቶችን

በኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ሰዎች የሚያቀርብ ነዋሪ ያልሆነ እና ለታክሱ ያልተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚያከናውን ከሆነ ለታክሱ መመዝገብ አለበት። ግብይቱ የተፈጸመው ከነጋዴ ወደ ነጋዴ በሚሆንበት ጊዜ ታክሱ በቀጥታ በገ fh ው ተይዞ የሚሰበሰብ ይሆናል።

- በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚቀርቡ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን የሚጨምር ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡-
  - ➢ ማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ጨዋታ፤ የኤሌክትሮኒክ ውርርድ፤
  - ➢ በበይነመረብ ላይ የተመሰረተ የጨረታ አገልግሎት መስጫ አቅርቦት፤
  - ➢ የማንኛውም ዲጂታል ይዘት ያለው መጽሐፍ ወይም ሕትመትን ጨምሮ የኤሌክትሮኒክ መጽሐፍ አቅርቦት፤
  - ➢ በተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ የሚጫኑ ዲጂታል ይዘት ያላቸው መተግበሪያዎች፣ኢ.መጽሐፍት እና ፊልሞች፣
  - ➢ በደንበኝነት ምዝገባ ላይ የተመሰረተ ሚዲያ ዜና፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ የቴሌቭ fh ን ፕሮግራሞች እና ሙዚቃዎች፣ ፖድካስቶች፣ ብሎግ፣ ጆርናል፣ ወቅታዊ ሕትመት፣ የማህበራዊ ትስስር አገልግሎት፣ ድር ጣቢያ፣ እና የድር መተግበሪያዎችን ማቅረብ፤
  - ➢ የሶፍትዌር ፕሮግራሞችን፣ ድራይቨር፣ የድር ጣቢያ እና ፋየርዎሎችን ማቅረብ፤
  - ➢ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ አስተዳደር የድር ጣቢያ ማስተናገጃ፣የመስመር ላይ ውሂብ ማከማቻ፣ የፋይል መጋራት እና ክላውድ ማከማቻ አገልግሎቶች፤
  - ➢ የሙዚቃ አቅርቦት (የድምጽ ቅንጥብር፣ ስርጭት፣ የቀጥታ ስርጭት፣ የስልክ ጥሪ ድምፅ፣ ዘፈን)
  - ➢ የሰርች ኢንጅን አገልግሎቶችን ጨምሮ የሰርች ኢንጅን እና አውቶሜትድ የደንበኞች እገዛ ዴስክ አገልግሎቶች አቅርቦት፤
  - ➢ ለቀጥታ ዝግጅቶች፣ ቲያትሮች፣ ምግብ ቤቶች ወዘተ የሚውሉ ትኬቶች በኢንተርኔት በኩል መሸጥ፤
  - ➢ በማንኛውም የድምጽ ቪ fh ዋል ወይም ዲጂታል ሚዲያ ላይ ለማዳመጥ፣ ለማየት ወይም ለመጫወት የሚያስችል የዲጂታል ይዘት አቅርቦት፤
  - ➢ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚወስናቸው ማንኛውም ሌላ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚቀርቡ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች።

### 3.15.1. በኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ አማካኝነት ከሩቅ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት

- በኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ አማካኝነት ከሩቅ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሲሟሉ ይሆናል፦
  - ➢ አቅራቢው <<እውነተኛ አቅራቢ>> ተብሎ የሚታወቀው ከሩቅ የሚከናወነውን አቅርቦት የሚያከናውነው በኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ አማካኝነት ሲሆን፣
  - ➢ የኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ ሥራ የሚያከናውነው ሰው <<የሥራ አንቀሳቃሽ>> በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ ቦታ የሌለው ከሆነ፣
  - ➢ የሥራው አንቀሳቃሽ ከሚከተሉት አንዱን የሚያከናውን ከሆነ፦
    - ✓ የአቅርቦቱን ዋጋ ከአቅርቦቱ ተጠቃሚ እንዲጠየቅ የሚያደርግ፤
    - ✓ አቅርቦቱን ለአቅርቦቱ ተጠቃሚ የሚያደርስ ወይም እንዲደርስ የሚያደርግ፤
    - ✓ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አቅርቦቱ የሚከናወንባቸውን የውል ቃሎችና ሁኔታዎች የሚወስን፤ እና
    - ✓ የአቅርቦቱ ተጠቃሚ የኢትዮጵያ ነዋሪ እና ያልተመዘገበ ሰው፤ የመንግስት ተቋም ወይም ከፍተኛ ያልተመዘገበ ሰው፤ ከሆነ ነው።
  - ➢ እነዚህ ድንጋጌዎች ሲሟሉ የኤሌክትሮኒክ ማከፋፈያ ገበያውን ሥራ የሚያከናውነው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ከሩቅ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚታዘዝ ዕቃ አቅርቦት እንደፈጸመ **ይቆጠራል።** ይህም መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ በገዢው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ሳይጨምር ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያከናውን እና በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የሥራ ቦታ የሌለው ሰው የሚያከናውነው የአገልግሎት አቅርቦት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተከናወነ ተቆጥሮ ታክስ ይከፈልበታል። ይህም ተፈጻሚ የሚሆነው በተጨማ ዕሴት ታክስ ህግ መሰረት "በኢትዮጵያ የተከናወነ የአገልግሎት አቅርቦት ነው" የሚለውን መስፈርት ሲያሟላ **ነው።**
  - ➢ በኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ አማካኝነት ከሩቅ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት በተመለከተ ባሉት ድንጋጌዎች ዋንኛው አቅራቢ የተመዘገበ ሰው በሚሆንበት ጊዜ ተፈጻሚ አይሆኑም።

### 3.15.2. በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚቀርብ የትራንስፖርት አገልግሎት

➢ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚቀርብ የትራንስፖርት አገልግሎት ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በዲጂታል መንገዶች "ፕላትፎርም" የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን በሚመለከት ነው፡፡

➢ "ፕላትፎርም አቅራቢ" ማለት የመንገደኞችን የትራንስፖርት አገልግሎት በማመቻቸት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መንገደኞችን ከትራንስፖርት አቅራቢዎች ጋር የሚያገናኝ ማንኛውም ሰው ነው።

➢ በፕላትፎርም አቅራቢ በኩል የሚመቻች የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን በተመለከተ ፕላትፎርም አቅራቢው ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦትን እንዳከናወነ ተደርጎ ይወሰዳል።

➢ የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት የተከናወነበት ቦታ የሚባለው አገልግሎቱ በሚሰጥበት ጊዜ ተሳፋሪው የሚገኝበት ቦታ ሲሆን ማናቸውንም ክፍያዎችን እና ኮሚሽኖችን ጨምሮ ሌሎች ተሳፋሪው ከሚከፍላቸው ጠቅላላ ክፍያዎች ላይ የፕላትፎርሙ አቅራቢ የተጨማሪ እሴት ታክስን መሰብሰብ አለበት።

- የፕላትፎርም አቅራቢው

➢ በየእለቱ መጨረሻ ለመንገደኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

➢ የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለታክስ ባለስልጣኑ ማስተላለፍ አለበት።

➢ አገልግሎት የተሰጠበትን ቀን፣ ሰዓት፣ ቦታ፣ የክፍያ መጠን እና የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ሁሉንም የመንገደኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ዝርዝር መረጃዎችን መያዝ አለበት።

➢ ተገቢውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።

➢ በመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅራቢዎች ምትክ ታክሱን የመሰብሰብ እና የማስተላለፍ ኃላፊነት ቢኖርበትም፣ የትራንስፖርት አቅራቢዎች አመታዊ የሽያጭ መጠን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ የተቀመጠውን የገንዘብ ገደብ የሚያሟላ ከሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ አለባቸው።

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ አሰራር ሥርዓት መሰረት የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅራቢው ከመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት ጋር በቀጥታ ለተያያዙ ግ fh ዎች የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግለት ሊጠይቅ ይችላል።

- የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ፕላትፍሮምን ሳይጠቀሙ ለሚሰጡት ለእያንዳንዱ የትራንስፖርት አገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ የመሰብሰብ እና ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።
- የዕቃ አቅርቦት በኢትዮጵያ ውስጥ ተከናውኗል ለማለት የሚቻለው፡-
  - ➢ የትራንስፖርት አገልግሎትን የሚጨምር የዕቃ አቅርቦት ሲሆን፣ የትራንስፖርት አገልግሎቱ ከኢትዮጵያ የሚነሳ ሲሆን፣ ወይም
  - ➢ ለሌላ ማናቸውም የዕቃ አቅርቦት፣ አቅራቢው ዕቃዎቹን በኢትዮጵያ ውስጥ ለገበያ ዝግጁ ሲያደርግ ይሆናል።
- ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያከናውን እና በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የስራ ቦታ የሌለው ሰው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የታዘዘን ዕቃ በኢትዮጵያ ውስጥ አቅርቧል የሚባለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ሲሆን ይህ ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ የኤሌክትሮኒክ ማከፋፈያው ገበያ አንቀሳቃሽ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ አፈጻጸም የዕቃ አቅርቦት እንደፈጸመ ይቆጠራል።
  - ➢ አቅራቢው ኢትዮጵያ ውስጥ እቃዎችን የሚስረክብ ወይም ግዢ የሚፈጽም፤ የሚያመቻች ወይም የሚያሰናዳ ሲሆን
  - ➢ አቅርቦቱ የተከናወነው በኤሌክትሮኒክ የማከፋፈያ ገበያ ሲሆን፤
  - ➢ የኤሌክትሮኒክ ማከፋፈያ ገበያውን የሚያስተዳድረው ሰው ዕቃውን ለማቅረብ ወይም አቅርቦቱን ለማመቻቸት የሚያስፈልገውን ግ fከ ከኢትዮጵያ የሚፈጽም ከሆነ፤ እና
  - ➢ ዕቃዎቹ የኤክሳይዝ ታክስ ያልተጣለባቸው ወይም የጉምሩክ ቀረጥ የማይከፈልባቸው ከሆነ ነው።
- በኢትዮጵያ የተከናወነ የአገልግሎት አቅርቦት፡-
  - ➢ የአገልግሎት አቅርቦት በኢትዮጵያ ውስጥ ተከናውኗል ለማለት የሚቻለው አገልግሎቱ የተሰጠበት የአቅራቢው የንግድ ሥራ ቦታ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ነው።።

➢ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ሳይጨምር ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚያከናውን እና በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የሥራ ቦታ የሌለው ሰው የሚያከናውነው የአገልግሎት አቅርቦት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተከናወነ ይቆጠራል፤

✓ አገልግሎቱ በአካል በኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወነ ሆኖ አቅርቦቱ በተሰጠ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በነበረ ሰው ከሆነ፣

✓ አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተገናኘ ከሆነ፤

✓ አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን፣

✓ አገልግሎቱ በጥቅል የሚሰጥ የቱሪዝም አገልግሎት ወይም በጥቅል ከሚሰጥ የቱሪዝም አገልግሎት ጋር የተያያዘ የውክልና ወይም የምዝገባ አገልግሎት ሲሆን፤

✓ አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ መጠቀም የሚቻል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ከሆነ፤ ወይም

✓ አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ መጠቀም የሚቻል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ከሆነ፤ የሚለውን ሳይጨምር የዓለም አቀፍ የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆነ ሰው ሞባይል ላይ የተጫነው የደንበኛ ማንነት ሞጁል ካርድ የሚያሳየው የሞባይል የሀገር መለያ ቁጥር የኢትዮጵያ ከሆነ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

➢ አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ሰው ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን ለሚለው አፈጻጸም ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መለኪያዎች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱ ከተሟሉ ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ እንደሆነ ይቆጠራል፡-

✓ ለአገልግሎቱ ተቀባይ የክፍያ መጠየቂያ የሚላክበት አድራሻ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሆነ፤

✓ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለክፍያ የሚጠቀምበትን የባንክ ሒሣብ ወይም በባንኩ ዘንድ የሚገኘውን የክፍያ መጠየቂያ አድራሻ ጨምሮ የተጠቃሚው የባንክ ሂሳብ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሆነ፤

- ✓ ለተጠቃሚው የስልክ አገልግሎት የሚሰጥበት የማይንቀሳቀስ ስልክ መስመር በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፤
- ✓ የዓለም አቀፍ የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ሰው በሚገለገልበት የደንበኛ ማንነት ሞጁል ካርድ ላይ የተጫነው የተንቀሳቃሽ ስልክ የሀገር መለያ ቁጥር የኢትዮጵያ ከሆነ፣
- ✓ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ አገልግሎቱን የሚያገኝበት መሳሪያ የኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻ ወይም ሌላ የቦታ አድራሻ መለያ የኢትዮጵያ ከሆነ፤ ወይም
- ✓ ሌላ ማናቸውም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የኢትዮጵያ ነዋሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ ለንግድ አግባብነት ያለው መረጃ። ከተዘረዘሩት መለኪያዎች ውስጥ ሁለቱ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በኢትዮጵያ ነዋሪ መሆኑን የሚደግፉ እና ሁለቱ ደግሞ በሌላ ሀገር ነዋሪ መሆኑን የሚደግፉ በሚሆንበት ጊዜ የአገልግሎቱን ተጠቃሚ አድራሻ ለመወሰን የበለጠ አስተማማኝ ናቸው የሚላቸውን መሠረት በማድረግ አቅራቢው የአገልግሎቱን ተጠቃሚ አድራሻ ይወስናል። ከላይ ከተዘረዘሩት መለኪያዎች ውስጥ አስተማማኝ ከሆነው በመጀመር አስተማማኝነትን መሠረት በማድረግ በቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል። አቅራቢውም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በኢትዮጵያ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በገfhው ተይዞ የሚከፈል ታክስ በሚለው አሰራር ካላስታወቀው በስተቀር የአገልግሎቱ ተጠቃሚ አቅርቦቱን በተመለከተ በገዢው የሚሰበሰብ ታክስ የማይመለከተው እንደሆነ መቁጠር አለበት።

<u>የሙከራ ጥያቄ</u>

- ➢ የዕድል ሙከራ ጨዋታ አቅርቦት ታክስ የሚከፈልበትን ሂደት አብራራ?

## ክፍል አራት
## አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ እና የአቅርቦት ዕሴት

### 4.1. አቅርቦት ተከናወነ የሚባልበት ጊዜ

- አቅርቦቱ ተከናወነ የሚባለው ከሚከተሉት በቀደመው ጊዜ ነው፡-

➢ ለአቅርቦቱ የታክስ ደረሰኝ በተሰጠበት ቀን፣

➢ ለአቅርቦቱ ማናቸውም ዓይነት ክፍያ (ከፊል ክፍያን ጨምሮ) በተፈጸመበት ቀን፣

➢ ከሚከተሉት አንዱ በተፈጸመበት ቀን፡-

  ✓ የዕቃ አቅርቦትን በሚመለከት፣ የዕቃው ርክክብ በተፈጸመበት ወይም ዕቃው ለአቅርቦቱ ተቀባይ ዝግጁ በሆነበት ቀን ወይም

  ✓ የአገልግሎት አቅርቦትን ወይም በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት በሚመለከት፣ አገልግሎት የመስጠቱ ተግባር ሲጠናቀቅ።

➢ የዕቃው አቅርቦት በማንቲም፣ በወረቀት ገንዘብ ወይም ገንዘብን በሚተካ ነገር በሚሠራ ማሽን፣ የመቁጠሪያ መሣሪያ ወይም ሌላ መሣሪያ አማካኝነት የሚፈጸም ከሆነ፣ በአቅራቢው ወይም አቅራቢውን በሚወክለው ሰው አማካኝነት ማንቲሙ፣ የወረቀት ገንዘቡ ወይም ገንዘብን የሚተካው ነገር ከማሽኑ፣ ከመቁጠሪያ መሣሪያው ወይም ከሌላ መሣሪያ በወጣበት ቀን አቅርቦቱ እንደተከናወነ ይቆጠራል።

- ማናቸውም በተወሰነ ጊዜ ልዩነት የሚከናወን አቅርቦት፡-

➢ በኪራይ ውሉ ወይም በስምምነቱ መሠረት ወይም እንደሁኔታው በሕግ በተወሰነው መሠረት ክፍያው የሚፈጸመው ለውሉ ከፊል ጊዜ በተከታታይነት ከሆነ የዚህ አይነቱ አቅርቦት በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በተከታታይነት ክፍያው የሚፈጸም ራሱን የቻለ አቅርቦት እንደሆነ፣ እና

➢ እያንዳንዱ ተከታታይ አቅርቦት ክፍያው ሊፈጸም በሚገባው ቀን ወይም ክፍያው በተፈጸመበት ቀን ከሁለቱ በቀደመው እንደተከናወነ፣ ይቆጠራል።

- <<በተወሰነ ጊዜ ልዩነት የሚከናወን አቅርቦት>> ማለት፡-

➢ በዱቤ ግfh ወይም በፋይናንስ ሊዝ ውል መሠረት የሚቀርብ ዕቃ፣ ወይም

➢ የሚከተሉትን አቅርቦት የሚያሟላ የአገልግሎት

  ✓ በዕቃ ኪራይ ውል የተሰጠ (ሊዝን ሳይጨምር)፤ ወይም

  ✓ ክፍያው በተወሰነ ጊዜ ልዩነት እንዲፈጸም በሚያዝ ውል ወይም ሕግ መሠረት በየደረጃው የሚፈጸም አቅርቦት።

## 4.2. የአቅርቦት እሴት

- የአቅርቦት እሴት ነው የሚባለው ለአቅርቦቱ የተከፈለው የግብይት ዋጋ ሲሆን የተመዘገበ ሰው አቅርቦቱን ያከናወነው ግንኙነት ላለው ሰው ከአቅርቦቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ በታች በሆነ ዋጋ (በነጻ የተከናወነ አቅርቦት ጭምር) የሆነ እንደሆነ የአቅርቦቱ ዋጋ እንደሆነ የሚቆጠረው አቅርቦቱ በተከናወነ ጊዜ ያለው የአቅርቦቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ **ይሆናል።** ከዚህጋር ተያዞ በነጻ የተከናወነ አቅርቦት ዋጋ ዜሮ **ነው።** የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ሲያከናውን የተጨማሪ እሴት ታክሱን መጠን ለይቶ ያላሳየ እንደሆነ የአቅርቦቱ ዋጋ በሚከተለው ቀመር መሠረት **ይሰላል።**

ሀ- (ሀ X

ለ) በዚህ ቀመር ውስጥ

"ሀ" ማለት፡- ለአቅርቦቱ የተከፈለው ጠቅላላ ዋጋ እና

"ለ" ማለት፡- የታክሱ ክፍልፋይ ነው።

- ➢ የተመዘገበ ሰው ለሌላ የተመዘገበ ሰው የሚያከናውነውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት በሚመለከት ተፈጻሚ በሚደረግበት ጊዜ፣ አቅርቦቱን የተቀበለው የተመዘገበ ሰው የግብአት ታክስ የሚሰላው ሀ - (ሀ X ለ) መሠረት በሚወሰነው የዕቃው ዋጋ ይሆናል።
- ➢ ከውጭ ሀገር በገባ የዕቃ አቅርቦት ላይ የተከፈለው ዋጋ ከዕቃው የጉምሩክ ዋጋ በታች የሆነ እንደሆነ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የዕቃው የጉምሩክ ዋጋ የአቅርቦቱ ዋጋ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል።

### 4.2.1. ወደ ሀገር የገባ ዕቃ እሴት

- ወደ ሀገር የገባ ዕቃ እሴት የሚከተሉት ድምር ይሆናል፡-
  - ➢ ወደ ሀገር የገባው ዕቃ ቀረጥ የሚከፈልበት ቢሆንም ባይሆንም በጉምሩክ የሚወሰነው የዕቃው ዋጋ እና
  - ➢ ወደ ሀገር በገባው ዕቃ ላይ የሚከፈል የጉምሩክ ቀረጥ፣ የኤክሳይዝ ታክስ እና ሌላ ማናቸውም ታክስ እንዲሁም ማናቸውም ክፍያ የሚያካትት ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስን ወይም በዕቃው ላይ የሚከፈልን ወይም የተከፈለን የገቢ ግብር የቅድሚያ ክፍያን አይጨምርም።
  - ➢ ወደ ሀገር በገባው ዕቃ ላይ፡-
    - ✓ የቅርጽ ወይም የባህሪ ለውጥ እና
    - ✓ ዕቃው ወደውጭ ከተላከበት ጊዜ አንስቶ የባለቤትነት ለውጥ እስካልተደረገ ድረስ ለጥገና፣ ለዕድሳት ወይም ለማሻሻያ ወደ ውጭ ሀገር የተላከ ዕቃ ተመልሶ ወደ ሀገር በሚገባበት ጊዜ

ለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ መሠረት የሚሆነው በጥገናው፣ በዕድሳቱ ወይም በማሻሻያው ምክንያት የታከለው ተጨማሪ እሴት ይሆናል፡፡

- ወደ ቦንድ የጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃን በሚመለከት እሴት ነው ተብሎ የሚወሰደው ከሚከተሉት ከፍተኛው ይሆናል፡-
    - ✓ ወደ ሀገር የገባው ዕቃ ቀረጥ የሚከፈልበት ቢሆንም ባይሆንም በጉምሩክ የሚወሰነው የዕቃው ዋጋ እና
    - ✓ ከቅድመ ክፍያ እና ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ በስተቀር ማንኛውም ክፍያ ወይም
    - ✓ ወደ ቦንድ የጉምሩክ መጋዘን የገባ እና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን አጠናቆ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውል ያልወጣ እቃ የሚወሰነው አቅርቦት እሴት፣
- <<የገቢ ግብር የቅድሚያ ክፍያ>> የሚባለው ወደ ሀገር በሚገባ ዕቃ ላይ የሚከፈለው ግብር ነው፡፡

## 4.2.2. ዕቃ ወደ ሀገር ገባ የሚባልበት ጊዜ

- ዕቃ ወደ ሀገር ገብቷል የሚባለው፡-
    - ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎችን በሚመለከት፡- የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን ባጠናቀቁበት ቀን፤
    - ለሌሎች ማናቸውንም ዕቃዎች በተመለከተ፡- ዕቃዎቹ ወደ ኢትዮጵያ በገቡበት ቀን ይሆናል፡፡
    - ወደ ቦንድ የጉምሩክ መጋዘን የገባ እና የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን አጠናቆ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውል ያልወጣ ዕቃን በሚመለከት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውል ከመጋዘን ከመውጣቱ በፊት የተከናወነ አቅርቦት ለዚህ ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ አፈጻጸም ከግምት ውስጥ የሚገባ አይሆንም፡፡
    - “የተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን” ማለት፡- የጉምሩክ ስነስርዓት ያልተፈጸመባቸው እቃዎች እንዲከማቹበት በኮሚሽኑ ፈቃድ የሚቋቋም የወል ጊዚያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም የወል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን እና የግል ጊዚያዊ ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ መጋዘን ወይም የግል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ነው፡፡
    - ወደአገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈል ከሆነ አስመጪው እቃዎቹ ወደአገር በገቡበት ጊዜ የገቢ እቃ ዲክላራሲዮን ለኮሚሽኑ ማቅረብ እና ወደአገር በገቡት እቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክሱን መክፈል አለበት፡፡

➢ የገቢ እቃ ዲክላራሲዮኑ፣

✓ ኮሚሽኑ በሚወስነው ቅጽ መሆን አለበት፤

✓ ወደአገር በገባው እቃ ላይ ተገቢውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማስላት የሚያስችል አስፈላጊውን መረጃ የያዘ መሆን አለበት

✓ ኮሚሽኑ በሚወስነው የአቀራረብ ሥርዓት መሰረት መቅረብ አለበት።

➢ በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት የሚሸፈን እቃ አስመጪው በቀረጥ ተመላሽ ስርአት የሚጠቀም ካልሆነ በስተቀር የተጨማሪ እሴት ታክስ አይከፈልበትም።

### 4.2.3. ወደ ሀገር በሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማዘግየት

- የተመዘገበ ሰው የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም ወደ ሀገር በሚያስገባቸው የካፒታል ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲዘገይ ለኮሚሽኑ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል። ኮሚሽኑ ማመልከቻ ሲቀርብለት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያምንበት ክፍያው እንዲዘገይ ሊፈቅድ ይችላል፡-

➢ የተመዘገበው ሰው ተገቢውን መረጃ የሚይዝ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢውን በወቅቱ የሚያስታውቅ እና ሌሎች ግዴታዎች የሚወጣ፤

➢ የተመዘገበው ሰው የሚፈለግበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ሌላ የግብር ዕዳ የሌለ እና

➢ አመልካቹ ሰው፡-

✓ በታክስ አስተዳደር ህግ መሰረት የሚፈለግበት አስተዳደራዊ መቀጫ የሌለ፤

✓ በታክስ አስተዳደር ህግ መሰረት ተከሶ ያልተፈረደበት ወይም

✓ በተመሳሳይ ጥፋት ምክንያት በጉምሩክ አዋጅ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት የማይፈለግበት ወይም በወንጀል ያልተቀጣ።

➢ ኮሚሽኑ እንዲዘገይ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ማመልከቻ ያቀረበው የተመዘገበ ሰው ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል። ኮሚሽኑ ማመልከቻ ያቀረበው ሰው ማመልከቻውን ባቀረበ በ 14 ቀናት ውስጥ በጥያቄው መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ እንዲያውቅ ማድረግ አለበት።

➢ በኮሚሽኑ እንዲዘገይ የሚሰጠው ፈቃድ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

✓ በፈቃዱ ለተመለከቱ ወደ ሀገር ለሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ወይም

✓ በፈቃዱ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ወደ ሀገር ለሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ይሆናል።

- የተመዘገበው ሰው፡-
  - ➢ ከላይ "አመልካቹ ሰው በሚለው ስር የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ወይም መስፈርቶች ካጓደለ ወይም
  - ➢ የካፒታል ዕቃዎቹን ለሌላ ሰው ካስተላለፈ ወይም ካስወገደ ኮሚሽኑ የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል።
  - ➢ ሊከፈል የሚገባው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ እንዲዘገይ ፈቃድ የተሰጠው የተመዘገበ ሰው ዕቃው ወደ ሀገር በገባበት የሒሣብ ጊዜ ሊከፈል የሚገባውን የተጣራ የተጨማሪ እሴት ታክስ ስሌት በሚያከናውንበት ጊዜ በፈቃዱ በተመለከተው ታክስ በሚከፈልበት የካፒታል ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካተት አለበት።
  - ➢ ሚኒስቴሩ ወደ ሀገር በሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲዘገይ የሚደረግበትን ሁኔታ በመመሪያ ሊወሰን ይችላል።
  - ➢ <<የካፒታል ዕቃ>> የሚለው ሀረግ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ለሽያጭ የሚያውለውን ወደ ሀገር የሚገባ የካፒታል ዕቃ አይጨምርም።
- ዘግይቶ ለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ለኮሚሽኑ ማመልከቻ የሚያቀርብ የተመዘገበ ሰው ከታክሱ ባለስልጣን የተሰጠውን የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት በደጋፊ ማስረጃነት አያይዞ ማቅረብ አለበት።

## 4.3. በአቅርቦት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ መለወጥ

I. ማናቸውም አቅራቢ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ በውሉ ወይም በሌላ ህግ የተደነገገው ቢኖርም ለአቅርቦቱ ከሚከፍለው ዋጋ በተጨማሪ የተጣለውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከአቅርቦቱ ተቀባይ ሊጠይቅ ይችላል።

- ✓ የተመዘገበ ሰው ለእቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ውል የፈረመ ከሆነ እና
- ✓ ውሉን ከፈረመ በኋላ በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተጣለ፤

II. ማናቸውም አቅራቢ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ በውሉ ወይም በሌላ ህግ የተደነገገው ቢኖርም በአቅርቦቱ ተቀባይ ሊከፈል የሚገባውን ሂሳብ ቀሪ በተደረገው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ልክ መቀነስ አለበት።

- ✓ የተመዘገበ ሰው ለእቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ውል የፈረመ ከሆነ፤

- ✓ ውሉን ከፈረመ በኋላ በአቅርቦቱ ላይ ተጥሎ የነበረው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከተነሳ፤

III. ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ እና ሁለት ተፈጻሚ የሚሆኑት በታክስ ህግ የተጣለ ማናቸውም አይነት ክፍያ፣ የዕቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን (በቁጥር የሚከፈል፣ ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ክፍያ፣ የዕቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን ቢሆንም) ተፈጻሚ በሚሆንበት የዕቃ እና የአግልግሎት አቅርቦት ላይ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አይነቱ ክፍያ የዕቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን እንደሁኔታው ሊከፈል በሚገባው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ወይም በታከለው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ልክ ከፍ ማለት ወይም ቀሪ በተደረገው የተጨማ ዕሴት ታክስ ልክ ዝቅ ማለት አለበት። ነገር ግን በናቸውም የታክስ ህግ የተወሰነው ክፍያ የዕቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን የተጣለውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ወይም የተነሳውን የተጨማሪ ዕሴት ታስ ከግምት ውስጥ ያስገባ በሚሆንበት ጊዜ ይህ ተፈጻሚ አይሆንም።

IV. በአቅርቦቱ ላይ የተጣለው ክፍያ፣ የእቃ እና የአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን የሚሰላው ለአቅርቦቱ ከተወሰነው አንድ የገንዘብ መጠን በመቶኛ ወይም በክፍልፋይ የሆነ እንደሆነ ከላይ የተገለጸው የሮማን ቁጥር ሦስት ድንጋጌ በክፍያ በእቃ እና በአገልግሎት ዋጋ ወይም ሌላ የገንዘብ መጠን ላይ እንደሁኔታው ሌላ ጭማሪ ወይም ቅናሽ ማድረግን የሚፈቅድ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም።

### 4.3.1. በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በሚከናወን አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም ላይ የሚደረግ ለውጥ

I. ከታች የሮማን ቁጥር ሁለት ተፈጻሚ የሚሆነው እና የአቅርቦቱ ዋጋ የሚወሰነው የሚከተሉት ተሟልተው ሲገኙ ነው።

- ➢ ሀ) በተወሰነ ጊዜ ልዩነት የሚከናወን አቅርቦት የዕቃ አቅርቦት የተፈጸመው ወይም አገልግሎት የተሰጠው የሚከተሉት ከመጀመራቸው በፊት ወይም ከመጠናቀቁ በኋላ ከሆ፤
  - ✓ በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተጣለበት ቀን ወይም
  - ✓ በአቅርቦቱ ላይ ተጥሎ የነበረው የተጨማሪ እሴት ታክስ የተነሳበት ቀን፤
- ➢ ለ) እቃው ወይም አገልግሎቱ የቀረበበት ቀን ከላይ ፊደል (ሀ) በተመለከተው ቀን ወይም ከዚያ ቀን በኋላ ከሆነ፤

II. ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ የተመለከቱት ሁኔታዎች የተሟሉ በሚሆንበት ጊዜ፤

- አዲስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ቢጣል ታክሱ ከመጣሉ በፊት ላለው አቅርቦት አዲሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አይሆንም፡፡ ወይም
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ቢነሳ ታክሱ ከመነሳቱ በፊት ያለው አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዳልተነሳ ተቆጥሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈልበታል፡፡

### 4.3.2. በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የሚደረግ ለውጥ በሌሎች ሁኔታዎች የሚኖረው ተፈጻሚነት

1. የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ከታች በቁጥር ሁለት የተገለጸው ተፈጻሚ ይሆናል፦
   - ሀ) ከማይንቀሳቀስ ንብረት በስተቀር አቅራቢው ከሚከተለው ጊዜ በፊት ያቀረባቸው እቃዎች ሲሆኑ፦
     (i) በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተጣለበት ቀን በፊት ወይም
     (ii) በአቅርቦቱ ላይ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተነሳበት ቀን በፊት፤
   - ለ) የእቃው አቅርቦት የተፈጸመው ከላይ በተራ ቁጥር አንድ ፊደል (ሀ) በተመለከተው ቀን ወይም ከዚያ በኋላ ሲሆን፤
2. ከላይ በቁጥር አንድ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ፦
   - በተራቁጥር አንድ (ሀ) ሮማን ቁጥር (i) በተመለከተው መሰረት ከአዲሱ ታክስ ጋር በተያያዘ አቅርቦቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፈልበት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ወይም
   - ከላይ በተራቁጥር (1) (ሀ) (ii በተመለከተው መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚነሳበት ጊዜ አቅርቦቱ ታክሱ እንዳልተነሳለት ተቆጥሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፤
3. የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ከታች በተራ ቁጥር አራት (4) የተገለጸው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
   - ሀ) በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በሚከናወን አቅርቦት ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ አገልግሎት የተሰጠ ወይም የእቃ አቅርቦት የተከናወነ በሚሆንበት ጊዜ፤

     i በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ በተጣለበት ቀን ወይም

     ii በአቅርቦቱ ላይ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተነሳበት ቀን፤
   - ለ) የእቃው አቅርቦት እና አገልግሎት የመስጠቱ ተግባር የተከናወነበት ጊዜ ከላይ በፊደል (ሀ) በተመለከተው ቀን ወይም ከዚያ ቀን በኋላ ከሆነ፤

4. ከላይ በተራ ቁጥር ሦስት የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ፡-

- ሀ) የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዲስ መልክ የተጣለ ሲሆን አቅርቦቱ ተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፈልበት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
- ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ የተነሳ እንደሆነ ታክሱ እንዳልተነሳ ተቆጥሮ ግብይቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

5. የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ከታች በተራ ቁጥር ስድስት የተገለጸው ተግባራዊ ይሆናል፦

ሀ)በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በሚከናወን አቅርቦት ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ አገልግሎት የተሰጠ ወይም የእቃ አቅርቦት የተከናወነ በሚሆንበት ጊዜ፡-

- በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ በተጣለበት ቀን ወይም
- በአቅርቦቱ ላይ ተጥሎ የነበረ የተጨማሪ እሴት ታክስ በተነሳበት ቀን፤

ለ) የእቃ እና አገልግሎት አቅርቦት ተፈጽሟል የሚባለው ከላይ በቁጥር አምስት ፊደል (ሀ) በተመለከተው ቀን ወይም ከዚያ ቀን በኋላ ነው፡፡

6. ከላይ በተራቁጥር አምስት የተመለከቱት ሁኔታዎች የተሟሉ በሚሆንበት ጊዜ የአቅርቦቱ ዋጋ የሚወሰነው በሚከተለው ሁኔታ ነው፦

- አዲስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ቢጣል አዲሱ ታክስ ከመጣሉ በፊት የነበረው ግብይት አዲሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት አይሆንም ወይም
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ቢነሳ ታክሱ ከመነሳቱ በፊት የነበረው ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዳልተነሳ ተቆጥሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይከፈልበታል፡፡

7. ከላይ ለተገለጹት ተራቁጥር (1)፤ (3) እና (5) አፈጻጸም እቃን በሚመለከት የአቅርቦት ተቀባዩ እቃውን በተረከበ ጊዜ እንዲሁም አቅርቦቱ የተፈጸመው በኪራይ ውል በሚሆንበት ጊዜ እቃው በአቅርቦቱ ተቀባይ ይዞታ ስር በዋለበት ጊዜ አቅራቢው አቅርቦቱን እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

<u>የሙከራ ጥያቄ</u>

የአቅርቦት ዕሴት ማለት ምን ማለት ነው?

ወደሀገር የሚገቡ ዕቃዎች ላይ የአቅርቦት ዕሴት የሚባሉትን ዘርዝር?

# ክፍል አምስት

## የግብዓት ታክስ ተቀናሽ እና ማስተካከያ ስለማድረግ

## 5.1. የግብዓት ታክስ ተቀናሽ

I. ተቀናሽ እንዲሆን የተፈቀደ የግብዓት ታክስ

- አቅርቦቱ ወይም ወደ ሀገር የማስገባቱ ተግባር በተከናወነበት ጊዜ ግዢው የተፈጸመው ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት መሆኑ ለተረጋገጠ ተቀናሽ ለሚደረግ ግ fh የተመዘገበ ሰው የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
- ተጨማሪ ዕሴት ታክስ በባህሪው በግ fh (ግብዓት) ላይ የተከፈለን ታክስ በሽያጭ (በውጤት) ላይ ከተከፈለው ታክስ የማቀናነስ እና የተንከባላይነት ባህሪ ያለው **ነው፡፡**
- በዚህም መሰረት <u>ተከፋይ ታክስ = ሽያጭ ላይ የተከፈለ ታክስ - ግf h ላይ የተከፈለ ታክስ</u> **ምሳሌ፡-**

ቢ.ፒ.ኤን እንጨት አቅራቢ ድርጅት የዋንዛ እንጨት የሆኑ ጥሬ ዕቃችን ለኤፍ.አር.ኤስ ጣውላና ኤም.ዲ.ኤፍ አቅራቢ ድርጅት በ 500,000 ብር ቢሸጠለት፤ ቢ.ፒ.ኤን እንጨት አቅራቢ (500,000 የዕቃው የሽያጭ ዋጋ*15%) = 75,000 ብር የሽያጭ ታክስ ለመንግስት ይከፍላል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኤፍ.አር.ኤስ ጣውላና ኤም.ዲ.ኤፍ አቅራቢ በ 500,000 ብር የገዛውን ጥሬ እቃ ወደ ጣውላ እና ኤምዲኤፍ በመቀየር በ 1,000,000 ብር ለጂ.ኤም.ሲ ፈርኒቸር ሸጠለት፤ ኤፍ.አር.ኤስ ጣውላና ኤምዲኤፍ አቅራቢ (1,000,000*15%) =150,000 ብር **ይሆናል፡፡** 150,000 ብር የሽያጭ ታክስ ሲቀነስ 75,000 ብር የግብዓት ታክስ = 750,00 ብር ለመንግስት ታክስ ይከፍላል፡፡ ጂ.ኤም.ሲ ፈርኒቸር በ 1,000,000 የገዛውን ጣውላና ኤም.ዲኤ.ፍ ወደ አልጋ እና ቁምሳጥን በመቀየር ለኤም.ኦ.አር በ 2,000,000 ሸጠለት በዚህም መሰረት ጂ.ኤም.ሲ (2,000,000*15%) = 300,000 ብር **ይሆናል፡፡** 300,000 ብር የሽያጭ ታክስ ሲቀነስ 150,000 ብር የግብዓት ታክስ = 150,000 ብር ለመንግስት የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የሚከፍል ይሆናል፡፡ ኤም.ኦ.አር የእንጨት ስራ ውጤቶች ቸርቻሪ በ 2,000,000 ብር የገዛቸውን ቁምሳጥን እና አልጋዎች በ 3,000,000 ብር ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች ሸጣላቸው ኤም.ኦ.አር የእንጨት ስራ ውጤቶች ቸርቻሪ (3,000,000*15%) = 450,000 **ይሆናል፡፡** 450,000 ብር የውጤት ታክስ ሲቀነስ 300,000 ብር የግብዓት ታክስ = 150,000 ብር ለመንግስት ይከፍላል ማት **ነው፡፡** የተጨማሪ ዕሴት ታክስን የሚከፍለው የመጨረሻው ተጠቃሚ በመሆኑ መጨረሻ ላይ ዕቃዎቹን የገዙት ተጠቃሚዎች በከፈሉት ታክስ ላይ የሚቀናነስላቸው ነገር አይኖርም፡፡ ስለሆነም በዚህ የአቅርቦት ሰንሰለት ሂደት ውስጥ መንግስት 450,000 ብር ከተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ያገኛል ማለት ነው፡፡ ከላይ የቀረበውን ምሳሌ በሚከተለው መልኩ ጠቅለል ተደርጎ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

| የንግድ ስራዎች | ግfh | ሽያጭ | የግብዓት | የሽያጭ | ተከፋይ ታክስ |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | ታክስ | ታክስ | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቢ.ፒ.ኤን እንጨት አቅራቢ | 0 | 500,000 | 0 | 75,000 | 75,000 |
| ኤፍ.አር.ኤስ ጣውላና ኤምዲኤፍ አቅራቢ | 500,000 | 1,000,000 | 75,000 | 150,000 | 75,000 |
| ጂ.ኤም.ሲ ፈርኒቸር | 1,000,000 | 2,000,000 | 150,000 | 300,000 | 150000 |
| ኤም.ኦ.አር የእንጨት ስራ ውጤቶች ቸርቻሪ | 2,000,000 | 3,000,000 | 300,000 | 450,000 | 150,000 |
| **አጠቃላይ** | | | | | 450,000 |

የተመዘገበ ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ተቀናሽ የሚደረግ ግfh በከፊል ታክስ ለሚከፈልባቸው አቅርቦቶች በከፊል ደግሞ ለሌሎች አቅርቦቶች የዋለ ከሆነ ተቀናሽ የሚደረገው የግብአት ታክስ የሚሰላው በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሆናል፡-

**ሀ x ለ/ሐ**

- ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፡-
  - “ሀ” ማለት፡- የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ባከናወነው በከፊል ታክስ ለሚከፈልባቸው አቅርቦቶች በከፊል ደግሞ ለሌሎች አቅርቦቶች በዋለው ተቀናሽ የሚደረግ ግfh ላይ የከፈለው የግብአት ታክስ ጠቅላላ ድምር፣
  - “ለ” ማለት፡- የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ጠቅላላ ዋጋ ድምር፣
  - “ሐ” ማለት የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ጠቅላላ አቅርቦት ዋጋ ድምር።
- ከላይ በተመለከተው ቀመር የ “ለ/ሐ” ክፍልፋይ፡-
  - “ሀ” 0.95 (ዜሮ ነጥብ ዘጠኝ አምስት) ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ የተመዘገበው ሰው ባከናወነው ተቀናሽ የሚደረግ ግ fh ላይ የከፈለው የግብአት ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ይደረጋል።
  - “ለ” ከ 0.05 (ዜሮ ነጥብ ዜሮ አምስት) በታች ከሆነ ተቀናሽ የሚደረግ ግ fh ላይ የከፈለው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም። ይህንን ጉዳይ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ከታች በምሳሌ ለማብራራት ተሞክሯል።

ለምሳሌ፡- ጂ.ም.ሲ. ፈርኒቸር በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ጠቅላላ አቅርቦት ዋጋ 1,000,000 ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ታክስ ሚከፈልበት አቅርቦት ጠቅላላ ድምር 800,000 ነው በዚህ መሰረት የተጨማሪ ዕሴት ታክሱ (15%*1,000,000) =150,000 ከላይ በተቀመጠው ቀመር መሰረት

- መጀመሪያ ለ/ሐ የሚለውን እናያለን የዚህ ውጤት 0.95 (ዜሮ ነጥብ ዘጠኝ አምስት) ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ የተመዘገበው ሰው ባከናወነው ተቀናሽ የሚደረግ ግfh ላይ የከፈለው የግብአት ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ይደረጋል።
- ሁለተኛ የለ/ሐ ክፍልፋይ ውጤት 0.05 (ዜሮ ነጥብ ዜሮ አምስት) ወይም ከዚያ በታች ከሆነ የተመዘገበው ሰው ባከናወነው ተቀናሽ የሚደረግ ግ fh ላይ የከፈለው የግብአት ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ አይደረግም
- ሦስተኛ የለ/ሐ ክፍልፋይ ውጤት በ 0.05 (ዜሮ ነጥብ ዜሮ አምስት) እና በ 0.95 መካከል ከሆነ ግን ቀጥታ **ሀ*ለ/ሐ** ወደ ሚለው ቀመር የምንገባ ሲሆን በዚህ ስሌት መሰረት በመጣው ውጤት ልክ የተመዘገበው ሰው ባከናወነው ተቀናሽ የሚደረግ ግ fh ላይ የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ ይደረግለታል። በምሳሌውም መሰረት

ሀ=150,000 ብር፣ ለ=800,000 ብር፣ ሐ=1,000,000 ብር ቢሆን፤ በዚህ መሰረት፡-

1. ለ/ሐ 800,000/1000,000 0.8 ይህ ውጤት በ 0.05 እና በ 0.95 መካከል በመሆኑ ቀጥታ ወደ ሀ*ለ/ሐ ወደሚለው ቀመር እንሄዳለን፤ በዚህም መሰረት
2. ሀ*ለ/ሐ 150,000*800,000/1000,000 =120,000 ብር ሲሆን ይህ ገንዘብ የተመዘገበው ሰው ባከናወነው ተቀናሽ የሚደረግ ግ fh ላይ ለከፈለው ታክስ ተቀናሽ ይደረግለታል።

- የግብአት ታክስ ተቀናሽ የሚደረግበትን ጊዜ በተመለከተ ተቀናሽ የሚደረገው ግ fh አቅርቦት በተከናወነበት ወይም ወደ ሀገር በገባበት የሒሣብ ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት። ተቀናሽ እንዲሆን የተፈቀደ የግብአት ታክስ ያለው የተመዘገበ ሰው የአንድን የሒሣብ ጊዜ የገቢ ማስታወቂያ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰነዶች በእጁ ሊኖሩ ይገባል። ሰነዶቹ በእጁ የሌሉ ከሆነ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊደረግ የማይችል ስለሆነ ተቀናሽ የሚደረገው የተመዘገበው ሰው ሰነዱ

በእጁ የገባበት የመጀመሪያው የሒሣብ ጊዜ ይሆናል። በእጁ ሊኖሩ የሚገባቸው ተፈላጊ የሚሆኑት ሰነዶች፡-

- ወደ ሀገር ከገባ ዕቃ ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረግን ግfh በሚመለከት በኮሚሽኑ የተሰጠ የጉምሩክ ዲክላራሲዩን ወይም ወደ ሀገር በገባው ዕቃ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሌላ ሰነድ፣
- ታክስ ከሚከፈልበት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረግን ግ fh በሚመለከት ታክስ ከሚከፈልበት አቅርቦት ግ fh ጋር በተያያዘ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለበት የታክስ ደረሰኝ፣
- በቀጥታ በገዢው ታክስ ከሚከፈልበት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ተቀናሽ የሚደረግ ግ fh ን በሚመለከት የአገልግሎቱ ተቀባይ ያዘጋጀው የታክስ ደረሰኝ፣
- በብልጫ ለተከፈለ ታስ የክሬዲት ሰነድ እና በማነስ ለተከፈለ ታክስ ደግሞ የደቢት ሰነድ ማቅረብ ይጠበቅበታል። የአዋጁ አንቀጽ 29/6/መ.ሠ.ረ

በማናቸውም ምክንያት የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ተቀናሽ ሊደረግ የሚገባን የግብዓት ታክስ በዚያው የሒሣብ ጊዜ ባቀረበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ውስጥ ያልጠየቀ እንደሆነ በሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ በሚያቀርበው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሂሳብ ማስታወቂያ ውስጥ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም በዚህ ዓይነት የተቀናሽ ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው ተቀናሹ ሊጠየቅ ከሚገባበት የሒሣብ ጊዜ ጀምሮ ከ12 ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ነው።

## II. ተቀባይነት የሌለው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ

የተመዘገበ ሰው ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም።

- የተመዘገበው ሰው የመንገደኛ ተሽከርካሪ ግብይት ወይም ኪራይ ላይ የተሰማራ እና ተሽከርካሪው የተገዛው እና ፈቃድ የተሰጠው ለዚህ ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ ካልሆነ በስተቀር የመንገደኞች ተሽከርካሪ ግfh ወይም ከእነዚህ ተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ወይም ጥገና ወይም ዕድሳት ጋር በተያያዘ የከፈለው ታክስ፤ ይህ ግን፡-
    - በዋነኝነት ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ የንግድ ወይም ሌሎች የጭነት መኪናዎችን እና የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን አይመለከትም።

- የመንገደኛ ተሽከርካሪዎች ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ወይም ከትራንስፖርት ንግድ አገልግሎት ውጪ የዋሉ በሚሆንበት ጊዜ ለእነዚህ ተሽከርካሪዎች ለተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብዓት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም፡፡

- ከዚህ በታች ከተመለከቱት በስተቀር የተመዘገበው ሰው ለመዝናኛ ወይም የመዝናኛ አገልግሎት ለመስጠት ያከናወነው ግዢ ከሆነ፤

  - የመዝናኛው አገልግሎት የተሰጠው ማናቸውም ሰው ታክስ የሚከፈልበትን መደበኛ የመዝናኛ አገልግሎት በሚሰጥበት ሁኔታ ከሆነ እና የመዝናኛ አገልግሎቱ ግንኙነት ላለው ሰው ወይም ለሰራተኛ የተሰጠ ካልሆነ፤

  - የመዝናኛ አገልግሎቱ የተሰጠው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ስራውን ለማከናወን ወይም የቀጣሪውን ስራ ለማከናወን ከመኖሪያ ቤቱ ርቆ ባለበት ጊዜ ከሆነ ወይም

  - ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የትራንስፖርት አገልግሎትን የሚያካትት ሆኖ የመዝናኛው አገልግሎት የትራንስፖርቱ አካል ሆኖ ለመገደኞች የተሰጠ ከሆነ፤

    - ✓ መዝናኛ ማለት፡- ማናቸውም የምግብ፣ የመጠጥ፣ የመኝታ፣ የማዝናናት ወይም የመስተንግዶ አገልግሎት ነው፡፡

    - ✓ የመንገደኛ ተሽከርካሪ ማለት፡- ድርብ ጋቢና ያለውን ተሽከርካሪ ጨምሮ ከነአሽከርካሪው ስምንት ወይም ከዚያ በታች የሆኑ መንገደኞችን እንዲጭን ተደርጎ የተመረተ ወይም ማሻሻያ የተደረገበት ተሽከርካሪ ነው፡፡

- የተመዘገበው ሰው የአንድ ክበብ፣ ማህበር ወይም የስፖርት፣ የማህበራዊ ወይም የመዝናኛ ባህርይ ያለው ስብስብ አባል በመሆኑ ምክንያት የተፈጸመ ግ fh፡፡ ይሁን እንጅ ታክስ የሚከፈልበት የስፖርት፤ የማህበራዊ ወይም የመዝናኛ አቅርቦት የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው እነዚህን አገልግሎቶች ለመስጠት ላከናወነው ታክስ ተቀናሽ የሚደረግበት ግብይት የግብአት ታክስ ተቀናሽ የማግኘት መብቱን የሚያሳጣ አይሆንም፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የንግድ ሥራ ቦታ ሳይኖረው ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው ከሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ጋር በተያያዘ ማናቸውንም አይነት የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊያገኝ አይችልም።

III. አዲስ የተመዘገበ ሰው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ አዲስ የተመዘገበ ሰው በተመዘገበበት ቀን በእጁ በሚገኙ እና ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ለማከናወን በሚውሉ የንግድ ዕቃዎች ወይም የካፒታል ዕቃዎች ላይ የከፈለው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ እንዲደረግለት ለመጠየቅ ይችላል። ይህ ሊሆን የሚችለው፡-

- ➢ የተመዘገበው ሰው የንግድ ዕቃዎቹን ወይም የካፒታል ዕቃዎቹን ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባለው የመጨረሻ ቀን በእጁ የያዘ ከሆነ፣
- ➢ የተመዘገበው ሰው የንግድ ዕቃዎቹን ወይም የካፒታል ዕቃዎቹን ያገኘው ተቀናሽ በሚደረግ ግfh ከሆነ፣
- ➢ ተቀናሽ የሚደረገው ግfh የተፈጸመው፡-
  - ✓ የንግድ ዕቃዎችን በሚመለከት፡- ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባለው የ 6 ወር ጊዜ ውስጥ ከሆነ፣
  - ✓ የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት፡- ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባለው የ 3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሆነ እና
  - ✓ የተመዘገበው ሰው የታክሱን ባለስልጣን በሚያረካ አኳኋን ተቀናሽ ለሚደረገው ግ fh የግብአት ታክስ የከፈለ መሆኑን እና የከፈለውን ታክስ መጠን የሚያሳይ የታክስ ደረሰኝ ወይም ሌላ የሰነድ ማስረጃ ካቀረበ ነው።።

- የሚደረገው የግብአት ታክስ ተቀናሽ የተመዘገበው ሰው ከተመዘገበበት ቀን ቀጥሎ ባለው የመጀመሪያ የሂሳብ ጊዜ መቅረብ አለበት። የንግድ እቃዎችን በተመለከተ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክስ ተቀናሽ ማግኘት የሚችለው በተመዘገበበት ቀን በእጁ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎችን በገዛበት ጊዜ ለከፈለው የግብአት ታክስ ይሆናል። ነገርግን የተመዘገበው ሰው በተመዘገበበት ቀን በእጁ

የሚገኙ የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት ለተመዘገበው ሰው ተቀናሽ የሚያደረገው የግብአት ታክስ የሚሰላው በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሆናል፡-

**ሀ(ሐ-ለ)/ሐ**

ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፡-

- “ሀ” ማለት፡- የተመዘገበው ሰው የካፒታል ዕቃዎቹን በገዛበት ጊዜ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
- “ለ” ማለት፡- በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚወሰነው ይህ ሰው በተመዘገበበት ቀን የካፒታል ዕቃዎቹ ያላቸው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ እና
- “ሐ” ማለት፡- ለካፒታል ዕቃዎቹ የተደረገው የመጀመሪያው ወጪ።

አዲስ የተመዘገበ ሰው የግብዓት ታክስ ተቀናሽን በተመለከተ፡- ተቀናሽ እንዲሆን የተፈቀደ የግብአት ታክስ ያለው የተመዘገበ ሰው የአንድን የሒሣብ ጊዜ የገቢ ማስታወቂያ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ዝርዝር ሰነዶች በእጁ የሌለ ከሆነ፣ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊደረግ አይችልም የሚለው ተፈጻሚ አይደረግበትም። (የአዋጁ አ 29/5 ተፈጻሚ አይደረግበትም)

የታክስ ማቀናነስ በሚፈቀድለት ግዢ በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የሚፈጸመው የታክስ ማቀናነስ ሂደት የታክስ ማቀናነስ በሚፈቀድለት ግዢ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ በሚጀመርበት ወይም በሚቋረጥበት ቀን የሚከናወነውን የግብአት ታክስ ማቀናነስ አሰራር ከግምት ውስጥ ያሰገባ መሆን አለበት።

## IV. የተጨማሪ እሴት ታክስን የተጣራ ተከፋይ ሒሣብ ስለማስላት

በአንድ የሒሣብ ጊዜ የተጣራ ተከፋይ የሚሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ሊከፍል የሚገባው የተጣራ የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሰላል። **ሀ-ለ**

- ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፡-

“ሀ” ማለት፡- የሚከተሉት ድምር ይሆናል፡-

- ➢ በአንድ የሒሣብ ጊዜ የተመዘገበው ሰው ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ ተቀናሽ ሊደረግ የሚገባው ከተከፋይ ሒሣብ ላይ የሚቀነስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተቀነሰ በኋላ ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የሚሰበሰበው የውጤት ታክስ ጠቅላላ ድምር፣
- ➢ የተመዘገበው ሰው በሒሳብ ጊዜው በቀረበለት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ በቀጥታ ሊከፍል የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ ድምር፤
- ➢ በሂሳብ ጊዜው የተፈቀደ የተመዘገበው ሰው ወደ ሀገር ባስገባቸው የካፒታል እቃዎች ላይ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ፤
- ➢ በሒሳብ ጊዜው የተፈቀደ የተመዘገበው ሰው ወደ ሀገር ባስገባቸው የካፒታል ዕቃዎች ላይ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ።

"ለ" ማለት የሚከተሉት ድምር ይሆናል፡-

- ➢ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊደረግላቸው ለሚችል በሒሣብ ጊዜው የተመዘገበው ሰው ለገዛቸው ተቀናሽ የሚሆኑ ግ fh ዎች የከፈለው የግብአት ታክስ ጠቅላላ ድምር እና
- ➢ በአንድ የሒሣብ ጊዜ ለተመዘገበው ሰው ተቀናሽ እንዲሆን የተፈቀደ የግብዓት ታክስ።

## 5.2. ማስተካከያ ስለማድረግ

❖ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን በማነሱ ምክንያት የሚደረግ ማስተካከያ

- ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-
  - ➢ የተመዘገበ ሰው አቅርቦት ሲያከናውን፤
  - ➢ በአቅርቦቱ ላይ ማስተካከያ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር፤
  - ➢ ማስተካከያ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት የተመዘገበው ሰው በአቅርቦቱ ላይ ሊከፍል የሚገባው ትክክለኛው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ ለማድረግ ከተሰበሰበው የገንዘብ መጠን የበለጠ ጊዜ ነው።

- በተጨማሪነት የተሰበሰበው ታክስ ማስተካከያው በተደረገበት የሒሣብ ጊዜ የአቅራቢው የውጤት ታክስ ሆኖ ይወሰዳል። ይህም ተፈጻሚ የሚሆነው በተመዘገበ ሰው ላይ በሚሆንበት እና አቅራቢው ለገfhው ዋነኛውን የታክስ ደረሰኝ የሰጠ በሚሆንበት ጊዜ፦
  - ➢ አቅራቢው በአቅርቦቱ ላይ በተጨማሪነት የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያሳይ የዴቢት ሰነድ ለገfhው መስጠት አለበት፣
  - ➢ ተቀባይነት ለሌለው የግብዐት ታክስ ተቀናሽ ተፈጻሚ የማይደረግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ገfhው አቅርቦቱን ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት እስካዋለው ድረስ በዴቤት ሰነዱ ለተመለከተው በተጨማሪነት ለተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብአት ተቀናሽ ማግኘት ይፈቀድለታል፤
  - ➢ በተፈቀደው ተቀናሽ የግብዓት ታክስ የገንዘብ መጠን ልክ ገfhው የዴቢት ሰነዱን በተቀበለበት የሒሣብ ጊዜ የግብዓት ታክስ ተቀናሹን ማግኘት አለበት።

❖ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ በሙብዛቱ ምክንያት የሚደረግ ማስተካከያ

- ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-
  - ➢ የተመዘገበ ሰው አቅርቦት ሲያከናውን፣
  - ➢ በአቅርቦቱ ላይ ማስተካከያ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር፣
  - ➢ ማስተካከያ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት የተመዘገበው ሰው ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ለማድረግ የሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ትክክለኛው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚበልጥ ሆኖ ሲገኝ ነው። ይህም ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ አቅራቢው በብልጫ የከፈለው ታክስ ድርጊቱ በተፈፀመበት የሒሣብ ጊዜ ውስጥ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሆኖ ይያዛል። ይህ ተፈጻሚ የሚሆንበት ግfh ፈፃሚው የተመዘገበ ሰው በሚሆንበት እና አቅራቢው ለገfhው ዋነኛውን የታክስ ደረሰኝ የሰጠ በሚሆንበት ጊዜ፡-
  - ➢ አቅራቢው በአቅርቦቱ ላይ ተከፋይ ሊሆን የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የቀነሰበትን መጠን የሚያሳይ የክሬዲት ሰነድ ለገfhው መስጠት እና
  - ➢ አቅራቢው የቀነሰበትም የገንዘብ መጠን ገfhው የክሬዲት ሰነድ በተቀበለበት የሒሣብ ጊዜ የውጤት ታክስ ሆኖ መያዝ አለበት። ነገርግን ገዢው ያልተመዘገበ ሰው በሚሆንበት ጊዜ አቅራቢው ለገዢው በብልጫ የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በጥሬ ገንዘብ እስከሚመልስ ወይም ገfhው ለአቅራቢው ሊከፍል ለሚገባው ሌላ ሒሣብ ማካካሻ እስከሚያውል ድረስ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊያገኝ አይችልም።

- ሊሰበሰብ ለማይችል ዕዳ ስለሚደረግ ማስተካከያ

- ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡-

i. የተመዘገበው ሰው ባከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ ለታክሱ ባለስልጣን የውጤት ታክስ ገቢ አድርጐ ከሆነ፤

ii. ለአቅርቦቱ ሊከፈል የሚገባው ዋጋ በፋይናንስ ሪፖርት አዋጅ በተመለከተው የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃ መሰረት በሙሉ ወይም በከፊል በተመዘገበው ሰው የሒሣብ መግለጫ ውስጥ ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ ተብሎ የተያዘ ከሆነ፤

iii. ዕዳውን ለማስከፈል የሕግ እርምጃ የተወሰደ ቢሆንም ሊከፈል የማይችል ሆኖ ከተገኘ ነው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው የተመዘገበው ሰው ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ ነው ከተባለው አቅርቦት ጋር በተያያዘ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ባደረገው የውጤት ታክስ መጠን የግብአት ታክስ ተቀናሽ ያገኛል፡፡ የግብዓት ታክሱም ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው ከሚከተሉት በዘገየው ቀን ነው፡-

- ከላይ ከሮማን ቁጥር አንድ እስከ ሮማን ቁጥር ሦስት የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው በተገኙበት ቀን ወይም
- የተመዘገበው ሰው በአቅርቦቱ ላይ የሚከፈለውን የውጤት ታክስ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ካደረገበት የሂሳብ ጊዜ መጨረሻ ጀምሮ ከሚቆጠር የ 12 ወራት ጊዜ በኋላ፡፡

ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የገዛው ሰው (ባለዕዳው) የተመዘገበ ሰው ከሆነ እና የግብአት ታክስ ተቀናሽ በሚደረግበት ጊዜ ያለ ከሆነ የግብአት ታክስ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው አቅራቢው ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ ላይ የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያሳይ የክሬዲት ሰነድ የሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የክሬዲት ሰነድ የተሰጠው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ገfh በክሬዲት ሰነዱ ለተገለፀው የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብአት ታክስ ተቀናሽ የጠየቀ ከሆነ በክሬዲት ሰነዱ የተገለጸውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የክሬዲት ሰነዱ በተሰጠበት የሒሣብ ጊዜ ውስጥ በገfhው የሚከፈል የውጤት ታክስ እንደሆነ አድርጐ መያዝ አለበት፡፡

- መልሶ ሊሰበሰብ ከማይችል ዕዳ ውስጥ የተሰበሰበ ገንዘብ

(i) የተመዘገበ ሰው የግብአት ታክስ ተቀናሽ ያገኘበትን አቅርቦት ዋጋ በሙሉ ወይም በከፊል መልሶ የሰበሰበ እንደሆነ ሊሰበሰብ የማይችለውን ዕዳ መልሶ በሰበሰበበት የሒሣብ ጊዜ ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሠረት የውጤት ታክስ እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡

**ሀ x ለ/ሐ**

- ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፡-
  - “ሀ” ማለት፡- የተመዘገበው ሰው ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ ነው ከተባለው አቅርቦት ጋር በተያያዘ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ባደረገው የውጤት ታክስ መጠን የሚያገኘው የግብአት ታክስ ተቀናሽ መጠን፤
  - “ለ” ማለት፡- መልሶ የተሰበሰበው ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ፤
  - “ሐ” ማለት፡- ከሒሣብ መዝገብ የተሰረዘው ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ ነው፡፡

(ii) ከታች የሮማን ቁጥር ሦስት ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል፡-

ሀ) ሊሰበሰብ ለማይችል ዕዳ ስለሚደረግ ማስተካከያ፡- የሚለው ድንጋጌ ተፈጻሚ የተደረገው ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት ከሆነ (ከዚህ በኋላ <<ዋንኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት>>)፣

ለ) ቀጥሎም ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ ተፈጻሚ የሚሆነው የዋንኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት አቅራቢ ከዋንኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ገዢ በተቀበለው የገንዘብ መጠን ላይ ሲሆን እና

ሐ) የዋነኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ገዢ ዋነኛው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት በተከናወነበት ጊዜ እና በዚሁ ከላይ በፊደል (ለ) በተጠቀሰው መሠረት ሊሰበሰብ የማይችለው ዕዳ መልሶ በተሰበሰበበት ጊዜ የተመዘገበ ሰው ከሆነ፡፡

(iii) ከላይ በሮማንቁጥር ሁለት የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው የተገኙ ከሆነ፡-

ሀ) አቅራቢው ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ የተጠቀሰውን የውጤት ታክስ የገንዘብ መጠን በመግለጽ ለገዢው የዴቢት ሰነድ መስጠት ወይም

ለ) ገዢው የመጀመሪያውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት ያዋለው እና “ተቀባይነት የሌለው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ” ተፈጻሚ የማይደረግበት ከሆነ ከላይ በፊደል (ሀ) ለተገለጸው የውጤት ታክስ የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲያገኝ መደረግ አለበት፡፡

(iv) የተመዘገበው ሰው ከላይ በሮማን ቁጥር ሦስት ፊደል (ሀ) መሠረት የዴቢት ሰነድ በተቀበለበት የሒሣብ ጊዜ በሮማን ቁጥር ሦስት ፊደል (ለ) መሠረት የግብአት ታክስ ተቀናሽ ማግኘት አለበት፡፡

➢ <u>የሙከራ ጥያቄ፡-</u> የግብዓት ታክስ እና የውጤት ታክስ ልዩነታቸውን አብራራ?

## ክፍል ስድስት የተጨማሪ

## ዕሴት ታክስ ተመላሽ

<u>ተመላሽ = የግብዓት ታክስ ከውጤት ታክስ በልጦ ሲገኝ ነው</u>

### 6.1. በብልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ ወደፊት ስለማሸጋገር

- "የግብዓት ታክስ ከውጤት ታክስ ከበለጠ" ከግብዓት ታክስ ላይ የውጤት ታክስን በመቀነስ የተገኘው የገንዘብ መጠን ወደፊት እንዲሸጋገር ተደርጐ የሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክስ ሆኖ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
- በሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ ተቀናሽ ያልተደረገው በብልጫ የተገኘው ማናቸውም ሒሣብ ወደሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ እንዲሸጋገር ተደርጐ በዚያ የሒሣብ ጊዜ የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
- በዚህ መንገድ በብልጫ የተገኘው የግብአት ታክስ ተመላሽ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ እስከሚሆን ድረስ ወደሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ እንዲሸጋገር ይደረጋል፡፡
- የተመዘገበው ሰው በብልጫ የከፈለው እና ከአንድ የሒሣብ ጊዜ በላይ እንዲሸጋገር የተደረገ ሒሣብ ያለው እንደሆነ ቀደም ሲል እንዲሸጋገር የተደረገው በብልጫ የተከፈለው ሒሣብ በቅድሚያ እንዲቀነስ ይደረጋል፡፡
- የተመዘገበ ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ያለው በብልጫ የከፈለው ታክስ ለስድስት የሒሣብ ጊዜ ያህል የተሸጋገረ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ያልተደረገ ከሆነ የተመዘገበው ሰው የጸደቀ ቅጽን በመጠቀም ተቀናሽ ያላደረገው የገንዘብ መጠን ተመላሽ እንዲደረግለት ለታክሱ ባለሥልጣን ሊያመለክት ይችላል፡፡
- የታክሱ ባስለልጣን የቀረበውን የማመልከቻ ጥያቄ ተገቢ መሆን እና ያለመሆኑን አጣርቶ የተመላሽ ጥያቄ ማመልከቻው በቀረበለት በአርባ አምስት (45) ቀናት ውስጥ ተመላሹን ገንዘብ መክፈል አለበት፡፡

- የተመዘገበ ሰው የሚያቀርበው የተመላሽ ጥያቄ ስድስተኛው የሒሣብ ጊዜ በተጠናቀቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት። የተመዘገበው ሰው በዚሁ መሰረት ጥያቄውን ካላቀረበ ተመላሽ የማግኘት መብቱን እንደተወ ይቆጠራል።

### 6.1.1. ወደፊት ሳይሸጋገር ተመላሽ የሚደረግ በብልጫ የተከፈለ የግብዓት ታክስ

I. የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ካከናወነው አቅርቦት ዋጋ ውስጥ አምሳ በመቶ (50%) ወይም ከዚያ በላይ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግበት ከሆነ የተመዘገበው ሰው የሒሣብ ጊዜውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ካስታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የታክሱ ባለሥልጣን በሒሣብ ጊዜው በብልጫ የተከፈለውን የግብዓት ታክስ ተመላሽ ማድረግ አለበት።

II. ከታች የተገለጸው ሮማን ቁጥር ሦስት ተፈተጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፦

- ዓመታዊው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦቱ 100 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ የተመዘገበ ሰው ተቀናሽ የሚደረግ የካፒታል ዕቃዎች ግዢ የፈጸመ እንደሆነ፣
- የተመዘገበው ሰው ተቀናሽ ለሚደረገው የካፒታል ዕቃዎች ግዢ የግብዓት ታክስ ተቀናሽ የማግኘት መብት ያለው ከሆነ፣
- ተቀናሽ የሚደረገው ግfh በተከናወነበት የሒሣብ ጊዜ የግብዓት ታክሱ የገንዘብ መጠን ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ያልተደረገ ከሆነ።

III. ከላይ በሮማን ተራቁጥር ሁለት የተቀመጡት ተሟልተው ሲገኙ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው የካፒታል ዕቃው ለተገዛበት የሂሳብ ጊዜ ተመላሽ እንዲፈቀድለት ማመልከቻ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሹን መክፈል አለበት።

IV. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባው የተሰረዘበት ሰው ምዝገባው በተሰረዘበት እለት ያልተቀናነሰለት እና ለወደፊት እንዲሸጋገር የተደረገው የግብአት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ለታክሱ ባለስልጣን በጽሁፍ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል። ለዚህ ጉዳይ የሚቀርብ ማመልከቻ ታክስ ከፋዩ ለተመዘገበበት የመጨረሻ የሂሳብ ጊዜ የሂሳብ ማስታወቂያ ማቅረብ በሚገባው ጊዜ ውስጥ ወይም በታክሱ ባለሥልጣን በሚፈቀድ ሌላ ቀን ለታክሱ ባለሥልጣን መቅረብ አለበት።

V. የታክሱ ባለስልጣን ምዝገባው የተሰረዘ ሰው ከላይ በሮማን ቁጥር አራት ተቀናሽ ያልተደረገ የግብዓት ተመላሽ እንዲደረግለት ያቀረበው ማመልከቻ በበቂ ማስረጃ የተደገፈ ሆኖ ሲያገኘው ማመልከቻው በቀረበለት በ ስልሳ (60) ቀን ጊዜ ውስጥ ተመላሹን መክፈል አለበት።

VI. ምዝገባው በተሰረዘበት እለት ተቀናሽ ያልተደረገ የግብአት ታክስ ያለው ሰው ተቀናሽ ያልተደረገው የግብአት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ከላይ በሮማን ቁጥር አራት መሠረት ማመልከቻ ያላቀረበ እንደሆነ መብቱ የሚቋረጥ ሲሆን ተቀናሽ ያልተደረገው የግብአት ታክስ ተመላሽ ሊደረግለት አይችልም።

## 6.2. ዘግይቶ በተከፈለ የተመላሽ ሒሳብ ላይ ስለሚከፈል ወለድ

I. የታክሱ ባለሥልጣን የተመላሹን ሒሣብ መክፈል በነበረበት ጊዜ ያልከፈለ ከሆነ የተመላሹ ሒሣብ መክፈል ከነበረበት አግባብነት ካለው ጊዜ መጨረሻ ጀምሮ ተመላሹ ሒሣብ እስከተከፈለ ድረስ ላለው ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን ወለድ መክፈል አለበት።

II. የሚከፈለው ወለድ መጣኔ ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ ከተመለከተው ጊዜ በፊት ባለው የሩብ ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ባንኮች የንግድ ብድር የሚሰጡበት ከፍተኛው የወለድ መጣኔ ይሆናል።

## 6.3. ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፣ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ለኢንቨስተሮች የሚከፈል ተመላሽ ሒሣብ

i. የታክሱ ባለሥልጣን የሚቀርብለትን ጥያቄ መሠረት በማድረግ የሚከተሉት አካላት የከፈሉትን የተጨማሪ እሴት ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል ተገቢው ማስረጃ ተሟልቶ በቀረበበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ማድረግ አለበት፡-

✓ በቪዬና የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ኮንቬንሽን ለሚሲዮን፣ ለዲፕሎማት ወይም ለቆንስላ የሚፈጸም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ እስከሆነ ድረስ ለውጭ ሀገር የዲፕሎማቲክ ወይም ለኮንስላር ሚሲዮኖች ወይም ለውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች እና ቆንስላዎች፤

✓ በዓለም አቀፍ ስምምነት ለዓለም አቀፍ ድርጅቱ የሚፈጸም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ እስከሆነ ድረስ ለዓለም አቀፍ ድርጅት፤

- ✓ የውጭ ሀገር መንግሥት በፋይናንስ፣ በቴክኒክ፣ በሰብአዊ ዕርዳታ ወይም አስተዳደራዊ ድጋፍን በሚመለከት ዓለም አቀፍ ስምምነት ለውጭ ሀገር መንግስት የሚፈጸም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የተደረገ ከሆነ ወይም
- ✓ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ህግ መሰረት ለኢንቨስተር የሚፈጸም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የተደረገ ወይም ታክሱ ተመላሽ እንዲደረግ የተፈቀደ ከሆነ፤

➢ ለኢትዮጵያ ዜጎች ወይም በኢትዮጵያ ቋሚ ነዋሪ ለሆኑ ሰዎች ተመላሽ ማድረግ አይቻልም።

➢ የታክሱ ባለስልጣን የተመላሽ ሒሣብን የሚከፍለው እንደአግባብነቱ በሁኔታ ወይም በገደብ ሊሆን ይችላል።

➢ ከላይ በ 6.3. ሮማን ቁጥር አንድ መሰረት የሚቀርበው የተመላሽ ጥያቄ፡-

- ✓ የተመላሽ ጥያቄ የቀረበበት አቅርቦት ከተከናወነበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወይም የታክሱ ባለስልጣን በሚፈቅደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም መቅረብ እና
- ✓ ከሚከተሉት ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-
  - የተመላሽ ጥያቄ የቀረበበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተከፈለበት የታክስ ደረሰኝ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማስረጃ፣
  - አመልካቹ የተመላሽ ጥያቄ እንዲያቀርብ የሚያስችለው ማስረጃ እና
  - የታክሱ ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ የሚጠየቀውን ማናቸውም ሌላ ማስረጃ።

- <u>አጠቃላይ ተመላሽን በተመለከተ፡-</u>

➢ የተመዘገበው ሰው ተመላሽ ሊከፈለው በሚገባ ጊዜ በማናቸውም የሂሳብ ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማስታወቅ ግዴታውን ያልተወጣ ሆኖ ከተገኘ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳያስታውቅ ለቆየበት የሂሳብ ጊዜ ሁሉ የማስታወቅ ግዴታውን እስከሚወጣ ድረስ ተመላሹ ገንዘብ ሳይከፈለው እንዲቆይ ሊደርግ ይችላል።

➢ የታክሱ ባለሥልጣን የተመላሽ ገንዘብ አከፋፈልን የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

➢ ለተመላሽ ስለሚያዝ ገንዘብ የታክሱ ባለሥልጣን ለተመላሽ ክፍያ እንዲያውለው ከጠቅላላ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተሰብሳቢ ገንዘብ ላይ በታክሱ ባለሥልጣን ተቀናሽ ተደርጎ የሚያዘው መቶኛ መጠን የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

<u>የሙከራ ጥያቄ</u>

➢ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የተመላሽ ስርአትን አብራራ?

## ክፍል ሰባት የተጨማሪ
## እሴት ታክስ ሰነዶች

### 7.1. የታክስ ደረሰኞች

ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው አቅርቦቱን ባከናወነበት ጊዜ አቅርቦቱን ለገዛው ሰው መደበኛውን የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት፡፡ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የገዛው ሰው ካልጠየቀ በስተቀር የተመዘገበ ሰው የአቅርቦቱ ጠቅላላ ዋጋ ከ10,000 ብር ላልበለጠ እና በጥሬ ገንዘብ ለሚፈጸም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ክፍያ መደበኛውን የታክስ ደረሰኝ እንዲሰጥ አይገደድም፡፡

- ለሚከተሉት ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የተመዘገበው ሰው በቀላል መንገድ የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ ሊሰጥ ይችላል፡-

  ➢ የአቅርቦቱ ጠቅላላ ዋጋ ከብር 10,000 ላልበለጠ እና በጥሬ ገንዘብ ለሚፈጸም ክፍያ፣

  ➢ አቅርቦቱ የተከናወነው በችርቻሮ ንግድ ሥራ ላይ በተሠማራ የተመዘገበ ሰው ከሆነ፡፡

- በቀጥታ በገዢው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት የተመዘገበ ሰው አገልግሎቱን ባገኘበት ጊዜ ለአቅርቦቱ በገ fh ው የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ ማዘጋጀት አለበት፡፡

### 7.1.1. የታክስ ደረሰኝ ይዘት

I. የታክስ ደረሰኝ በቀላል መንገድ የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ እና በገfhው የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዙ ይገባል፦

➢ ግልጽ በሆነ ቦታ “ የታክስ ደረሰኝ “ የሚል ጽሁፍ፤

➢ የአቅራቢው ስም፣አድራሻ፣የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

➢ የአቅርቦቱ ተቀባይ ስም፣አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

➢ የታክስ ደረሰኙ መለያ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን፤

➢ ሰለእቃው መግለጫ (ብዛቱን እና መጠኑን ጨምሮ) ወይም የተሰጠውን አገልግሎት እና

➢ ለአቅርቦቱ የተከፈለውን ዋጋ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

II. የተመዘገበው ሰው አቅርቦቱን የሚፈጽመው በመሳሪያ፣ በቆጣሪ ወይም በሌላ በሳንቲም፣ በገንዘብ ወካይ ነገር ወይም በዴቢት ወም ክሬዲት ካርድ ከሆነ መሳሪያው፣ ቆጣሪው ወይም ገንዘብ መቀበያው ማሽን ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ ቀለል ያለ ደረሰኝ ለአቅርቦቱ ተቀባይ መስጠት አለበት። ነገርግን መሳሪያው፣ ቆጣሪ ወይም ገንዘብ መቀበያ ማሽን የታክስ ደረሰኝ ለመስጠት የማይችል ከሆነ፡-

➢ የተመዘገበው ሰው በየቀኑ በመሳሪያው፣ በቆጣሪው ወይም በገንዘብ መቀበያው ማሽን የተከናወነውን ግብይት የሚያሳይ ከላይ ያሉትን ዝርዝር መረጃ በመያዝ በየቀኑ መጨረሻ የታክስ ደረሰኝ መቁረጥ አለበት።

➢ በአቅርቦት ተቀባዩ የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

✓ በሚታይ ቦታ ላይ “በአቅርቦት ተቀባይ የተዘጋጀ የታክስ ደረሰኝ” የሚል ጽሁፍ፣

✓ በአቅርቦት ተቀባዩ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ተቀባይ ስም፣አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤

- ✓ የአቅራቢው ስም እና አድራሻ፤
- ✓ በአቅርቦት ተቀባዩ የተዘጋጀው የታክስ ደረሰኝ መለያ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን፤
- ✓ የተሰጠው አገልግሎት መግለጫ እና
- ✓ ለአቅርቦቱ የተከፈለው ዋጋ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

## 7.2. የክሬዲት እና የዴቢት ሰነዶች

የተጨማሪዕሴት ታክስ ማስተካከያ ጋር ተያይዞ ያሉት ሁኔታዎች በሚሟሉበት ጊዜ የተመዘገበው ሰው ለሌላው የተመዘገበ ሰው እንደሁኔታው የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ መስጠት አለበት። የተመዘገበው ሰው ለአቅርቦቱ ገዢ የክሬዲት ወይም የዴቢት ሰነድ የሚሰጠው ሰነዱ እንዲሰጥ ምክንያት የሆነው የማስተካከያ ተግባር በተፈጸመበት የሒሣብ ጊዜ መጨረሻ ሊሆን ይገባል። "የማስተካከያ ተግባር" የሚለው ሐረግ የማይሰበሰብ ዕዳ በመኖሩ ምክንያት የሚደረግን ማስተካከያ ይጨምራል።

### 7.2.1. የክሬዲት ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፦

- ➢ በሚታይ ቦታ ላይ "የክሬዲት ሰነድ" የሚል ጽሁፍ፤
- ➢ የአቅራቢው ስም፣አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤
- ➢ የአቅርቦቱ ተቀባይ ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤
- ➢ የክሪዲት ሰነዱ መለያ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን፣
- ➢ ክሬዲት ሰነዱ የተሰጠበትን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ለይቶ ማወቅ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መረጃን ጨምሮ የክሬዲት ሰነድ ለመስጠት ምክንያት የሆነውን የሚያስረዳ አጭር መግለጫ እና
- ➢ በታክስ ደረሰኙ የተመለከተው የአቅርቦቱ ዋጋ፣ ትክክለኛው የአቅርቦቱ ዋጋ፣ በእነዚህ ሁለት ዋጋዎች መካከል ያለው ልዩነት እና በልዩነቱ ላይ የሚታሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን፤

### 7.2.2. የደቢት ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፦

- ➢ በሚታይ ቦታ ላይ "የዴቢት ሰነድ" የሚል ጽሁፍ፤

- የአቅራቢው ስም፣አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤
- የአቅርቦቱ ተቀባይ ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተመዘገበ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤
- የዴቢት ሰነዱ መለያ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን፤
- ዴቢት ሰነዱ የተሰጠበትን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ለይቶ ማወቅ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መረጃን ጨምሮ የዴቢት ሰነድ ለመስጠት ምክንያት የሆነውን የሚያስረዳ አጭር መግለጫ እና
- በታክስ ደረሰኙ የተመለከተው የአቅርቦቱ ዋጋ፣ ትክክለኛው የአቅርቦቱ ዋጋ፣ በእነዚህ ሁለት ዋጋዎች መካከል ያለው ልዩነት እና በልዩነቱ ላይ የሚታሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን፤

## 7.3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነድ እንዲሰጥ ስለመጠየቅ

- በማናቸውም ምክንያት ዋንኛው የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ ያልተሰጠው የተመዘገበ ሰው አቅራቢው የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ እንዲሰጠው በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል። የሚቀርበው ጥያቄ፡-
  - የታክስ ደረሰኝን በሚመለከት የታክሱ ደረሰኝ እንዲሰጥ ምክንያት የሆነው አቅርቦት ከተከናወነበት ቀን አንስቶ በ 60 ቀናት ውስጥ ወይም
  - የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድን በሚመለከት የክሬዲት ሰነዱ ወይም የዴቢት ሰነዱ እንዲሰጥ ምክንያት የሆነው ሁኔታ ካጋጠመበት ቀን ጀምሮ በ 60 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት። በዚህ መሠረት ጥያቄ የቀረበለት የተመዘገበ ሰው ጥያቄው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በ 14 ቀናት ውስጥ በጥያቄው መሠረት መፈጸም አለበት።
- የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የተከናወነበት ዋንኛ የታክስ ደረሰኝ ወይም ማስተካከያ የተደረገበት የክሬዲት ወይም የዴቢት ሰነድ ዋንኛ ቅጂ የጠፋበት መሆኑን የገለጸ ከሆነ አቅርቦቱን ያከናወነው የተመዘገበው ሰው የዋንኛውን የታክስ ደረሰኝ ወይም የክሬዲት ሰነዱን ወይም የዴቢት ሰነዱን ቅጂ ሊሰጠው ይችላል። ለተመዘገበው ሰው የሚሰጠው የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ ቅጂ በላዩ ላይ ቅጂ በሚል ሊጻፍበት ይገባል።

## 7.4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች አያያዝ

- የተመዘገበ ሰው ለአንድ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ሊሰጥ የሚችለው አንድ ደረሰኝ ብቻ ሲሆን ማስተካከያ ማድረግ ለሚያስገድድ አንድ ሁኔታ ሊሰጥ የሚችለው አንድ የክሬዲት ሰነድ ወይም አንድ የዴቤት ሰነድ ነው። ሆኖም ዋነኛው ቅጂ ጠፍቶብኛል ለሚል የተመዘገበ ሰው ቅጂ የሚል ጽሑፍ የሰፈረበት ቅጂ ሊሰጠው ይችላል።
- የተመዘገበ ሰው ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ ውጪ የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ ሊሰጥ አይችልም።
- ለተጨማሪ ዕሴት ታስ እና ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም የተመዘገበ ሰው የሚከተሉትን ሰነዶች መያዝ አለበት።
  - ➢ የተቀበላቸውን ዋንኛ የታክስ ደረሰኞች፣ የክሬዲት ሰነዶች እና የዴቢት ሰነዶች በሙሉ፣
  - ➢ የተቀበላቸውን የታክስ ደረሰኞች፣ የክሬዲት ሰነዶች እና የዴቤት ሰነዶች ቅጂዎች በሙሉ፣
  - ➢ የሰጣቸውን የታክስ ደረሰኞች፣ የክሬዲት ሰነዶች እና የዴቢት ሰነዶች ቅጂዎች በሙሉ፤
  - ➢ ወደ ሀገር ካስገባቸው ወይም ወደ ውጭ ከላካቸው ዕቃዎች ጋር የተያያዙ የጉምሩክ ሰነዶች እና
  - ➢ የአገልግሎቱ ተቀባይ በሆነ የተመዘገበ ሰው የተዘጋጁ ከሆነ ይህ ሰው በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚመለከቱ የታክስ ደረሰኞች።
- የሰጣቸውን የታክስ ደረሰኞች፣ የክሬዲት ሰነዶች እና የዴቢት ሰነዶች ቅጂዎች በሙሉ በቅደም ተከተላቸው መሠረት መያዝ አለባቸው።

## 7.5. በወኪሎች አማካኝነት የተከናወኑ አቅርቦቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶች

- ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የተከናወነው በተመዘገበው ወካይ ስም በተወካዩ አማካኝነት የሆነ እንደሆነ እና ወካይ እና ተወካይ ሁለቱም የተመዘገቡ ሰዎች ከሆኑ ወካዩ ለአቅርቦቱ ሊሰጥ የሚገባውን ማናቸውንም የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ ተወካዩ የወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር በመጠቀም መስጠት ይችላል።

- የተመዘገበ ሰው በተወካዩ አማካኝነት ለወካዩ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነ እና ወካይ እና ተወካይ ሁለቱም የተመዘገቡ ከሆነ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ ለወካዩ ሊሰጥ የሚገባውን የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ እና የዴቢት ሰነድ የተወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር በመጠቀም ለተወካዩ መስጠት ይችላል።
- ተወካይ በተመዘገበ ወካይ ስም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነ እንደሆነ እና ወካዩ የተመዘገበ ሰው ሆኖ ተወካዩ ያልተመዘገበ ከሆነ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ በወካዩ ሊሰጥ የሚገባውን የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ እና የዴቢት ሰነድ የወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር በመጠቀም ተወካዩ ሊሰጥ ይችላል።
- የተመዘገበ ሰው ለወካዩ በተወካዩ አማካኝነት ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነ እንደሆነ እና ወካዩ የተመዘገበ ሰው ሆኖ ተወካዩ ያልተመዘገበ ከሆነ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ ለወካዩ ሊሰጥ የሚገባው የታክስ ደረሰኝ የወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ቁጥር በመጠቀም ለተወካዩ መስጠት ይችላል።
- ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት በወካዩ ስም ለተወካዩ የቀረበ ወይም በወካዩ ስም በተወካዩ የቀረበ እንደሆነ ከአቅርቦቱ ጋር በተያያዘ ሊሰጥ የሚገባው የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ አንድ ጊዜ ብቻ መሰጠት ያለበት ሲሆን ለወካዩ እና ለተወካዩ ወይም በወካዩ እና ለተወካዩ ሊሰጥ አይችልም። በዚህ መሠረት በተወካዩ የተሰጠ ወይም ለተወካዩ የተሰጠ የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ እና የዴቢት ሰነድ በወካዩ እና ለተወካዩ እንደተሰጠ ይቆጠራል።
- በወካዩ ወይም ለተወካዩ የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት ሰነድ ወይም የዴቢት ሰነድ የተሰጠ እንደሆነ ተወካዩ የወካዩን ስም፣ አድራሻ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር ማረጋገጥ የሚያስችል በቂ መረጃ መያዝ አለበት።

## 7.6. የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶችን

- የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ ለሚያቀርባቸው ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች የታክስ ደረሰኝ መስጠት የለበትም። ሆኖም የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት፦
  - ➢ ለኢንቮይሱ ወይም ለደረሰኙ በተለይ የተሰጠ ቁጥር፤
  - ➢ የውጭ አቅራቢውን ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ምዝገባ ቁጥር፤

➢ የአቅርቦቱን ተቀባይ ስም እና አድራሻ፤

➢ አቅርቦቱ የተፈጸመበትን ቀን፤

➢ የእቃዎቹን እና ከሩቅ የተሰጡትን አቅርቦቶች መግለጫ እና

➢ ለአቅርቦቱ የተከፈለውን ዋጋ እና የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ።

- የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነዶችን በውጭ አገር ሊይዝ የሚችል ሲሆን በታክሱ ባለስልጣን በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ በሚወሰን ቀን እነዚህን ሰነዶች እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ ማቅረብ አለበት።

<u>የሙከራ ጥያቄ፡-</u> የክሬዲት እና የዴቢት ሰነዶች ልዩነታቸውን አብራራ

## ክፍል ስምንት በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ስለመጠቀም

### 8.1. የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ

- “የኢሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ” ማለት የሽያጭ እና ተያያ fh ነት ያለውን መረጃ ለመመዝገብ እና ለማስተለለፍ የሚያግዝ የኢሌክትሮኒክ መሳሪያ ነው።
- የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ የሚጠቀምበት ሶፍትዌር በታክሱ ባለስልጣን የተፈቀደ መሆን ያለበት ሲሆን የተመዘገበው ሰው የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያን ጥቅም ላይ ከማዋሉ 7 (ሰባት) ቀን በፊት በእያንዳንዱ የንግድ ስራው ቦታ የሚጠቀምበትን መሳሪያ እና ሶፍትዌር ዝርዝር ባህሪያት ለታክሱ ባለስልጣን በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት።
- የታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቂያው በደረሰው በሰባት (7) ቀናት ውስጥ ሶፍትዌሩ ከታክስ ህጉ ጋር የሚጣጣም መሆኑን የሚገልፅ ማረጋገጫ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት።
- የኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ጥቅም ላይ ከመዋሉ ከሰባት ቀን በፊት የተመለከተውን ማስታወቂያ ለታክስ ባለስልጣኑ የሚያቀርበው የተመዘገበ ሰው በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያው ለመጠቀም የተመዘገበ ሰው መሆን አለበት።
- የተመዘገበ ሰው በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ መሰረት በእያንዳንዱ የንግድ ስራ በሚያከናውንበት ቦታ በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ መጠቀም አለበት።

## 8.2. የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ ተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር

- የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፦

➢ ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረብ ጋር ግንኙነት ሊኖረው የሚችል መሆን አለበት፤

➢ መረጃዎችን በበቂ ሁኔታ መያዝ የሚያስችል ማከማቻ ሊኖረው ይገባል፤

➢ በታክስ ህግ መሰረት የስራ ቋንቋ መለከቶችን ማሳየት የሚችል መሆን አለበት፤

➢ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በቀላሉ ሊለወጥ እና ጉዳት ሊደርስበት የማይችል ሊሆን ይገባል፤

➢ የሚከተሉትን የሚያከናውን ሊሆን ይገባል:-

✓ ለደንበኞች የኤሌክትሮኒክ የታክስ ደረሰኞችን ማተም ወይም የኤሌክትሮኒክ የታክስ ደረሰኞችን ማስተላለፍ የሚችል፤

✓ ከታክስ ባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርአት ጋር መጣጣም የሚችል፤

✓ በውስጡ የተመዘገበውን መረጃ ለታክሱ ባለስልጣን ማስተላለፍ የሚችል ወይም ከታክሱ ባለስልጣን መሳሪያ ጋር መገናኘት የሚችል፤

✓ በታክስ ህጎች ላይ የሚደረገውን ለውጥ ተከትሎ ወቅታዊ ሊደረግ የሚችል፤

✓ በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደንብ ላይ የተዘረዘሩ መረጃዎችን መያዝ የሚችል።

## 8.3. የተመዘገበ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ተጠቃሚ ግዴታ

➢ እያንዳንዱን የሚፈጽመውን ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያን በመጠቀም መመዝገብ አለበት፤

➢ ለእያንዳንዱ ለሚፈጽመው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያን በመጠቀም የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት፤

➢ የሚሰጠው የታክስ ደረሰኝ በዚህ ሰነድ ክፍል ስምንት (8.2) ላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ መሆን አለበት፤

➢ በአንድ ግብይት ከአንድ በላይ የሆኑ እቃዎች እና አገልግሎቶች አቅርቦት የሚፈጸም ከሆነ አቅርቦቱ የሚያካትታቸውን እቃዎች እና አገልግሎቶች በመዘርዘር አንድ ደረሰኝ ብቻ መስጠት ይቻላል።

➢ ይህ ተፈጻሚ በሚሆንበት ሁኔታ የተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፈልባቸው በዝርዝሩ ወስጥ የተካተቱ እቃዎች በደረሰኙ ውስጥ ተለይተው መታየት አለባቸው።

➢ የተመዘገበ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ተጠቃሚ፦

✓ ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦቱ ተቀባዩ የኤሌክትሮኒክ የታክስ ደረሰኝ መስጠት ወይም ማስተላለፍ እና

✓ የኢሌክትሮኒክ የታክስ ደረሰኙን ለታክሱ ባላስልጣን መላክ ወይ ማስተላለፍ አለበት።

✓ በኤሌክትሮኒክ የፊሲካል መሳሪያ መጠቀም የሚችለው በመሳሪያው ለመጠቀም የተመዘገበ ተጠቃሚ ብቻ ሲሆን የገቢዎች ሚኒስቴር በኤሌክትሮኒክስ የፊስካል መሣሪያ ለመጠቀም የሚመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ሊከተሉት የሚገባውን ስርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

## 8.4. በኢሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ መገልገል አለመቻል

- የተመዘገበ ተጠቃሚ በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያው የኤሌክትሪክ አቅርቦት በሌለ ጊዜም ያለማቋረጥ መጠቀም እንዲችል ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ አለበት።
- የተመዘገበው ተጠቃሚ በማናቸውም ምክንያት በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያው መጠቀም ያልቻለ እንደሆነ፦

➢ በመሳሪያው መጠቀም እንዳይችል ያደረገው ሁኔታ በተፈጠረ በ24 ሰአት ውስጥ ይህንኑ ለታክሱ ባላስልጣን ማስታወቅ አለበት፤

➢ በመሳሪያው መጠቀም ባልቻለበት ጊዜ ውስጥ ያከናወነውን አቅርቦት በማናቸውም ሌላ ዘዴ መመዝገብ  እና በማናቸውም ሌላ ዘዴ መሰረት ያከናወነውን አቅርቦት በዝርዝር በመሳሪያው ውስጥ መመዝገብ እና ማስገባት አለበት

- ➢ በመሳሪያው መጠቀም ባልቻለበት ጊዜ ውስጥ ላከናወነው ግብይት ለአቅርቦቱ ተቀባይ የገቢዎች ሚኒስቴር በመረጠው የማተሚያ ድርጅት የታተመ በእጅ የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

## 8.5. የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ ዝግጁነት

- የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ የተመዘገበ ተጠቃሚ፦

- ➢ የሽያጭ ተግባር በሚያከናውንባቸው ቦታዎች ሁሉ የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ እንዲኖር ማድረግ፤
- ➢ የኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያዎችን ለመቆጣጠር የተመደቡ ሰራተኞች ስራቸውን እንዲያከናውኑ ማገዝ፤
- ➢ መሳሪያው ሁልጊዜም ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆን ወቅታዊ የሆነ እድሳት እንዲደረግለት ማድረግ፤
- ➢ የተመዘገበው ተጠቃሚ ለሚጠቀምበት የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ የተደረገውን እድሳት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ የሚያሳይ መዝገብ ማቋቋም እና ጠብቆ ማቆየት፦
  - ✓ የመሳሪያውን እድሳት ስራ ያከናወነውን ሰው ስም እና አድራሻ እና
  - ✓ የመሳሪያውን እድሳት ስራ ባከናወነው ሰው ፊርማ የተረጋገጠ በእያንዳንዱ እድሳት በተደርገበት ጊዜ የተከናወነውን እድሳት የሚያሳይ ዝርዝር፤
- ➢ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዘሩ ሌሎች ተፈላጊ ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት።
- ➢ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያውን እድሳት የሚያከናውነው ሰው የመስሪያውን አሰራር ለመለወጥ የተከናወነ ተግባር መኖሩን ሲደርስበት ይህንኑ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።

## 8.6. በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ መጠቀምን ስለማቋረጥ

- የተመዘገበ ሰው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች በኤሌክትሮኒክ ፍስካል መሳሪያ መጠቀምን ማቋረጥ ከፈለገ ይህንኑ ለታክሱ ባላስልጣን ማስታወቅ አለበት፦

- ➢ የተጠቃሚው የንግድ ስራ ከተዘጋ፤

➢ ታክስ የሚከፈልባቸውን አቅርቦቶች ማከናወን ካቆመ፤

➢ ሌሎች ምክንያቶች ካሉ፤

- በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ መጠቀምን ለማቋረጥ የሚቀርበው ማስታወቂያ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም ከኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ መጠቀም ከመቋረጡ ከ 30 ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን መቅረብ አለበት።
- የታክሱ ባለስልጣንም ማስታወቂያ በቀረበ በ21 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያውን አገልግሎት ማቋረጥ አለበት።
- የታክሱ ባለስልጣን በ21 ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ በመሳሪያው መጠቀም እንደተቋረጠ ይቆጠራል።

## 8.7. በኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ የሚዘጋጅ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰነድ

- በኤሌክትሮኒክ የፊስካል መሳሪያ የሚዘጋጅ የኤሌክትሮኒክ የታክስ ደረሰኝ የግሬዲት ኖት እና የዴቢት ኖት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

➢ እንደሁኔታው በዚህ ሰነድ ክፍል ስምንት ላይ በ 8.2 የተዘረዘሩትን መረጃዎች፤

➢ የመሳሪያውን የተለየ መለያ፤

➢ እንደአግባብነቱ የታክስ ደረሰኙን፣ የክሬዲት ኖቱን ወይም የዴቢት ኖቱን የተለየ መለያ፤

➢ የፈጣን ምላሽ ( ፈም) ኮድ እና

➢ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዝራቸው ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፤

## 8.8. የመረጃ ደህንነት እና መረጃን ስለማስተላለፍ

- የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ የሚተገብራቸው ዋናዋና ተግባራት

➢ የታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት እና የዴቢት ኖት መረጃዎችን እንዲሁም የየእለቱን መጨረሻ የማጠቃለያ መረጃ የታክስ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሰረት ወደታክስ ባለስልጣኑ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርአት ማስተላለፍ፤

- በውስጡ የተከማቸውን መረጃ ማተም እና መስጠት፤
- በውስጡ የያዘውን መረጃ ለማየት ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ሊረዱት በማይችል አኳኋን መረጃን በውስጡ ማከማቸት፤
- በውስጡ ያለው መረጃ አስተማማኝ መሆን፤
- የተፈቀደላቸውን ሰዎች ማንነት ማረጋገጥ የሚችል፤
- በመሳሪያው የተከናወኑ ተግባራትን በሙሉ መዝግቦ የሚያዝ፤
- ለእያንዳንዱ የታክስ ደረሰኝ የተለየ መለያ መስጠት የሚችል፡፡

| |
|---|
| ከላይ በክፍል ስምንት (8) ስር የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ተላልፎ የተገኘ ሰው በተላለፈው በዕያንዳንዱ ድንጋጌ ልክ 100,000 ሺ ብር አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፡፡<br><br>የኤሌክትሮኒክ የፊዚካል መሳሪያ በትክክል እንዳይሰራ ለማድረግ የነካካ፣ያመቻቸ ወይም በአሰራሩ ጣልቃ የገባ ማናቸውም ሰው በወንጀል ተጠያቂ ከመሆኑም በተጨማሪ 200,000 ሺብር አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፡፡ |

የሙከራ ጥያቄ፡-

- የተመዘገበ የኤሌክትሮኒክ ፊስካል መሳሪያ ተጠቃሚ ግዴታዎችን አብራራ?

## ክፍል ዘጠኝ የተጨማሪ
## ዕሴት ታክስ ስረዛ

### 9.1. የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ ሲያቆም ስለሚሰጥ ማስታወቂያ

- የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ማከናወኑን ሲያቆም ይህንኑ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡
- የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው ምዝገባው ከጸናበት ቀን አንስቶ ለተከታታይ ለስድስት (6) ወር ምንም አይነት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ያለማከናወኑን ካረጋገጠ ምዝገባው ከጸናበት ቀን አንስቶ

እንዲሰረዝ ሊወሰን ይችላል። ሆኖም የታክስ ከፋዩ ምዝገባ መሰረዝ ግዴታውን ባለመወጣቱ በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት የሚጣልበትን መቀጫ የሚያስቀር አይሆንም።

- የታክስ ከፋዩ ምዝገባ ከተሰረዘ በኋላ ያላስታወቀውና ያልከፈለው የታክስ ዕዳ መኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ የታክሱ ባለስልጣን በማናቸውም ግዜ ታክሱን ከነመቀጫው ለመጠየቅ ይችላል።
- የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ ሲያቆም የሚሰጠው ማስታወቂያ፡-
  - ➢ በተፈቀደው ቅጽ በመጠቀም የሚቀርብ፤
  - ➢ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወን ያቆመበትን ቀን፤
  - ➢ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወን ካቆመበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 12 ወራት ውስጥ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ለማከናወን ፍላጐት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን እና የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ካቆመበት ቀን አንስቶ በ 7 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።
- የታክሱ ባለስልጣን ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወኑን ያቆመን የተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሚቀርብለትን ማስታወቂያ መሠረት በማድረግ ወይም በራሱ አነሳሽነት ለተመዘገበው ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ለመሠረዝ ይችላል።
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀትን ለመሠረዝ የተሰጠ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወን ካቆመበት የሒሣብ ጊዜ የመጨረሻ ቀን ወይም በስረዛው ውሳኔ ማስታወቂያ ከተገለፀው ቀን ጀምሮ ይሆናል።

## 9.1. ምዝገባን ስለማገድ

- ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የማከናወኑን ተግባር በጊዜያዊነት ያቋረጠ የተመዘገበ ሰው የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም ምዝገባው ለ 12 (አስራሁለት) ወራት እንዲታገድለት ሊያመለክት ይችላል።
- የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወኑን ካቆመበት ቀን አንስቶ በ12 ወራት ጊዜ መልሶ የሚጀምር መሆኑን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ካገኘ ምዝገባውን በመሰረዝ ፈንታ የተመዘገበውን ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የማገድ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባው የታገደበት ሰው ምዝገባው በታገደበት ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን መፈጸም የለብትም:-

- ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት መፈጸም፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ፣ የክሬዲት እና የዴቢት ሰነድ መቁረጥ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እዲሰጠው ወይም የግብአት ተመላሽ እንዲፈቀድለት መጠየቅ ወይም
- ታክስ የሚከፈልበት ግብይት በሚያከናውንበት በማናቸውም ሰነድ ወይም ድረ-ገጽ የማሕበራዊ ሚዲያ አድራሻ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግብይት በሚያከናውንበት መድረክ የተመዘገበ ሰው መሆኑን መግለጽ፤

- ምዝገባው የታገደበት ሰው የምዝገባው መታገድ በጸናበት ቀን ወደፊት የተሸጋገረ ክሬዲት ሊደረግ የሚችል ሂሳብ ያለው እንደሆነ ክሬዲት ሊደረግ የሚገባው ሂሳብ እገዳው እስከሚሻር ድረስ እንዲቆይ ሆኖ እገዳው ሲነሳ ተፈጻሚ ይሆናል።
- ምዝገባው የታገደበት ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማከናወኑን የማይቀጥል ከሆነ ምዝገባው ታግዶ ባለበት በማናቸውም ጊዜ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የታደበት ሰው ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች አቅርቦት ለመቀጠል ከፈለገ እገዳው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ከ 15 ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ጥያቄ ማቅረብ አለበት።
- ምዝገባ የታገደበት ሰው ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች አቅርቦት ማከናወን ለመቀጠል ከፈለገ እገዳው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ካላቀረበ የእገዳው ጊዜ እንደተጠናቀቀ ምዝገባው ይሰረዛል።

## 9.2. የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን በታች በመሆን ምክንያት ስለሚቀርብ የምዝገባ ሥረዛ ማመልከቻ

- የተመዘገበ ሰው የሚያከናውነው ዓመታዊ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ዋጋ የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን ሲወርድ የተመዘገበው ሰው የተፈቀደውን ቅጽ በመጠቀም ምዝገባው እንዲሰረዝለት ሊያመለክት ይችላል። ምዝገባ እንዲሰረዝ ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው ምዝገባው ከተከናወነበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር የ 2 (ሁለት) ዓመት ጊዜ በኋላ ነው። ነገር ግን ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት መሆኑን በማመን በስህተት የተመዘገበ ሰው የምዝገባ ሥረዛ ማመልከቻውን ከተመዘገበበት ቀን በኋላ የመጀመሪያውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ማስታወቂያ ማቅረብ ከሚገባው ቀን በፊት ሊያቀርብ ይችላል።

- የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው በአንድ ዓመት ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ዋጋ የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን በታች መሆኑን ሲያምንበት ምዝገባው እንዲሠረዝ ተገቢውን ማመልከቻ ላቀረበው የተመዘገበ ሰው ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ሊሰርዝ ይችላል።
- የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው በአንድ ዓመት ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ዋጋ የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠንበታች ሲሆን እንዲሁም የታክሱ ባለስልጣን ከሚከተሉት ሁለቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ መፈፀማቸውን ሲያምንበት-
  - ➢ የተመዘገበው ሰው ተገቢ የሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ መረጃዎች ያለመያዙን፣
  - ➢ የተመዘገበው ሰው በመደበኛነት እና በአስተማማኝነት የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢውን የማያስታውቅ መሆኑን ሲያምንበት በራሱ ተነሳሽነት ለተመዘገበው ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ሊሠረዝ ይችላል።
- የተመዘገበ ሰው ዋና መስሪያ ቤት ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፣ የስራ ክፍል፣ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ምዝገባ እንዲሰረዝ ለታክሱ ባለስልጣን በጽሁፍ ሊያመለክት ይችላል። ምዝገባው የሚሰረዘው የሚከተሉት ሲሟሉ ይሆናል፦
  - ➢ የታክሱ ባልስልጣን ከዚህ ያነሰ ጊዜ ካልፈቀደ በስተቀር፤የቅርንጫፍ የተለየ ምዝገባ ቢያንስ ለሁለት አመት ጸንቶ መቆየት አለበት፣
  - ➢ ማናቸውም ድርጅት ወይም ቅርንጫፍ ለቅርንጫፍ ምዝገባ የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች ማሟላቱን ያቋረጠ እንደሆነ ኩባያው ከቅድመ-ሁኔታዎች አንዱ መሟላቱ በተቋረጠ በ 30 ቀናት ውስጥ ይህንን ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።
- የታክሱ ባለስልጣን ለቅርንጫፍ ምዝገባ የተቀመጡት ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸው የተቋረጠ ወይም ለመንግስት ገቢ ደህንነት አስፈላጊ መስሎ ከታየው የቅርንጫፍ ምዝገባን ለመሰረዝ ይችላል።
- የታክሱ ባለስልጣን የቅርንጫፍ ምዝገባ የሚቀጥል መሆን ያለመሆኑን የመወሰን ሙሉ ስልጣን አለው።
- የቅርንጫፍ ምዝገባ መሰረዝ የጸና የሚሆነው የታክሱ ባለስልጣን ምዝገባው መሰረዙን ለማስታወቅ በሚሰጠው ማስታወቂያ ከተገለጸው ቀን አንስቶ ይሆናል።

## 9.3. ምዝገባው የተሰረዘበት ሰው ግዴታዎች

አንድ ሰው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባው የተሰረዘበት እንደሆነ ፡-

- ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን የሚጠቀምባቸውን ማናቸውንም ሰነዶች እና ማናቸውንም ድረ ገጽ፣ ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክስ መድረክ ጨምሮ በማናቸውም መልኩ ይህ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ መሆኑን የሚገልፁ ድርጊቶችን ወዲያውኑ ማቆም፣
- ምዝገባው ከተሰረዘበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወይም የታክሱ ባለስልጣን በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ በሚገለጽ ቀደም ያለ ሌላ ጊዜ ውስጥ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም የመጨረሻውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የገቢ ማስታወቂያ ማቅረብ እና የሚፈለግበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል፣
- የተሰጠውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ዋና የምዝገባ የምስክር ወረቀት እና የዚህን የምስክር ወረቀት ይፋዊ ቅጂዎች ወዲያውኑ ለታክሱ ባለስልጣን የመመለስ ግዴታ አለበት።
- የተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢውን በማስታወቅ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ በመክፈል ረገድ ያለበትን ግዴታ ጨምሮ ምዝገባው ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ውስጥ ካከናወናቸው ተግባራት ወይም ካልፈፀማቸው ግዴታዎች ጋር በተያያዘ የሚኖርበት ግዴታ እና ተጠያቂነት ምዝገባው በመሰረዙ ምክንያት ቀሪ አይሆኑም።

## 9.4. ምዝገባ በሚሠረዝበት ጊዜ እንደተከናወኑ ስለሚቆጠሩ ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች

- የተመዘገበ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የተሰረዘ እንደሆነ ምዝገባው በተሰረዘ ጊዜ በእጁ የሚገኙት የንግድ ዕቃዎች እና የካፒታል ዕቃዎች ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች እንደሆኑ ይቆጠራል። ሆኖም እነዚህ ዕቃዎች ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች እንደሆኑ የሚቆጠረው የተመዘገበው ሰው እነዚህን የንግድ ዕቃዎች ወይም የካፒታል ዕቃዎች ሲገዛ ወይም ወደአገር ሲያስገባ ለከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ (ክሬዲት) ያገኘ ወይም የንግድ ዕቃዎችን በሚመለከት ለእነዚህ ዕቃዎች ማምረቻ የዋሉ ግብአቶችን ሲገዛ ወይም ወደአገር ሲያስገባ ለከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ያገኘ እንደሆነ ነው። ይህ ተፈጻሚ ሲሆን የተመዘገበው ሰው ምዝገባው ከመሰረዙ በፊት ባለው ጊዜ የንግድ ዕቃዎች ወይም የካፒታል ዕቃዎች ታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች እንዲሆኑ የማድረግ ተግባር ያከናወነ እንደሆነ ተደርጐ ይቆጠራል።

- ምዝገባው በተሰረዘ ጊዜ የንግድ ዕቃዎች በእጁ የሚገኙ የተመዘገበ ሰው ምዝገባው ከመሰረዙ በፊት ባለው ጊዜ እነዚህን ዕቃዎች በሚገዛበት ወይም ወደአገር በሚያስገባበት ጊዜ ለከፈለው የግብአት ታክስ ካገኘው ቅናሽ ለእነዚህ የንግድ ዕቃዎች ማምረቻ በዋለው ግብአት ላይ ለከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ካገኘው ቅናሽ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የውጤት ታክስ እንደተቀበለ ይቆጠራል።
- የተመዘገበ ሰው ምዝገባ በሚሰረዝበት ጊዜ በእጁ የሚገኙ የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት ተፈፃሚ በሚደረግበት ጊዜ ምዝገባው ከመሰረዙ በፊት ባለው ጊዜ በእጁ ለሚገኙ የካፒታል ዕቃዎች ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሠረት የውጤት ታክስ እንደተቀበለ ይቆጠራል። **ሀ x ለ/ሐ**
  - ➢ “ሀ” ማለት፡- የተመዘገበው ሰው የካፒታል ዕቃዎችን በገዛበት ጊዜ ያገኘው የግብአት ታክስ ተቀናሽ፣
  - ➢ “ለ” ማለት፡- በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚወሰን የተመዘገበው ሰው ምዝገባ በተሰረዘበት ጊዜ የካፒታል ዕቃዎች ያላቸው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ፣ እና
  - ➢ “ሐ” ማት፡- የካፒታል ዕቃዎች የተደረገው የመጀመሪያው ወጪ.

<u>የሙከራ ጥያቄ</u>

- ➢ ምዝገባው የተሰረዘበት ሰው ግዴታዎችን አብራራ?
- ➢ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባን ማገድ ማለት ምን ማለት ነው?

## ክፍል አስር
## የአስተዳደር እና የሥነ - ሥርዓት ደንቦች

የታክስ አስተዳደር አዋጅ የተጨማ ዕሴት ታክስ አስተዳደር በተመለከተም ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

### 10.1. የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ

- የተጨማሪ እሴት ታክስ የሂሳብ ጊዜ የሚባለው አንድ ወር ሲሆን ማናቸውም የተመዘገበ ሰው የእያንዳንዱን የሒሣብ ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የሒሣብ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ቀጥሎ ባለው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ ማቅረብ አለበት።
- ማናቸውም የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው ውስጥ ተከፋይ የሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ቢኖረውም ባይኖረውም የሒሣብ ጊዜውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

- በአንድ ወር ውስጥ በቀጥታ በገዢው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው ወይም ያልተመዘገበ የመንግሥት ተቋም ለዚህ ወር ግብይቱ በሚቀጥለው ወር የመጨረሻ ቀን ለታክሱ ባለስልጣን የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት።
- የታክሱ ባለስልጣን የእቃ እና አገልግሎት አቅርቦት የሚያከናውን ያልተመዘገበ ሰው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ ሊከፍል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በሚመለከት መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ በሚመለከት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ሊሰጥ ይችላል።
- የታክሱ ባለስልጣን ታክስ የሚከፈልበት የእቃ እና አገልግሎት አቅርቦት በሚያከናውን ሰው ላይ የሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የመክፈያውን ጊዜ የያዘ ማስታወቂያ ለከፋዩ ሰው መስጠት አለበት።
- ለከፋዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል የሚሰጠው የውሳኔ ማስታወቂያ ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም "የታክስ ውሳኔ" እንደሆነ ይቆጠራል።
- በዚህ መሰረት በከፍተኛ ያልተመዘገበ ሰው ወይም በመንግሥት ተቋም ሊቀርብ የሚገባው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ አስተዳደር አዋጁ አፈጻጸም" የታክስ ማስታወቂያ>> እና <<የራስ የታክስ ማስታወቂያ" ሆኖ ይቆጠራል።
- የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ከሂሳብ ጊዜው ቀጥሎ ባለው ወር የመጨረሻ ቀን ወይም ከዚያ በፊት በኢሌክትሮኒክ ዘዴ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት።
- የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የታክስ ማስታወቂያውን በየሶስት ወሩ ማቅረብ እንዲፈቀድለት ሊጠይቅ ይችላል። የታክሱ ባለስልጣን የውጭ አቅራቢው ግዴታውን የሚወጣ መሆኑን ካመነበት በጥያቄው መሰረት ሊፈቅድ ይችላል። የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ የውጭ አቅራቢው የሂሳብ ጊዜ ሶስት ወር ይሆናል።
- የታክስ ማስታወቂያውን በየሶስት ወሩ እንዲያቀርብ የተፈቀደለት የውጭ አቅራቢ የታክስ ማስታወቂያውን በወቅቱ የማያቀርብ እና የተጨማሪ እሴት ታክሱን በወቅቱ የማይከፍል ከሆነ የታክሱ ባለስልጣን በየሶስት ወሩ የታክስ ማስታወቂያ እንዲያቀርብ የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል።
- "ሶስት ወር" ማለት በግሪጎሪያን ቀን መቁጠሪያ ውስጥ ባለው በሶስተኛው፤ በስድስተኛው፤ በዘጠነኛው ና በአስራ ሁለተኛው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ የሶስት ወር ጊዜ ነው።

## 10.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈያ ጊዜ

- የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው የሚኖረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ የተጣራ ሒሣብ ታክሱን ሊያስታወቅ በሚገባው ጊዜ ውስጥ መክፈል አለበት፡፡
- በቀጥታ በገዢው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው ወይም ያልተመዘገበ የመንግሥት ተቋም በገዢው ተይዞ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በፈጸመበት ወር ውስጥ ታክሱን የመክፈል ግዴታው የሚቋቋም ሲሆን፤ ይህ ሰው የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ ባለበት ጊዜ ውስጥ ታክሱን መክፈል አለበት፡፡
- ማናቸውም አስመጪ ወደ ሀገር ባስገባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ዕቃዎቹን ወደ ሀገር ባስገባበት ጊዜ መክፈል አለበት፡፡
- የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ በሂሳብ ጊዜው ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቅ ባለበት ጊዜ መክፈል ይጠበቅበታል፡፡
- የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ የታክሱ ባለስልጣን በሚፈቅደው መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክሱን በአሜሪካ ዶላር፤ በዩሮ፤ በእንግሊዝ ፓውንድ ወይም በሌላ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያጸድቀው የውጭ አገር ገንዘብ ሊከፍል ይችላል፡፡
- የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈለው የገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው የኤሌክትሮኒክ ዘዴ መሆን አለበት፡፡

## 10.3. ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ታክስን ስለመሰብሰብ

- ኮሚሽኑ፡-
  - ➢ ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ዕቃዎቹ ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ ታክስን መሰብሰብ፣
  - ➢ የአስመጪውን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (ከለ) እና የዕቃዎቹን የዋጋ ኢንቮይስ መቀበል፣ እና
  - ➢ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት በፖስታ ቤት በኩል ከሚመጡ ዕቃዎች ላይ ኮሚሽኑን በመወከል ወደሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ታክሱን የመሰብሰብ ተግባር መፈጸም እንዲችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፡፡

- በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ የተመለከተው ማስተካከያ ወይም የተለየ አሠራር እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት እስካላቸው ድረስ ወደ ሀገር ስለሚገቡ እና በትራንዚት ላይ ስላሉ ዕቃዎች፣ ወደ ሀገር ስለሚገቡ ዕቃዎች ክሊራንስ፣ የጉምሩክ ቀረጥን ስለመክፈል እና ታክስን ስለማስመለስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመሰብሰብም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።
- ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመሰብሰብ ሲባል ኮሚሽኑ በጉምሩክ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን በተጨማሪ እሴት ታክስ ህግ መሰረት ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ጭምር እንደተሰጠው በመቁጠር ሊሰራበት ይችላል።

## 10.4. ከአቅርቦቱ ተጠቃሚ ላይ ስለሚጠየቅ ታክስ

I. ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው የአቅርቦቱ ተጠቃሚ በሰጠው የተሳሳተ መረጃ ወይም በፈጸመው የማጭበርበር ድርጊት ምክንያት የተመዘገበው ሰው፡-

- ➢ አቅርቦቱ ከታክስ ነጻ እንዲሆን፣
- ➢ በአቅርቦቱ ላይ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንዲሆን፣ ወይም
- ➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዳይከፈልበት ያደረገ፣ እንደሆነ ነው።

II. ከላይ የተጠቀሰው ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን የአቅርቦቱ ተጠቃሚ ተገቢ ባልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ አወሳሰን ምክንያት በአቅርቦቱ ላይ ያልከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ክፍያው በመዘግየቱ የሚከፈለውን ወለድ፣ ክፍያው በዘገየበት የሚጣለውን መቀጫ እንዲከፍል ሊጠይቀው ይችላል። የታክሱ ባስልጣን በዚህ መሠረት የአቅርቦቱ ተጠቃሚ ታክሱን እንዲከፍል ሲጠይቅ ከታች የተመለከቱትን ዝርዝር ሁኔታዎች የሚገልጽ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፡-

- ➢ የታክስ ውሳኔ ለመስጠት ያበቃውን ምክንያት፣
- ➢ በታክስ ውሳኔው መሰረት ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ በዘገየበት ሊከፈል የሚገባውን ቅጣት እና ወለድ፤ እና
- ➢ በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት ቅሬታ ሊቀርብ የሚችልበትን ጊዜ፤ ቦታ አቀራረብ።

III. የታክሱ ባለሥልጣን የተጨማሪ እሴት ታክሱን በሙሉ ወይም በከፊል፣ ክፍያ በመዘግየቱ የሚከፈል ወለድ እና ክፍያው በመዘግየቱ ከሚጣል መቀጫ ጋር አቅርቦቱን ካከናወነው ከተመዘገበው ሰው ላይ ከመጠየቅ አያግደውም። ሆኖም የታክሱ ባለስልጣን የሚጠይቀው ታክስ በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ክፍያ በመዘግየቱ ከሚከፈል ወለድ እና በዘገየበት ከሚጣል መቀጫ የበለጠ ሊሆን አይችልም። በዚህም መሠረት ከአቅርቦቱ ተጠቃሚ የሚሰበሰበው ታክስ አቅራቢው በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ላይ ይቀነሳል እንዲሁም ከአቅራቢው የሚሰበሰበው ማናቸውም ገንዘብ የአቅርቦቱ ተጠቃሚ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ ላይ ይካካሳል።

IV. ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ መሠረት በአቅርቦቱ ተጠቃሚ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ክፍያ በመዘግየቱ የሚከፈል ወለድ እና በዘገየበት የሚጣል መቀጫ የከፈለ አቅራቢ የከፈለውን ገንዘብ ከአቅርቦቱ ተጠቃሚ ሊጠይቅ ይችላል። ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ እና ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ መሰረት የተወሰነ ታክስ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት የተጠየቀ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሆኖ ይቆጠራል። የታክስ አስተዳደር አዋጅ ድንጋጌዎች የታክሱ ባለሥልጣን ከላይ በሮማን ቁጥር ሦስት የተገለጸውን ተፈጻሚ ለማድረግ የታክስ ከፋዩን የገቢ ማስታወቂያ ጨምሮ ማናቸውንም ውሳኔ ከማሻሻል አያግዱትም።

## 10.5. ከተከፋይ ሒሣብ ላይ የሚቀነስ የተጨማሪ እሴት ታክስ

- የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነው ለመንግሥት ተቋም የሆነ እንደሆነ፣ አቅርቦቱ የተፈጸመለት የመንግሥት ተቋም፡-
  - ➢ በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ 50 በመቶ ቀንሶ የማስቀረት፣
  - ➢ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው አኳኋን ቀንሶ ያስቀረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ የማድረግ እና
  - ➢ በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀሪውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሒሣብ 50 በመቶ ለተመዘገበው ሰው የመክፈል ግዴታ አለበት።

- በመንግሥት ተቋም ተቀንሶ የተያዘ ማናቸውም የተጨማሪ እሴት ታክስ አቅርቦቱን ባከናወነው የተመዘገበ ሰው ለታክሱ ባለስልጣን እንደተከፈለ ይቆጠራል፡፡
- ለመንግሥት ተቋም ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ያከናወነ እና የተጨማሪ እሴት ታክሱ ሒሳብ ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ተቀንሶ የተያዘበት የተመዘገበ ሰው አቅርቦቱ በተከናወነበት ወቅት ባለው የሒሳብ ጊዜ ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ተቀናሽ ለተደረገበት የገንዘብ መጠን ተቀናሽ የማግኘት መብት ይኖረዋል።

## 10.6. ዕቃዎችን በመመዝገብ ረገድ ስለተጣለ ገደብ

- የባለቤትነት ምዝገባ የሚያስፈልጋቸውን ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው አካል እነዚህን ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ ያስገባው ሰው የሚከተሉትን ማስረጃዎች ካላቀረበ በስተቀር መመዝገብ የለበትም ፡-
    - ➢ ወደ ሀገር በገቡት ዕቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፣ ወይም
    - ➢ ወደ ሀገር የገቡት ዕቃዎች ከታክሱ ነጻ መሆናቸውን የሚገልጽ የጉምሩክ ሰነድ።
    - ➢ ወደ ሀገር በገቡት እቃዎች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ በታክሱ ባለስልጣን የተሰጠ የምስክር ወረቀት።
- መመዝገብ ያለባቸውን ዕቃዎች የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው አካል አቅርቦቱ የተፈጸመለት ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ካላቀረበ በስተቀር መመዝገብ የለበትም፡-
    - ➢ አቅርቦቱን ያከናወነው የተመዘገበ ሰው በታክሱ ባለሥልጣን የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም የሰጠውን በአቅርቦቱ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ ወይም የሚከፈል መሆኑን የሚያረጋግጥ ዋንኛውን ደረሰኝ፣ ወይም
    - ➢ የታክሱ ባለስልጣን የሰጠውን አቅርቦቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት።
- <<የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው አካል>> ማለት፡- በሕግ የመመዝገብ ግዴታ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የመመዝገብ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

- <<መመዝገብ ያለባቸው ዕቃዎች>> ማለት፡- በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት መመዝገብ ያለባቸው ዕቃዎች ናቸው።

- የውጭ ሀገር አገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች

  - ➢ የታክሱ ባለስልጣን የመመዝገብ ግዴታ ያለበት እና ከኢትዮጵያ ውጪ ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ የሚያከናውን በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት የሌለው ሰው ለታክሱ መከፈል ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።
  - ➢ ይህም ተፈጻሚ የሚሆነው የታክሱ ባለሥልጣን የውጭ ሀገር አገልግሎት ሰጪው በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ የተጣሉበትን ግዴታዎች የማይወጣ መሆኑን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ሲኖረው ነው።
  - ➢ ስለሆነም ዋስትና ያቀረበ ሰው በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ በተጣለበት ግዴታ መሠረት ያልፈጸመ እንደሆነ የታክሱ ባልስልጣን ይህ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል እንዲሰይም ሊያስገድደው ይችላል።
  - ➢ በዚህ መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል የሆነ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ ማመልከቻ ማቅረብን፤ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብን፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈልን ጨምሮ በወከለው ሰው ስም በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ የተመለከቱ ተግባሮችን የመፈጸም ኃላፊነት አለበት።
  - ➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል ምዝገባ የሚከናወነው በወካዩ ስም ሲሆን አንድ ሰው ለብዙ ሰዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል መሆን ይችላል። ሆኖም ለእያንዳንዱ ለሚወክለው ሰው የተለያየ ምዝገባ መፈፀም አለበት። በዚህም መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል የሚሆን ሰው፡-

    - ✓ የወካዩ የታክስ እንደራሴ ሆኖ ይቆጠራል፤
    - ✓ ለሚወክለው ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስ ግዴታ የግል ተጠያቂነት ይኖርበታል።

- የታክሱ ባለስልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስ ወኪል የሚሾምበትን መንገድ፣ አኳኋን እና ተፈላጊ ሁኔታዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

## 10.7. በገዢው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው

- በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ድርጅት ሳይኖረው ከውጭ ሀገር ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከሚያከናውን የተመዘገበ ሰው ግብይት የሚፈጽም የተመዘገበ ሰው፤ የመንግሥት ተቋም ወይም ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው በሚፈጽመው በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን በታክስ ባለስልጣኑ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም ለአቅራቢው ማሳወቅ አለበት።
- በዚህ መሠረት ለአቅራቢው የሚላከው ማስታወቂያ አቅርቦቱ በተፈጸመ ጊዜ ወይም ከመፈጸሙ በፊት መሰጠት አለበት።

## 10.8. የተጨማሪ እሴት ታክስ ቅጣት

- ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ከዚህ በታች ለተመለከተው ለእያንዳንዱ ጥፋት 100 (አንድ መቶ) ሺ ብር አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፡-

➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ዋነኛ ቅጂ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት ዋና መስሪያ ቤት እንዲሁም የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ቅጂ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት በእያንዳንዱ የስራ ቦታ ያልለጠፈ እንደሆነ፤

➢ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት ማናቸውም ዌብሳይት፣ የማህበራዊ ሚዲያ ገጽ ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክ መድረክ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባውን ዝርዝር መረጃ ያልገለጸ እንደሆነ፤

➢ በስራው ላይ የተደረገውን ለውጥ ያላሳወቀ እንደሆነ፤

➢ ለታክስ ባለሥልጣኑ መረጃ ያልሰጠ እንደሆነ፤

➢ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት በማከናወን ላይ እያለ ለታክሱ ባልስልጣን ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት አቁሚያለሁ የሚል ማመልከቻ ያቀረበ ወይም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታው ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፤

➢ ምዝገባው የተሰረዘበት ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን የሚጠቀምባቸውን ማናቸውንም ሰነዶች እና ማናቸውንም ዌብሳይት፤ ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክ

መድረክ ጨምሮ በማናቸውም መልኩ ይህ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ መሆኑን የሚገልጹ ድርጊቶችን የማቆም ግዴታውን ያልተወጣ ወይም

➢ የተሰጠውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ዋና የምዝገባ የምስክር ወረቀት እና የዚህን የምስክር ወረቀት ይፋዊ ቅጂዎች ወዲያውኑ ለታክሱ ባለስልጣን ያልመለሰ፡-

✓ በተቀባዩ የሚዘጋጅ ደረሰኝ ባልቆረጠበት በእያንዳንዱ ግብይት፤

✓ የዴቢት ኖት ወይም የክሬዲት ኖት ባልቆረጠበት በእያንዳንዱ ግብይት፤

✓ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ሰነዶችን በተመለከተ በሚገባ መያዝ እና መፈጸም ሲገባው በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ መሰረት ሰነዶችን ያለ አግባብ የተጠቀመ እንደሆነ እና ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ የተጨማ እሴት ታስ ደረሰኝ፣የደቢት ሰነድ እና የክሬዲት ሰነድ የሰጠ ከሆነ

✓ ታክስ ለሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያስተዋውቀው ወይም የሚሰጠው ዋጋ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስን ያላካተተ ወይም ልገለጸ ከሆነ

- ከጠጨማሪ እሴት ታክስ ህግ ውጭ የታክስ ደረሰኝ፤ የክሬዲት ኖት ወይም የዴቢት ኖት የሰጠ ማናቸውም ሰው ለእያንዳንዱ ድርጊት 50 ሺ (ሃምሳ ሺ) ብር የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

- በገዢው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ እያለበት ይህንን ያልተወጣ የተመዘገበ ሰው፤ ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው ወይም የመንግሥት ተቋም 50ሺ (ሃምሳ ሺህ) ብር የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

## 10.9. የተጨማሪ እሴት ታክስ የታከለበት ዋጋ

- የተመዘገበ ሰው ታክስ ለሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያስተዋውቀው ወይም የሚሰጠው ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስን ማካተት ያለበት ሲሆን፣ ይህም በማስታወቂያው ወይም በሚሰጠው ዋጋ በግልጽ መመልከት አለበት፡፡
- በሚከተሉት ሁኔታዎች የተመዘገበ ሰው የሚያስተዋውቀው ወይም የሚሰጠው ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስን የማይጨምር ሊሆን ይችላል፡-

➢ ማስታወቂያው ወይም የሚሰጠው ዋጋ በአቅርቦቱ ላይ ሊከፈል የሚገባው የተጨማሪ እሴት እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲታከል የሚኖረውን የዕቃውን ዋጋ ጭምር የሚገልጽ ከሆነ፤እና

- ➢ የተጨማሪ እሴት ታክስ የታከለበትን ዋጋ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልታከለበትን ዋጋ በሚመለከት የሚወጣው ማስታወቂያ ወይም የሚሰጠው ዋጋ የሚኖረው ተፈላጊነት ወይም ውጤት እኩል ከሆነ፡፡
- የተመዘገበ ሰው የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማስታወቂያ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በሚያከናውንበት ቦታ የመግቢያ በሮች ወይም ደንበኞች ክፍያ በሚፈጽሙበት ቦታ በተገቢው ሁኔታ እስከተገለጸ ድረስ በክፍያ መቀበያ ቲኬቶች ላይ ዋጋው የተጨማሪ እሴት ታክስ የታከለበት መሆኑን መግለጽ አስፈላጊ አይሆንም፡፡
- የታክሱ ባለሥልጣን ማናቸውም የተመዘገበ ሰው ወይም የተመዘገቡ ሰዎች ቡድን የሚያቀርቡትን ዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ የሚገልጹበትን ሌላ ዘዴ ሊወስን ይችላል፡፡
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው በጨረታ ተሳታፊ የሆነ እንደሆነ፡-
  - ➢ በጨረታው የመወዳደሪያ ዋጋውን የሚያቀርበው የተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር መሆን አለበት፤ እና
  - ➢ በጨረታው አሸናፊ ከሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ በጨረታው መሠረት በሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ አለበት፡፡

## 10.10. የተመዘገበ ሰው መሞት፣ ክፍያ መፈጸም ያለመቻል ወይም መክሰር እና ንብረት በመያዣነት የተቀበለ ሰው

I. ከታች የሮማን ቁጥር ሁለት ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡-

➢ የተመዘገበው ሰው ሲሞት፣ ወይም ክፍያ መፈጸም ያለመቻሉ ወይም መክሰሩ ሲረጋገጥ፤ እና

➢ ከሚከተሉት አንዱ ሲያጋጥም፡-

- ✓ ቀደም ሲል በተመዘገበው ሰው ሲካሄዱ የነበሩ ታክስ የሚከፈልባቸውን እንቅስቃሴዎች የሞተውን፤ ክፍያ መፈጸም ያቋረጠውን ወይም የከሰረውን የተመዘገበ ሰው ሀብት የሚያስተዳድረው ሰው ሲያካሂድ፤ ወይም
- ✓ የተመዘገበውን ሰው ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ የሚያቋርጥ ማናቸውም ተግባር ሲፈጸም፡፡

II. ከላይ በሮማን ቁጥር አንድ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የተመዘገበው ሰው ሀብት አስተዳዳሪ የተመዘገበውን ሰው ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በማከናወን ተግባር እንደቀጠለ ይቆጠራል፡፡

III. ንብረት በመያዣነት የተቀበለ ሰው ቀደም ሲል ንብረቱን በመያዣነት የሰጠውን የተመዘገበ ሰው የመሬት ይዞታ ወይም ሌላ ንብረት የተረከበ እና በመያዣነት የሰጠው ሰው ሲያካሂድ የነበረውን ታክስ የሚከፈልበት የሥራ እንቅስቃሴ

ማካሄድ የቀጠለ እንደሆነ ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ ማካሄድ እስከቀጠለበት ጊዜ እና በዚያው መጠን መሬቱን ወይም ንብረቱን በመያዣ እንደሰጠው ሰው ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## 10.11. የተጨማሪ እሴት ታክስ ያለመክፈል ዕቅድ

- ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡-
  - ➢ ታክስ ያለመክፈል ዕቅድ የተዘረጋ ወይም ተግባራዊ የተደረገ ከሆነ፤
  - ➢ ማናቸውም ሰው ታክስ ያለመክፈሉን ዕቅድ በመጠቀም የታክስ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ፤ እና
  - ➢ ታክስ ያለመክፈሉ ዕቅድ ይዘት ሲመረመር፣ ታክስ ባለመክፈሉ ዕቅድ የተሳተፈ ወይም ተግባራዊ ያደረገው ሰው ወይም ካደረጉት ሰዎች አንዱ ይህንን ድርጊት የፈጸመበት ብቸኛ ዓላማ ወይም ዋነኛ ዓላማ የታክስ ጥቅም ለማግኘት ከሆነ ነው፡፡
- ይህ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን ዕቅዱ ያልተዘረጋ ወይም ተግባራዊ እንዳልሆነ በመቁጠር የተገኘውን የታክስ ጥቅም ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ ያስችላል ብሎ የሚያምንበትን እርምጃ በመውሰድ በተዘረጋው ዕቅድ ታክስ ላለመክፈል የቻለው ሰው እና ከተዘረጋው ዕቅድ ጋር ግንኙነት ያለው ማናቸውም ሰው የሚኖርበትን ተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ሊወስን ይችላል፡፡
- የታክሱ ባለሥልጣን ውሳኔ ሲሰጥ በታክስ አስተዳደር ህግ መሰረት የታክስ ውሳኔ ማሻሻያን ጨምሮ በውሳኔው ምክንያት የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ የተጣለበትን ሰው ወይም ሰዎች ግዴታ የሚገልጽ የውሳኔ ማስታወቂያ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ያለመክፈል ዕቅድ <<ዕቅድ>> ለሚለው ሀረግ <<ዕቅድ>> ማለት፡- የሚከተሉትን ይጨምራል፡-
  - ➢ በግልጽ የተደረገ ወይም በግልጽ ሳይነገር የተደረገ ቢሆንም ባይሆንም፣ በክርክር ሂደት ሕጋዊ አስገዳጅነት ቢኖረውም ባይኖረውም ስምምነት፣ ማመቻቸት ወይም ቃልኪዳን፤ ወይም
  - ➢ በአንድ ሰው ወይም በሁለት እና ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች የተፈፀመ ማናቸውም ግዴታ፣ ዕቅድ፣ የውሳኔ ሀሳብ፣ የድርጊት መርሀ ግብር፣ ወይም የድርጊት ስልት እና

  <<የታክስ ጥቅም>> ማለት፡-
  - ➢ አንድ ሰው ሊከፍል የሚገባውን ተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን መቀነስ፤
  - ➢ ሊያገኝ የሚገባውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ መጨመር፤
  - ➢ ሊያገኝ የሚገባውን ተመላሽ መጨመር፤

➢ ሊከፍል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማዘግየት፤

➢ ሊያገኝ የሚገባውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ ማፋጠን፤

➢ ሊከፍል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከማዘግየት ወይም ሊያገኝ የሚገባውን የግብአት ታክስ ተቀናሽ ከማፋጠን የሚገኝ ማናቸውም ሌላ ጥቅም፤

➢ ታክስ ሊከፈልበት የሚገባው አቅርቦት፣ ወደ ሀገር የሚገባ ዕቃ ወይም በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት፤ እንደሁኔታው፤ ታክስ የማይከፈልበት አቅርቦት፣ ታክስ የማይከፈልበት ወደሀገር የሚገባ ዕቃ ወይም ታክስ የማይከፈልበት በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት እንዲሆን የሚያስችል ማናቸውም ድርጊት፤ ወይም

➢ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ከማከናወን ውጪ ባለ ድርጊት ጥቅም ላይ የዋለው ወይም የሚውለው ተቀናሽ የሚሆን ግዢ የግብአት ታክስ ተቀናሽ እንዲገኝበት ማድረግ።

## 10.12. የገንዘብ ምንዛሪ

- ማናቸውም የገንዘብ መጠን በብር መገለጽ አለበት።
- የገንዘቡ መጠን የተገለጸው በብር ሳይሆን በሌላ የገንዘብ ዓይነት የሆነ እንደሆነ፦

➢ ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎችን በሚመለከት፣ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን የጉምሩክ ቀረጥ ለማስላት በጉምሩክ አዋጅ ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደውን የውጭ ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መሠረት በማድረግ የገንዘቡ መጠን ወደብር እንዲቀየር ይደረጋል፤

➢ በሌሎች ማናቸውም ሁኔታዎች የገንዘቡ መጠን ወደ ብር የሚለወጠው የገንዘቡ መጠን ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ አፈጻጸም በሒሣብ ስሌት ውስጥ መካተት በሚገባው ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሥራ ላይ ባዋለው በውጭው ሀገር ገንዘብ እና በኢትዮጵያ ብር መካከል ባለው የውጭ ገንዘብ የምንዛሪ ተመን ይሆናል።

- የውጭ ሀገር ገንዘብን ወደብር ለመለወጥ ከሚከተሉት አንዱን ዘዴ ሊጠቀም ይችላል፦

➢ በሌሎች ማናቸውም ሁኔታዎች የገንዘቡ መጠን ወደ ብር የሚለወጠው የገንዘቡ መጠን ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ አፈጻጸም በሒሣብ ስሌት ውስጥ መካተት በሚገባው ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሥራ ላይ ባዋለው በውጭው ሀገር ገንዘብ እና በኢትዮጵያ ብር መካከል ባለው የውጭ ገንዘብ የምንዛሪ ተመን ይሆናል።

- አግባብነት ባለው የሒሣብ ጊዜ የመጨረሻ ቀን በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ጸንቶ የሚሰራበትን በውጭ ሀገር ገንዘብ እና በኢትዮጵያ ብር መካከል ያለውን የምንዛሪ ተመን፤ ወይም
- ከታክሱ ባለሥልጣን ጋር ስምምነት የሚደረስበትን ሌላ ዘዴ። በዚህ መሰረት የውጭ ሀገር አቅራቢ የውጭ ሀገር ገንዘብን ወደብር ለመለወጥ የሚመርጠው አሠራር አቅራቢው ለሚፈጽመው አቅርቦት ሁሉ ተፈጻሚ የሚደረግ ሲሆን፣ የታክሱ ባለስልጣን ካልተስማማ በስተቀር አቅራቢው ምርጫውን ከአንድ ዓመት በፊት ሊሰርዝ አይችልም።

<<የውጭ ሀገር አቅራቢ>> ማለት፡-

- በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚታዘዝ እቃ አቅራቢ፤ ወይም
- ከሩቅ የሚሰጥ አገልግሎት አቅራቢ፤
- የኤሌክትሮኒክ ማከፋፈያ ገበያ አስተዳዳሪ የሆነ ሰው ነው። <u>የሙከራ</u>

<u>ጥያቄ</u>

- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ያለመክፈል ዕቅድ ማት ምን ማለት ነው?
- በተጨማሪ ዕሴት ታክስ ህግ መሰረት የውጭ ሀገር ገንዘብ ወደብር የሚቀየርበትን ዘዴ አብራራ?

## ማጠቃለያ

ይህ ሰነድ ለግብር ከፋዮችም ሆነ ግብር ከፋይ ላልሆኑ ለማንኛውም ዜጋ ስለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ማስተማሪያ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ይሆን ዘንድ በገቢዎች ሚኒስቴር የተዘጋጀ ነው።

**ማጣቀሻ**

- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016
- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 575/2017
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚሆኑ እቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1006/2016
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚሆነውን የኤሌክትሪክ እና የውሀ ፍጆታ መጠን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1021/2016